አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

አማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረምረቃ መርሃ ግብር

# በሶስት የሻሸመኔ ከተማ ትምህርት ቤቶች የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የክፍል ውስጥ አተገባበር


በካሳሁን አጬሮ



ነሐሴ 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በሶስት የሻሸመኔ ከተማ ትምህርት ቤቶች የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የክፍል ውስጥ አተገባበር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ አማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረምረቃ መርሃ ግብር

ለተግባራዊ ሥነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ካሳሁን አጤሮ

ነሐሴ 2010 ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## የድኅረምረቃ መርሃ ግብር

# በሶስት የሻሸመኔ ከተማ ትምህርት ቤቶች የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የክፍል ውስጥ አተገባበር


በ

ካሳሁን አጤሮ


የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | | |
|---|---|---|
| አማካሪ | ጌታቸው እንዳላማው ዶ/ር | ፊርማ------------------------- |
| ፈታኝ | ጌታቸው አዱኛ ዶ/ር | ፊርማ------------------------- |
| ፈታኝ | ግርማ ገብሬ ዶ/ር | ፊርማ------------------------- |

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ በሄድኩበት መንገድ ሁሉ ለመራኝና እስከዚህ ቀን ላደረሰኝ ለእግዚአብሄር ከዘላለም እስከ ለዘላለም ክብር ይሁን፡፡

በመቀጠልም አማካርዬና መምህሬ የሆኑት ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ በማዘጋጅበት ጊዜ እያንዳንዱን የጥናቱን ክፍል በትኩረት በመመልከት፣ በየምእራፉ ረቂቆችን በማንበብና ስህተቶችን በማረም፣ አስተያየት በመስጠት እገዛ ስላደረጉልኝ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

እንዲሁም ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ ሳዘጋጅ መረጃዎችን እንድሰበስብ ለተባበሩኝ በሻሸመኔ ከተማ መስተዳድር ለአሌሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህርና የአማርኛ ቋንቋ መምህር፣ ለመልካ ኤሳ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህርና የአማርኛ ቋንቋ መምህር፣ ለኤዱ መዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህርና የአማርኛ ቋንቋ መምህር እንዲሁም በሶስቱም ትምህርት ቤት ለሚማሩና የጽሁፍ መጠይቁን በመሙላት መረጃ ለሰጡኝ ተማሪዎች በሙሉ ልባዊ ምስጋና ይድረሳቸው አላለሁ፡፡

በተጨማሪም በጉድለቴ ከጎኔ በመቆም፣ በማበረታታትና ድጋፍ በማድረግ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ከግብ እንዲደርስ የበኩሏን አስተዋጾ ላበረከተችልኝ ለውድ ባለቤቴ ለወ/ሮ ያለምዘርፍ መኮንን ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመለገስ በማበረታታት ድጋፍ ላደረጉልኝ ለት/ቤቴ ርእሰ መምህራንና መምህራን፣ እንዲሁም የትምህርት ወጪዬን በመሸፈን ላስተማረኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ፡፡

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሶስት የሻሸመኔ ከተማ ትምህርት ቤቶች የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞድል የክፍል ውስጥ አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ የሞዴሉን አተገባበር ሲፈትሽ አይነተዊ እና መጠናዊ የምርምር ስልትን በመጠቀም በጥናቱ ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ ሰጥቷል፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በሻሻመኔ ከተማ መስተዳድር ከሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተራ እጣ ናሙና ዘዴ በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች ነው፡፡ ለዚህ ጥናት በናሙናነት በተመረጡት ሶስት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን ለመፈተሽ በአጥኚው የተደረገ የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ፣ ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መልኩ ከተሰበሰቡ በኋላ የተገኙት መረጃዎች ተጠቃለው አይነታዊ የምርምር ዘዴ በሆነው በገላጭ የአተናተን ዘዴ እና በመጠናዊ የአተናተን ዘዴ በመቶኛ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው በደረጃው ተግባራዊ የሆነው የሞዴሉ የክፍል ውስጥ አተገባበር ምንም እንኳን ሞዴሉን ተጠቅሞ በክፍል ውስጥ ትግበራው ቢካሄድም መምህራን ሞዴሉን በወሰዱት ስልጠና መሰረት በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ትግበራው ጉድለቶች አሉበት፡፡ ለዚህም በምክኒያትነት የሚጠቀሰው ተግባራትን ሰርቶ ለማጠናቀቅ የጊዜ እጥረት፣ የተማሪ ቁጥር መብዛት፣ ተጨማሪ የንባብ መጻሃፍ አለመገኘት እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በመጨረሻም በጥናቱ የተገኙትን ውጤቶች በመመርኮዝ የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል የክፍል ውስጥ አተገባበር ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን ጠቃሚ አስተያየቶች ማለትም በክፍል ውስጥ የተማሪ ቁጥር መጠነኛ ቢሆን፣ ተጨማሪ የንባብ መጽሃፍት ለፈጣን አንባቢዎች ቢዘጋጁ … የሚሉ በአጥኚው ተሰንዝሯል፡፡*

# ማውጫ


ምስጋና……. ........................................................................................................ i
አጠቃሎ……. ...................................................................................................... ii
ማውጫ……. ...................................................................................................... iii
የሰንጠረዥ ማውጫ .............................................................................................. vi
ምዕራፍ አንድ ...................................................................................................... 1
መግቢያ……. ....................................................................................................... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ...................................................................................................... 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት .................................................................................. 4
1.3 የጥናቱ አላማ ................................................................................................... 5
1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ......................................................................................... 5
1.5 የጥናቱ ወሰን ................................................................................................... 6
1.6 የጥናቱ ውስንነት ............................................................................................. 6
ምእራፍ ሁለት ................................................................................................... 7
ክለሳ ድርሳን ...................................................................................................... 7
2.1 የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴል ምንነት ........................................ 7
2.2 የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴል አወቃቀር ..................................... 9
2.3 የሞዴሉ ዝርዝር የትምህርት መዋቅር ............................................................... 11
2.3.1 እኔ ልስራ -እኔ እተገብረዋለሁ .......................................................................... 11
2.3.2 አብረን እንስራ -አብረን እንተግብር ................................................................. 14
2.3.2.1 በሞዴሉ የማዳመጥ ትምህርት አተገባበር ......................................................... 15
2.3.2.2 በሞዴሉ የማንበብ ትምህርት አተገባበር .......................................................... 17
2.3.2.3 በሞዴሉ የንግግር ትምህርት አተገባበር ........................................................... 17
2.3.2.4 በሞዴሉ የመጻፍ ትምህርት አተገባበር ............................................................. 18
2.3.3 እናንተ ስሩ -ቢጋራ እና በግል ተግብሩ .............................................................. 18
2.3.3.1 በጋራ ተግብሩ .............................................................................................. 18
2.3.3.2. በግል ተግብሩ ............................................................................................. 22
2.4 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት .................................................................................. 23

ምዕራፍ ሶስት ...................................................................................................25
የጥናቱ ዘዴ ...................................................................................................25
3.1 የአጠናን ዘዴ ...................................................................................................25
3.2 የመረጃ ምንጮች ...................................................................................................25
3.3 የናሙና አመራረጥ ...................................................................................................25
3.3.1 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ ...................................................................................................25
3.3.2 የመምህራን አመራረጥ ...................................................................................................26
3.3.3 የተማሪዎች አመራረጥ ...................................................................................................26
3.3.4 የመማሪያ ክፍል አመራረጥ ...................................................................................................26
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ...................................................................................................26
3.4.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ ...................................................................................................27
3.4.2 ቃለ መጠይቅ ...................................................................................................27
3.4.3 የጽሁፍ መጠይቆች ...................................................................................................28
3.4.4 የሙከራ ጥናት ...................................................................................................29
3.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ...................................................................................................29
ምዕራፍ አራት ...................................................................................................31
የመረጃዎች ትንተናና የጥናቱ ውጤት ...................................................................................................31
4.1 የተጠኚ መምህራንና ተማሪዎች ዳራ ...................................................................................................31
4.2 ከክፍል ውስጥ ምልከታ እና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ...................................................................................................33
4.2.1 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የግልና የቡድን ተግባራት ...................................................................................................33
4.2.2 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የጾታ ተኮር አካቶ ትምህርት እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አተገባበር ...................................................................................................36
4.2.3 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የማንበብ ተግባር ...................................................................................................39
4.2.4 በእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የመጻፍ ተግባር42
4.2.5 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ አናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የማዳመጥ ተግባር ...................................................................................................43
4.2.6 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የንግግር ተግባር ...................................................................................................45

4.2.7 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ግብረ መልስ፣ ድጋፍና ማበልጸግ ........ 47

4.3 ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 49

4.3.1 የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴልን በተመለከተ ... 50

4.3.2 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴል የመምህሩ ሚና በተመለከተ ........ 51

4.3.3 በሞዴሉ አብረን እንስራ ክንውንን በተመለከተ ........ 51

4.3.4 በሞዴሉ የግልና የቡድን ተግባራትን በተመለከተ ........ 53

4.3.5 በሞዴሉ የማንበብ ተግባርን በተመለከተ ........ 53

4.3.6 በሞዴሉ የንግግር እና የጽህፈት ተግባርን በተመለከተ ........ 54

4.3.7 ተግባራትን በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ተግብሮ መጨረስን በተመለከተ ........ 55

4.3.8 ማበረታቻና ግብረ መልስን በተመለከተ ........ 56

4.3.9 ተከታታይ ምዘናን በተመለከተ ........ 57

4.3.10 በሞዴሉ የጾታ እኩልነትን በተመለከተ ........ 58

4.3.11 በሞዴሉ አካቶ ትምህርት ልዩ ፍላጎት ትምህርትን በተመለከተ ........ 59

ምዕራፍ አምስት ........ 60

ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳብ ........ 60

5.1 ማጠቃለያ ........ 60

5.2 የመፍትሄ ሃሳብ ........ 61

ዋቢ ፅሁፎች ........ 63

አባሪዎች.. ........ 67

አባሪ አንድ ........ 67

አባሪ ሁለት ........ 71

አባሪ ሶስት ........ 75

አባሪ አራት ........ 77

አባሪ አምስት ........ 80

አባሪ ስድስት ........ 84

# የሰንጠረዥ ማውጫ


ሰንጠረዥ 1. የመምህራን ዳራ ........ 31

ሰንጠረዥ 2. የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች ዳራ ........ 32

ሰንጠረዥ 3. በእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ከቡድንና ከግል ተግባራት አተገባበር፡፡ ........ 33

ሰንጠረዥ 4. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የግልና የቡድን ተግባራት የተማሪዎች ምላሽ ........ 34

ሰንጠረዥ 5. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ጾታ ተኮር፣ አካቶ ትምህርትና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አተገባበር በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ........ 36

ሰንጠረዥ 6. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞደል የጾታ ተኮር፣ አካቶ ትምህርትና ልዩ ፍላጎት ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች ምላሽ፡፡ ........ 37

ሰንጠረዠ 7. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናነተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የማንበብ ተግባር የክፍል ምልከታ መረጃ፡፡ ........ 39

ሰንጠረዥ 8. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የማንበብ ተግባር የተማሪዎች ምላሽ፡፡ ........ 40

ሰንጠረዥ 9. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የመጻፍ ተግባር የክፍል ምልከታ መረጃ ........ 42

ሰንጠረዥ 10. በእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የመጻፍ ተግባርን አስመልክቶ ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ፡፡ ........ 42

ሰንጠረዥ 11. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የማዳመጥ ተግባር የክፍል ምልከታ መረጃ፡፡ ........ 43

ሰንጠረዥ 12. በእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የማዳመጥ ተግባር የተማሪዎች ምላሽ፡፡ ........ 44

ሰንጠረዥ 13. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የንግግር ተግባር የክፍል ምልከታ መረጃ፡፡ ........ 45

ሰንጠረዥ 14. በእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣ አናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የንግግር ተግባር የተማሪዎች ምላሽ፡፡ ........ 45

ሰንጠረዥ 15. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ግብረመልስ፣ ድጋፍ እና ማበልጸግን በተመለከተ በተመለከተ የክፍል ምልከታ መረጃ ........ 47

ሰንጠረዥ 16. በእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ግብረ መልስ፣ ድጋፍና እና ማበልጸግን በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ፡፡ ........ 48

# ምዕራፍ አንድ
# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በየትኛውም ደረጃ ባሉ የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ዘንድ የቋንቋ ትምህርት አቀባበልና የተቀበሉትን በተግበር ላይ በሚያዉሉበት ጊዜ በርካታ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት አቀባበልና አተገባበር ላይ በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ዘንድ ችግሮች የሚስተዋሉ ከሆነ እነዚህ ችግሮች እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ዘልቀው እንደሚታዩ Richards and Rodgers (1986) ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች ከዝቅተኛው የክፍል ደረጃ ተነስተው እስከ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ሊዘልቁ የሚችሉበት ምክንያቶች በርካቶች እንደሆኑ Ellis (1989) እና Norrish (1983) ያስረዳሉ፡፡ Richards and Rodgers (1986) በበኩላቸው ለተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚጠበቀውን ያህል ውጤታማ ያለመሆን ችግሮች በርካታ ቢሆኑም ከተገለጹት ዋና ዋና ችግሮች ውስጥ አንዱ የመምህሩ የማስተማርያ ስልት (ዘዴ) ወይም ተማሪው የቋንቋ ትምህርትን የሚማርበት ስልት (ዘዴ) እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

የማስተማር ዘዴ መምህራን የትምህርት አይነቱን ለተማሪዎች የሚያስተላልፉበት፣ ዕውቀት እንዲጨብጡ የሚረዱበት ክህሎትና አመለካከትን ልምድንና ባህርይን የሚያዳብሩበት፣ ተማሪዎችን ከውጫዊ ሁኔታ ጋር የሚያስታውቁበት ዘዴ ነው (Brown,1994)፡፡ ስለዚህም የማስተማር ዘዴ በራሱ ለውጥ የሚያመጣ ሳይሆን ዕውቀትን ለማስጨበጥ የሚረዳ መምህሩ የሚፈልገውን እውቀት ለማስተላለፍ የሚጠቀምበት መንገድ ነው፡፡ ጥሩ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉና የሚፈለገው የባህርይ ለውጥ እንዲመጣ እገዛ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የማስተማሪያ ዘዴዎችን አጠቃቀም አስመልክተው Larsen and Richards (1986) ሲገልጹ ዋናው ነገር አንዱን የማስተማሪያ ዘዴ ከሌላው የመምረጥ ጉዳይ ሳይሆን እንደአመቺነቱ ለመጠቀም እያንዳንዱን ዘዴ በሚገባ ማወቅ ጠቃሚ ነው ይላሉ፡፡

በአንፃሩ Raimes (1983) የቋንቋ ትምህርት ለማስተማር ተገቢ የሆነውን የማስተማር ዘዴ ለመምረጥ አስቸጋሪ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ Richardes and Rodgers (2001) በበኩላቸው ጥሩ የማስተማሪያ ዘዴ ነው የሚባለው ጥሩ የመማሪያ ዘዴ ሊሆን ይችላል በማለት የተሻለ ዘዴን የመምረጥን አስቸጋሪነት ይጠቁማሉ፡፡ ምክንያቱም የእያንዳንዱን ዘዴ አተገባበር ሊወስኑ የሚችሉ የተለያዩ ተላውጦዎች (variables) ስላሉ ነው፡፡ ለምሳሌ ቋንቋው የሚነገርበት ማህበራዊ አውድ፣ የቋንቋው ትምህርት አላማ፣ ትምህርቱ የሚሰጥበት የጊዜ መጠን፣ በአንድ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ብዛት፣ ስነ ልሳናዊ፣ ስነ ልቦናዊና አእምሮታዊ ችግሮች የተማሪዎች ዳራ የተለያየ መሆኑ አንዱ ዘዴ በሁሉም ሁኔታዎችና ቦታዎች ላይ በብቃት ሊያገለግል አለመቻሉ ነው፡፡ ስለዚህም መምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎቻቸውንና የሚያስተምሩበትን ክፍል ተማሪዎች ሁኔታ በማጥናት የተማሪዎቻቸውን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር አመቺ የሆነውን ማስተማሪያ ዘዴ በመምረጥ ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡

ቋንቋን የመማር ማስተማር ክንውን አያሌ ዘመናትን ያስቆጠረ ታሪክ እንዳለው ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ በአለፉት ብዙ አመታት ቋንቋ ማስተማርን በተመለከተ የተለያዩ የትኩረት አቅጣጫዎችን እየተከተለ የተጓዘ መስክ ነው፡፡ ከ1970ዎቹ በፊት የነበረው የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ትኩረት በቋንቋ ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ የቋንቋ ትምህርት ብቻ ተግባራዊ መደረግ አለበት በሚለው ላይ ነበር በማለት Tudor (1996) ይገልጻሉ፡፡ ይህ ሂደትም የቋንቋ ተማሪዎችን የመማር ተሳትፎ የዘነጋ እና ቋንቋን ከመልመድ ተፈጥሯዊ ሂደት ጋር የማይጣጣም እንደነበር ተገንዝበው የቋንቋ ምሁራኑ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸውን Tudor (1996:41) ያስረዳሉ፡፡

በየዘመናቱ የተነሱ የቋንቋ ትምህርት ምሁራን በቋንቋ ማስተማር ዘዴ ላይ በርካታ ምርምር ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከ2000 ዓመት በላይ እድሜ ካስቆጠረው ከሰዋ ስው ወትርጉም የማስተማር ዘዴ ጀምሮ እስከ ዘመናችን የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ አይነቶች ድረስ በርካታ ለውጦች ተካሂደዋል፡፡

ቋንቋን በመማር ማስተማር ክንውን ሂደት ረገድ በተከሰተው የለውጥ ፍላጎት በተመለከተ Wondon and Joan (1987፡15) እንደገለጹት እ.ኤ.አ. ከ1970ዎቹ

በፊት የቋንቋ መማር ማስተማር ትኩረት ከነበረው ብቁ ወይም ውጤታማ የቋንቋ ማስተማሪያ ስነ ዘዴዎችን ከማፈላለግና በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ ረገድ በርካታ ጥረቶችና ለውጦች ተካሂደዋል ወይም ተደርገዋል፡፡ በአገራችንም የቋንቋ ትምህርት የማስተማርያ ዘዴዎች የለውጥ ሂደትን ተከትሎ ከመምህር መራሽ የማስተማር ዘዴ ወደ ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴ ሽግግር ተደርጓል፡፡ ይህንን በተመለከተ

> በሀገራችን ለቋንቋ ትምህርትም ሆነ ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ቀድሞ በማስተማርያ ዘዴነት ሲያገለግል የቆየው መምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ነበረ፡፡ በዚህ ዘዴ መምህሩ ብቸኛና ፍጹማዊ የእውቀት ምንጭ ነኝ ብሎ ያስባል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚያስተምረውን ትምህርት ሁሌም ረጅም ጊዜን ወስዶ በስፋት መናገርና በተማሪዎች በኩል ደግሞ ማድመጥን ይጠይቃል፡፡ እውቀት፣ ክህሎትና የአመለካከት ለውጥ የሚመጣበት ሂደት ላይ ከማተኮር ይልቅ በተማሪዎች የፈተና ውጤት ለይ ያተኩራል፡፡ ዋነኛው አላማውም ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት እንዲከልሱና እንዲሸመድዱ የሚያበረታታ ነው፡፡ ይህ ዘዴ ተማሪው በራሱ እንዲመራመር እድል የሚሰጥ አልነበረም፡፡ በመሆኑም በተማሪው ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አምጥቶ ነበር፡፡

በማለት አለማየሁ (2009:25) ገልጸዋል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ተግባራዊ የተደረገው የማስተማር ዘዴ ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴ ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች እንደ መምህር መራሽ የትምህርት አቀራረብ በአንድ ወገን መረጃ ተቀባዮች የሚሆኑበት ሳይሆን ራሳቸው ተማሪዎች መረጃ ፈላጊዎችና አዲስ ግኝት አፍላቂዎች የሚሆኑበት ስልት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህም የማስተማር ስልት የሚጠበቀውን ያህል ውጤት አላመጣም፡፡

በቀደመው ጊዜ ተግባራዊ ሲደረግ የነበረው መምህር መራሽ የማስተማሪያ ዘዴ እንዲሁም በኋላ ተግባራዊ ሲደረግ ከነበረው ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተውጣጣና የተሸለ ነው ተብሎ በውጭ የተጀመረው እና በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የማስተማሪያ ዘዴ ቀስ በቀስ ሚናን የማስተላለፍ (የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ እናንተ ስሩ) ሞዴል (The Gradual Release of Responsibility Model) ነው፡፡ ስለዚህ ሞዴል Duke and Pearson, (2002, P. 211). ሲገልጹ ቀስ በቀስ ሚናን እያስተላለፉ መሄድ ሞዴል መምህሩ ሁሉንም ሃላፊነት ተሸክሞ ከመጓዝ ይልቅ ሀላፊነትን ቀስ በቀስ ለተማሪዎችም በማሸጋገር ተግባራትን መስራት ነው ይላሉ፡፡

ቀስ በቀስ ሚናን ማስተላለፍ ሞዴል የተለያዩ የማስተማርያ ሞዴሎችን በመቀመር አሁን ላለበት ደረጃ የደረሰው በዳግ ፊሸር እና ናንሲ ፌሪ የፈጠራ ልምምድ ነው፡፡ በልምምዳቸው ተለዋዋጭ ሞዴልን በመጠቀም ምቹ የሆኑ የመማርያ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ችለዋል (Levy 2007)፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አነሳሽ የሆነው ምክንያት በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በ2007 ዓ.ም. ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሃፍ የክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ በ2008 ዓ.ም. በኦሮሚያ በተለያዩ ዞኖች ለአንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስልጠና ተሰጥቶ ነበር፡፡ የስልጠናው አላማ በአዲሱ መጽሃፍ የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴልን ተጠቅመው እንዴት እንደሚያስተምሩ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የታለመ ነበር፡፡

ስልጠናው ለቋንቋው መምህራን በበቂ ሁኔታ ይሰጥ እንጂ ሰልጣኝ መምህራኑ በስልጠናው ወቅት ያገኙትን የእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የክፍል ውስጥ አተገባበር እውቀት እና ልምድ ከስልጠናው በኋላ በክፍል ውስጥ ተገባራዊ እያደረጉት ነው? ወይስ ቋንቋውን እያስተማሩ ያሉት በቀድሞው የማስተማር ዘዴ ነው? መምህራኑ የማስተማር ሞዴሉን አስመልክተው የወሰዱትን ስልጠና መነሻ አድርገው ቋንቋን ሲያስተምሩ ከስልጠናው ካገኙት እውቀት ጋር አጣጥመው የመጠቀም ሁኔታ ምን ይመስላል? መምህራን በአዲሱ የመማሪያ መጽሃፍና የመምህሩ መምሪያ ላይ ያሉትን ተግባራት አዲሱን የማስተማሪያ ሞዴል በመጠቀም በአግባቡ በክፍል ውስጥ ይተገብራሉ ወይ? እንዲሁም አዲሱ የማስተማሪያ ሞዴል በተማሪ የትምህርት አቀባበልና ውጤት ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ለማምጣት ችሏል ወይ? ለተማሪውስ አዲሱ የማስተማር ሞዴል ለትምህርት አቀባበሉ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮለታል? በሚሉና በመሰል ጉዳዮች ላይ ከስልጠነው በኋላ ስለ አተገባበሩ ምንም ክትትል እንዳልተደረገ አጥኚው በመገንዘቡ ይህንን ጥናት እንዲያጠና አነሳሽ ምክንያቶች ሆነዋል፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ለኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በ2007 ዓ.ም. አዲስ በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ቀስ በቀስ ሚናን የማስተላለፍ ሞዴል ወይም የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ አዲስ የማስተማርያ ሞዴል የክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ በሻሸመኔ ከተማ በተመረጡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት የአተገባበሩን ሁኔታ ለመፈተሽ ሲሆን ዝርዝር አላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡-

- እኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናነተ ስሩ የማስተማር ሞዴል መምህራን በወሰዱት ስልጠና መሰረት የትኞቹን ተግብረዋል የሚለውን መገምገም፣
- መምህሩ በክፍል ውስጥ የእኔ ልስራ፣ አበረን እንስራ፣ እናነተ ስሩ ሞዴልን በልስራ ጊዜ እንዴት እንደሚተገብር መፈተሽ፣
- ሞዴሉ ለተማሪዎች ምቹ የመማር ሁኔታን እንደፈጠረላቸው መመርመር፣
- በእንስራ ጊዜ መምህሩ ከተማሪዎች ጋር አብሮ ሲተገበር የአተገባበሩን ሁኔታ መፈተሽ፣
- ተማሪዎቹ በስሩ ጊዜ ተግባራትን እንደተ እንደሚተገብሩ መፈተሸ፣
- በሞዴሉ የክሂሎችን አተገባበር ሁኔታ መፈተሸ፡፡

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- በተሰጠው ስልጠና እና በመምህራን ትግበራ መካከል ያለውን ክፍተት በመገንዘብ ለአሰልጣኞች ወደፊት ሊሻሻል ስለሚገባው ነገር ፍንጭ መስጠት፣
- ለትምህርት ባለሞያዎች የሞዴሉን ጠንካራና ደካማ ጎን ለመገምገም መነሻ ሃሳብ ይሆናል፣
- ሞዴሉን በሚመለከት በቀጣይ በትምህርት ባለሞያዎች በሚደረግ የመምህራን የቋንቋ ትምህርት ስልጠና ግብአት በመሆን ያገለግላል፣
- ስለማስተማሪያ ሞዴሉ የተሻለ ግንዛቤ ስለሚፈጥር መምህራን ጠንካራውን በማጎልበት ደካማውን በማሻሻል የትምህርት ስራን ለማቀላጠፍ ያገለግላል፣
- ሞዴሉን ለመተግበር የሚያስችሉ የተለያዩ አጋዥ የትምህርት ቁሳቁሶች ለሚያዘጋጁ ክፍሎች የመንደርደሪያ ሃሳብ ያስገኛል፣

- መምህራን በትግበራው ላይ የታዩ ደካማ ጎኖችን በመለየት ተገቢ የሆነ ማስተካከያ በማድረግ ተማሪዎችን ለመርዳት ሊያገለግል ይችላል፡፡
- በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ ወደፊት ጥናት ለሚያደርጉ አጥኚዎች መነሻ ሃሳብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት አጥኚ ጥናቱን የሚያካሂደው በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ መስተዳድር በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ነው፡፡ ጥናቱ በሻሸመኔ ከተማ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ደግሞ በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ሶስት የተመረጡ ትምህርት ቤቶች በሚማሩ አፍ ፈት የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ብቻ ጥናቱ ይካሄዳል፡፡ ሌሎች የክፍል ደረጃዎች በዚህ ጥናት ውስጥ አይዳሰሱም፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረቱ በአዲሱ የማስተማር ሞዴል እኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ወይም ቀስ በቀስ ሚናን እያስተላለፉ እያበቁ መሄድ የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ቢሆንም ጥናቱ በክፍል ደረጃው የሞዴሉን አተገባበር ሲያጠና የስነ ልሳን ትምህርት አተገባበርን፣ የስነ ጽሁፍ ትምህርት አተገባበርን የመርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀምን፣ የመምህሩ መምርያና እና የተማሪ መጽሃፍ አጠቃቀምን በዝርዝር ማጥናትን አያካትትም፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

አጥኚው ይህንን ጥናት በሚያጠናበት ወቅት የተለያዩ ችግሮች ወይም ውስንነቶች አጋጥመውታል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ለጥናቱ መረጃ እንዲሰጡ የተጠየቁ መረጃ ሰጪዎች መረጃ ለመስጠት ሙሉ ፍቃደኛ አለመሆንና ከመደበኛ ስራ ሰአት ውጪ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ፍቃደኛ አለመሆን፣ አጥኚው ከመደበኛ ስራ በተጓዳኝ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እና የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተን የጊዜ እጥረት ማጋጠሙ፣ የማስተማር ሞዴሉ ወይም ዘዴው በሃገራችን በጅምር ላይ ያለ በመሆኑ አስፈላጊ የሆኑ ክለሳ ድርሳናትን እና ተዛማጅ ቀደምት ስራዎችን በመረጃ ምንጭነት ለማግኘት መቸገር ዋና ዋናዎቹ አጥኚውን የገጠሙ ተግዳሮቶች ነበሩ፡፡

# ምእራፍ ሁለት
# ክለሳ ድርሳን

## 2.1 የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴል ምንነት

ቀስ በቀስ የማብቃት አቀራረብ ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ የተመረጡ ይዘቶችን በቅደም ተከተል በልዩ ልዩ ተገቢ የትምህርት ምራፎች ውስጥ በማደራጀት ተከታታይ ትምህርታዊ መተጋገዝ እና ድጋፍ የሚደረግበት አቀራረብ ነው፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ግልጽ በሆነ መንገድ በሚቀርብ ማብራሪያ ተጀምሮ ክሂሎችን ሰርቶ ወይም ተግብሮ በማሳየት ለምሳሌ፡-በማጣመር፣ በመነጠል ከሁኔታቸው ተነስቶ የራስን ትርጉም በመስጠት የሚተገበር ሲሆን በመጨረሻም በተጨማሪ ደጋፊ ተግባራት እና ወቅታዊ ግብረ መልስ የሚጠናከር ነው (Buehl, 2005)::

ቀስ በስ የማብቃት የማስተማር ሞዴል የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርአተ ትምህርት ለማስተማር በዋናነት የቀረበ ሞዴል ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን ትምህርቱን እና ተግባራቱን ሞዴል ሆነው እየሰሩ በማሳየት ቀስ በቀስ ተማሪዎቻቸው እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩና እንዲበቁ የሚያስችል የማስተማር ዘዴ ነው፡፡ ዘዴው የቋንቋ ክሂሎችን በቀጥታና ስልታዊ በሆነ መንገድ ለመማር የሚያስችል ነው፡፡ ዘዴው በመማር ማስተማር ሂደት የመምህራንና የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚያሳድግ እና ተማሪዎች ትምህረቱን መረዳታቸውን ማረጋገጥ የሚያስችል ነው (Fisher and Frey, 2007)::

የትምህርት ባለሞያዎች የሞዴሉን የክፍል ውስጥ አተገባበር አስመልክተው ባደረጉት ምርምር መመርያዎችን ግልጽ በሆነ መንገድ በማስተላለፍ ወደተግባር ልምምድ በማሸጋገር ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው ወደሚለማመዱበት ደረጃ እንደሚደርሳቸው በምርምራቸው አረጋግጠዋል፡፡ በተጨማሪም የምርምሩ ውጤት እንዳረጋገጠው መምህሩ የራሱን ተግባር ሲወጣ ተማሪዎችም በትምህርቱ ሙሉ ሃላፊነት ተሰምቷቸው እንዲማሩ የሚያደርግ መሆኑን ነው (Pearson, and Gallagher,1983)::

ይህንን የማስተማር ሞዴል አስመልክቶ Buehl, (2005). ሲገልጹ የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴል ተግባራዊ የሚሆነው በቀን ውስጥ፣ በሳምንት ውስጥ፣ በወር ውስጥ ወይም በአመት ውስጥ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ አገላለጽ ይህ ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ ወይም የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴል አስረግጦ የሚናገረው ተማሪዎችን በሚሰጣቸው መመርያ ወደላቀ የአስተሳሰብ ደረጃ ማምጣት እና የላቀ የትምህርት ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማድረግ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማስቻል ነው ይላሉ፡፡

የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴል በተለየ የማስተማር ዘዴ በትምህርት ሂደት ውስጥ ቀስ በቀስ ሃላፊነት ከመምህሩ ወደ ተማሪዎች የሚተላለፍበት የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ የማስተማርያ ሞዴል መምህሩ ወደ ተማሪዎች እንዲሸጋገር እና ተማሪው እንዲያውቀው የተፈለገውን ነገር በመቅረጽ ተማሪዎች ሁሉንም ሃላፊነት ወስደው ወደሚሰሩበት ደረጃ የሚሸጋገሩበትን ንድፍ ይነድፋል፡፡ ትምህርቱ በሚቀረጽበት ጊዜ ትምህርቱ የሚሸጋገርላቸው ተማሪዎች በራስ የመተማመን መንፈስ የሚፈጥርላቸው እና ትምህርቱንም የራሳቸው አድርገውት ስለትምህርቱ ሃላፊነት እንዲወስዱ በሚያስችል ሁኔታ ይቀረጻል፡፡ በዚህ ሞዴል ተማሪዎች ተለይቶ የተተኮረውን ወይም ለትምህርት የተለየውን ተግባር የራሳቸው አድርገው እንዲያዳብሩት እና በአእምሯቸው ልቀው አርቆ አሳቢ እንዲሆኑ በሚያስችል ሁኔታ ትምህርቱ ይሰጣል (Buehl, 2005: 36)

የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ ሞዴልን ለማሳካትና ትምህርቱን ከግብ ለማድረስ የትምህርቱን ቁልፍ ጉዳይ ማወቅ ቀዳሚው ነገር ነው፡፡ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባር ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆንና በግላቸው ሲተገብሩ ለችግሮች መፍትሄ ለማምጣት የሚችሉበትን መንገድ እና የአፈታት ደረጃውንም ይወስናሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ተማሪዎቹ የተሰጣቸውን ተግባር የትኞቹን ያለምንም እርዳታ እንደሚተገብሩና የትኞቹን በመተጋገዝ እንደሚተገብሩ ለይተው ይረዳሉ፡፡ ተማሪዎች በሞዴሉ ሲማሩ የሞዴሉን የአተገባበር ደረጃዎች በመለየት በተላያዩ ተግባራት በየደረጃው ይሳተፋሉ፡፡ መምህሩም በዚህ ሂደት ተማሪዎቹን በመለየት ቀድመው ተግባሩን ላጠናቀቁት ችሎታቸውን የበለጠ የሚያዳብሩትን ጠጠር ያለ ተግባር በመስጠት እና ወደኋላ ለቀሩት ባሳዩት ክፍተትና በፍላጎታቸው ላይ

የተመሰረተ ተግባር ለመስጠት እና ተማሪዎችን ለማገዝ እድሉን ያገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መምህራን በየአተገባበር ደረጃዎቹ ላይ የተማሪዎችን ተሳትፎ በማጠናከር እያንዳንዱ ተማሪ በነጻነት እንዲወዳደር ያስችሉታል፡፡ ተማሪው በነጻነት እራሱን ችሎ ተግባራትን እስኪተገብሩ ድረስ መምህራን መከታተልና ሚናቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል (Levy, 2007) ::


## 2.2 የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴል አወቃቀር

የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል መዋቅር መምህሩ ሞዴል ሆኖ ያለውን እውቀት ቀስ በቀስ ከተማሪዎች ጋር በጋራ ወደሚሰራበት እና ወደሚያሳይበት ደረጃ የሚወርድበት ከዚያም ተማሪ ከተማሪ ጋር በትብብር ወደሚሰራበት ብሎም ተማሪው እራሱን ችሎ በግሉ የሚማርበት ደረጃ የሚወርድ መዋቅር ነው፡፡ በዚህ ሂደት መምህሩ ሁሉንም ሃላፊነት ተግብሮ ከማሳየት ሃላፊነት ወደ ተማሪዎች ሁሉንም ሃላፊነት ወስደው እንዲተገብሩ የማድረግ ሂደትን ተከትሎ ይዋቀራል፡፡ በሌላ መልኩ በዚህ መዋቅር መምህሩ ቀስ በቀስ ተግባሩ እየቀነሰ ሲመጣ ተማሪው ደግሞ ቀስ በቀስ ተግባሩ ወይም ሃላፊነቱ የሚጨምርበት ነው፡፡ በዚህ ሂደት በዚህ መዋቅር ተማሪው ቀስ በቀስ ሃላፊነቱ እየጨመረ ስለሚመጣ ተወዳዳሪ ሆኖ ብቻውን የመማር አቅም ያጎለብታል (Duke and Pearson 2002፡25)::

ልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል ዘወትር በመዋቅሩ መሰረት የሚተገበር መሆን አለበት፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ከነዚህ መዋቅሮች ውስጥ በስሩ ግዜ በቡድን ከጓደኛ ጋር ሆኖ መስራትን ወደ ጎን በመተው በግል ተግባር ላይ ብቻ ትኩረት ይደረጋል፡፡ ይህ ደግሞ የሞዴሉን ትክክለኛ መዋቅር ስለሚያዛባ እንዲሁም ተማሪዎች ከአቻዎቻቸው ጋር ነጻ ሆነው የሚወያዩበትንና ሃሳብ ለሃሳብ የሚለዋወጡበትን እድል ስለሚያስቀር ትምህርቱን ሙሉ አያደርገውም፡፡ በሞዴሉ መምህሩ ከተማሪዎች ጋር ሲተገብር፣ ተማሪዎች ከተማሪዎች ጋር በትብብር ሲማሩ በሚመሰረተው ቡድን ውስጥ ጾታ ተኮር ትምህርት፣ አካቶ ትምህርት፣ አካል ጉዳተኛ፣ የልዩ ተሰጥኦ ባለቤት ተማሪዎች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል (Fisher and Frey 2008:2)፡፡

የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ ሞዴል የተሟላ መዋቅር ለኡደታዊ የመማር ጠባይ እውቅና ይሰጣል፡፡ መምህሩም ይህንን ኡደት እንደ ትምህርቱ ጠባይ እና እንደ አስፈላጊነቱ ሊያዘዋውረው ይችላል፡፡

Fisher and Frey (2008) የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴልን መዋቅር በምስል እንደሚከተለው አስቀምጠውታል፡፡




Fisher and Frey (2008:3) Better Learning Through structured Teaching

በዚህ ሞዴል መዋቅር ሁል ጊዜ ትምህርቱ የሚጀምረው ከተተኳሪ ትምህርት አላማ አተገባበር ብቻ ነው ብሎ መወሰን አይቻልም፡፡ ከትምህርቱን መሪ ሆኖ ማሳየት ጀምረን ወደ ትብብር መማር ከዚያም ወደ ግል ተግባር ወይም መማር ልናመራ እንችላለን፡፡ መምህራን አንዳንዴ ሞዴሉን ሲተገብሩ ትምህርቱን በግል ከመማር ተግባር ጀምረው (ለምሳሌ በንግግር ወይም በፍጥነት ጽሁፍ) ወደ ከጓደኛ ጋር በትብብር መማር ብሎም ትምህርቱን መሪ ሆኖ ወደማሳየት ሊወስዱት ይችላሉ፡፡ ይህንን ተግባር ስንተገብር በዋነኛነት ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ጥልቅ ትምህርት ለመስጠት አስፈላጊውና ጠቃሚው ነገር ተማሪዎች ይህንን የሞዴሉን መዋቅር ተገንዝበው አዲስ ትምህርት ሲያጋጥማቸው በደረጃው ትምህርቱን እንዴት የራሳቸው ያደርጉታል የሚል ነው (Fisher and Frey 2008:3)::

ተማሪዎች ሊማሩ የታቀደውን ትምህርት ከእነሱ በእውቀት ከላቁ እና ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ሲተገብሩ ወይም ሲሰሩ የማሰብ ደረጃቸው የላቀ እንዲሆን ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል፡፡ ቀስ በቀስ የማብቃት ሞዴል ሶስት ደረጃዎች አሉት እነዚህም እኔ ልስራ (እኔ እተገብረዋለሁ) ፣ አብረን እንስራ (አብረን እንተግብር) እናንተ ስሩ(በጋራ እና በግል ተግብሩ) የሚሉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ የመዋቅሩ ተግባራት ውስጥ የመጀመርያው እና ሁለተኛው የመዋቅሩ ደረጃ በመምህሩ መሪነት የሚተገበር ሲሆን ቀጣዩ የመዋቅር ደረጃ ደግሞ ተማሪዎች የተግባሩን ሙሉ ሃላፊነት ወስደው ተግባራትን የሚተገብሩበት ደረጃ ነው፡፡በጋራ ስራ ውስጥ አዋቂዎች ወይም ታላላቆች እውቀታቸውን ለሌሎች ጀማሪ ተማሪዎች የሚያስተላልፉበት የተለያየ መንገድ አለ፡፡ ይህ የእውቀት ሽግግር ደግሞ እውን የሚሆነው በተሳትፎ ውስጥ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በመጀመርያው የትምህርት ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን መርዳት ተማሪው አቅሙን እስኪያጎለብት ድረስ ይቀጥላል፡፡ በሂደት ግን ተማሪው እራስን ችሎ መማርን ሲቀጥል እና እራሱን ችሎ መተግበር ሲችል የሌሎች ድጋፍ በሂደት ይቋረጣል ወይም ይቆማል (Tharp, and Gallimore, 1991:42-62)::

## 2.3 የሞዴሉ ዝርዝር የትምህርት መዋቅር

የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴል ሶስት ደረጃዎች አሉት፡፡ እነዚህም ልስራ (ተተኳሪ ትምህርትን መተግበር)፣ እንስራ (ትምህርቱን በተግባር አብረው እየሰሩ ማሳየት) እና ስሩ (ተማሪዎች በጋራ አብረው እየሰሩ መማር እና በግል እየሰሩ መማር) የሚሉ ናቸው (Fisher and Frey 2008:3)::

### 2.3.1 እኔ ልስራ -እኔ እተገብረዋለሁ

ይህ ደረጃ በሞዴሉ መዋቅር የመጀመርያው ክፍል ሲሆን መምህሩ የአዲሱን ትምህርት ተግባር አላማ ሞዴል በመሆን የሚገልጽበት ደረጃ ነው፡፡ በመዋቅሩ መምህሩ ሊያስተምር የተዘጋጀበትን ትምህርት ያቀርባል፡፡ በዚህ ተግባር ወቅት የመምህሩ ሚና ጎልቶ የሚታይበት እና ተማሪዎቹ መምህሩ የሚገልጸውን በጥሞናና በጥንቃቄ የሚከታተሉበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ዋናው ቁም ነገር እንዲተላለፍ የተፈለገው እውቀት ከመምህሩ ወደ ተማሪዎች መተላለፉ ነው፡፡ በተጨማሪም መምህራን የእውቀት ማእከላት ስለሆኑ፣ የያዙትን እውቀት ወይም መረጃ ቀስ በቀስ

ወደተማሪው ይለቂታል፡፡ ይህንን ተግባር መምህሩ ሲተገብር መረጃ ማስተላለፍ፣ ስለነገሩ መረጃ መስጠት፣ ምሳሌ መሆንና ምሳሌዎችን ማመንጨት ይጠበቅበታል (Levy, 2007 )

Fisher and Frey (2008:3) በእኔ ልስራ ጊዜ ተተኳሪው ትምህርት በሞዴሉ አጠቃላይ የማስተማርያ ንድፍ ወሳኝ አካል እንዲሁም እጅግ አስፈላጊው እና የመጀመርያው ክፍል ወይም ደረጃ ነው፡፡ ተተኳሪ ትምህርቱን መምህሩ ሲያቀርብ በሁሉም ተማሪ ፊት እና ሁሉም ተማሪ በግልጽ እንዲሰማ በማድረግ ነው፡፡ በተለምዶ ይህ ተግባር የሚተገበረው ለ15 ደቂቃ ያክል ሲሆን ጊዜው እንደ አስፈላጊነቱ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ሊረዝምና ሊያጥር ይችላል በማለት ገልጸዋል፡፡

በዚህ ክፍል ወይም ደረጃ መምህሩ ሞዴል በመሆን ስለትምህርቱ ያለውን አመለካከት፣ አስተሳሰብና መረዳት ለተማሪዎች የሚያቀርብበት ደረጃ ነው፡፡ በደረጃው እንዲማሩ የታቀደው ትምህርት እና በትምህርቱ የሚገኘው ውጤት ወይም የሚመጣው ለውጥ ግልጽ በሆነ መንገድ የሚተዋወቅበት ነው፡፡ በተጨማሪም በዚህ ደረጃ መምህሩ በሞዴልነት በሚገልጸው የትምህርቱ አላማ ውስጥ የቀደመ እውቀቱን በማነሳሳት እንዲጠቀምበት እድል ይሰጠዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር መምህሩ የትምህርቱን ይዘት ግብ፣ የቋንቋ መማር ግብ እና ማህበራዊ ግብ በዝርዝር ማስቀመጥ ይጠበቅበታል (Kong and Pearson 2003:42-62)::

ተማሪዎች ክህሎትን፣ ጽንሰ ሃሳብን፣ ስልትን እንዴት እንደሚጠቀሙበት ሞዴል ሲቀርብላቸው የበለጠ ይማራሉ ወይም ግንዛቤ ያገኛሉ፡፡ አስተማሪው/ዋ የእውቀት (ኮግኒቲቭ) ተሸካሚና የሂደቱ ወይም የስልቱ ምንጭ ነው/ናት፡፡ በዚህ ጊዜ አስተማሪው/ዋ ለተማሪዎቹ እውቀት ለማጋራት ዝግጁ የሚሆኑበት ነው፡፡ በትግበራው ሂደትም መምህራን ተማሪዎች እየተማሩ ካሉት ክህሎት ወይም አስትራቴጂ ጋር ተያያዥነት ያለው ሞዴል ተግባር ያፈልቃሉ፡፡ በዚህ መዋቅር ደረጃ ተማሪዎቹ አስተማሪው ስለትምህረቱ አቅጣጫ በሚያሳያቸው ካርታ ላይ ተመርኩዘው እንዲጓዙ የሚያስችል ትክክለኛ ክህሎት ወይም ስልት ነድፈው ወደ ትግበራ ይሸጋገራሉ፡፡ በሂደቱም ተማሪዎቹ መምህሩ ሞዴል ሆኖ ስለትምህርቱ ያለውን ሃሳብ ሲያንጸባርቅ ተማሪዎች በጥሞና ማዳመጥ አለባቸው፡፡ እንዲገነዘቡት

የታቀደውን ትምህርት እና በትምህርቱ የሚገኘውንም ውጤት በጥሞና ሊያጤኑት ይገባል (Tharp, and Gallimore, 1991:42-62)፡፡

በእኔ ልስራ ጊዜ መምህሩ በክፍል ውስጥ ሞዴል ሆኖ ተግባራትን ሲተገብር የጾታ ትምህርትን፣ አካቶ ትምህርትን፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርትን፣ አካል ጉዳተኞችን ከግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ ተግባራትን ማከናወን አለበት (ትምህርት ሚኒስቴር 2007)፡፡

በሞዴሉ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ነገሮች አንዱ የጾታ ጉዳይ ነው፡፡ በእኔ ልስራ ጊዜ መምህራን ወንድና ሴት ተማሪዎችን እኩል ተሳታፊዎች እና ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን የክፍል ውስጥ ሁኔታዎች የመፍጠርና የማመቻቸት ሃላፊነት አለባቸው፡፡ መምህሩ በሞዴሉ ከመጀመርያ ትገበራ ጀምሮ የጾታ እኩልነትን በመቀበል ወይም የጾታ አድሎ ያሰወገደ ተግባር ለተማሪዎች ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ ተግባራትን በክፍል ውስት ሲተገብሩ ሁለቱንም ጾታ በእኩል በመጥራት እኩል ተግባር በመስጠት በእኩል ተሳትፏቸውን ማረጋገጥ አለባቸው (ትምህርት ሚኒስቴር 2007)፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር(2007) አገላለጽ ጾታን በተመለከተ መምህሩ ሞዴል ሆነው ተግባራትን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የሚከተሉትን ከጾታ ጋር የተገናኙ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገበት አለባቸው፡፡

- በክፍል ውስጥ ለሴቶችም ሆነ ለወንዶች የተሻለ የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር ለማስተማርያ መሳሪያዎች፣ ለክፍል አደረጃጀት፣ ለክፍል ውስጥ ግንኙነት ለጾታዊ እድገት ትኩረት ሰጥተው ሁለቱም ጾታዎች ጥሩ የመማር አካባቢ እንዲፈጠርላቸው ማድረግ አለባቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ለማስተማርያነት የሚጠቀሙባቸው የትምህርት መሳሪያዎች፣ ጽሁፍና ገለጻዎች ወንድና ሴት ጾታዎችን በትክክል ከመወከል እና ከመሳል አንጻር ትክክለኛነታቸውን እየገመገሙ ማቅረብ አለባቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ የተማሪዎች አቀማመጥ ሁሉንም ወንድና ሴት ተማሪዎች በእኩል ንቁ ተሳተፊ የሚያደርግ መሆን አለበት፡፡

- በወንድና ሴት ተማሪዎች ላይ የሚታየውን አካላዊና ስነልቦናዊ ለውጦችን በመገንዘብ ለሁለቱም ጾታዎች ተገቢ የሆነ ምክር መስጠት፡፡

በሞዴሉ በመጀመርያ መዋቅር ትምህርቱን ሲያቀርቡ ሌላው ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ አካቶ ትምህርት ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የምጡቅ አእምሮ ባለቤት የሆኑ ተማሪዎች፣ ከሌላ ባህልና ቋንቋ የመጡ ተማሪዎች፣ በኑሯቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች፣ በቆዳ ቀለም ለየት ያሉ ተማሪዎች፣ ማህበረሰቡ ከለመደው ጠባይ ወጣ ያሉ ተማሪዎች፣ ወላጅ አልባ ተማሪዎች፣ በተለያየ ህመም የተጠቁ ተማሪዎች እና የመሳሰሉ ተማሪዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ መምህሩ በሞዴል ትግበራው ወቅት ከግንዛቤ ሊያስገባቸው ይገባል (ትምህርት ሚኒስቴር 2007)፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር (2007) አገላለጽ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች እንደማንኛውም ተማሪ በእኩል የመማር እድል ማግኘት አለባቸው፡፡ ስለዚህ መምህራን በክፍል ውስጥ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ጨምሮ ሁሉንም ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ተስማሚ የትምህርት አካባቢ ተፈትሮላቸው መማር አለባቸው፡፡ መምህሩም በእኔ ልስራ ጊዜ እነዚህ ተማሪዎች እንደሚኖሩ አስቦ ተግባራትን ማቀድ አለበት ይላል፡፡

### 2.3.2 አብረን እንስራ -አብረን እንተግብር

አብረን እንስራ በሞዴሉ ሁለተኛ የመዋቅር ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ መምህሩና ተማሪው በጋራ አብረው ተግባራትን የሚተገብሩበት ወይም የሚሰሩበት ደረጃ ነው፡፡ መምህሩ ቀድሞ የተገበረውንና ለተማሪዎች ያሳየውን ተግባር ከተማሪዎች ጋር አብሮ በመስራት የሚያለማምድበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተማሪዎች የትምህርቱን አደረጃጀት በቅደም ተከተል ከመምህሩ ጋር አብረው በጋራ ይተገብራሉ፡፡ መምህሩ ቀደም ብለው የተለዩና ተማሪዎቹ ማወቅ ያለባቸውን የትምህርት ይዘት ወይም ቁልፍ ነጥብ እንዲያስታውሱ፣ ክፍተቶችን እንዲሞሉ፣ የተጀመሩትን እንዲጨርሱ እና የመሳሰሉትን ተግባራት ከተማሪዎች ጋር አብሮ የሚተገብርበት ደረጃ ነው (Fisher and Frey 2007:23)፡፡

ትምህርቱን በተግባር በማሳየት ደረጃ መምህሩ ለተማሪዎች ተግብሮ ያሳያቸውን ይዘት ወደ ተማሪዎች የሚያሸጋግርበት ወይም የሚያስተላልፍበት ሂደት ነው፡፡ መምህሩ በዚህ ደረጃ ረጅም ገለጻ ከማድረግ ይልቅ በውይይት በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ይረዳል፡፡ በዚህ ምእራፍ ወይም ክፍል ተግባራትን ተግብሮ ሲያሳይ የባህሪ ለውጥ ትግበራን መሰረት አድርጎ ትምህርቱን ያቀርባል፡፡ በእንስራ ተማሪዎች ሊደርሱበት ይገባል ወደተባለው ደረጃ ወይም ወደ ታላሚ ግብ ለማድረስ ብርቱ ድጋፍ የሚደረግበት የመዋቅሩ ክፍል ነው፡፡ በተጨማሪም መምህሩ እንደ አቀራረብ ሁንታው የትምህርቱን ይዘት፣ የትምህርቱን ሂደት እና በትምህርቱ የተገኘውን ውጤት ይገመግማል (Kong, and Pearson 2003: 85-90)

Fisher and Frey (2008:3) በበኩላቸው በዚህ ተግባር ጊዜ ተማሪዎቹ የትምህርቱን ይዘት የመረዳት አቅማቸው እንዲጨምር መምህሩ ተማሪዎችን ለትምህርቱ ማነሳሳት፣ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎችን መምራት ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሁሉንም ተማሪ ማዳረስ ቢቻልም በንባብ ተግባር ጊዜ ግን አነስተኛ ቡድን መመስረት አስፈላጊ ይሆናል ይላሉ፡፡

በእኔ ልስራ ጊዜ መመህሩ የተማሪዎችን ፍላጎት በሚገባ በመገምገም ክሂላቸው የሚዳብርበትን ሁኔታ ለማየት እድል ያገኝበታል፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መምህሩ ከተማሪዎች ጋር ሲተገብር ሊገነዘባቸው የሚገቡ ቁልፍ ጉዳዮች አሉ፡፡ መምህሩ ከተማሪዎች ጋር ሲተገብር የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ማለትም የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የማዳመጥ እና የመናገር ክሂል ደረጃ በሚገባ በመለየት ተማሪዎችን መርዳት አለበት፡፡ በልስራ ጊዜ መምህሩ አራቱን ክሂሎች የማስጨበጥ አላማውን ከግብ ለማድረስ እና የቋንቋ ትምህርት አላማን ከግብ ለማድረስ በትግበራው ወቅት በክሂሎች ጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ላይ ተመስረቶ ከተማሪዎች ጋር መስራት አለበት (Tharp, and Gallimore, 1991: 35-37)::

### 2.3.2.1 በሞዴሉ የማዳመጥ ትምህርት አተገባበር

የማዳመጥ ትምህርት በክፍል ውስጥ የሚተገበረው የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ ለማዳበር ነው፡፡

Kral, (1996፡ 189) ይህንን አስመልክተው ለተማሪዎች የሚቀርበው የማዳመጥ ትምህርት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ከእለት ወደ እለት እያደገ መሄድ እንዳለበት ይገልጻሉ፡፡ ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ትምህርቱ በእቅድ ሊቀርብላቸው እና ሊተገብሩት ያስፈልጋል፡፡ አብረን የምንተገብረው ተግባርም በተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ ልዩ ልዩ መልመጃዎችን የያዙና በልዩ ልዩ መርጃ መሳሪያዎችም የታገዙ ሊሆኑ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡

የማዳመጥ ትምህርት አተገባበር ሶስት ደረጃዎች አሉት፡፡ እነዚህም ቅድመ ማዳመጥ፣ የማዳመጥ ሂደት እና ድህረ ማዳመጥ ናቸው፡፡ በቅድመ ማዳመት ተግባር ጊዜ ተማሪዎች ስለሚያዳምጡት ታሪክ፣ በታሪኩ ውስጥ ሊነሱ ስለሚችሉ ገጸባህሪያት ገጸባህሪያቱ ስለሚንቀሳቀሱበት ቦታ እና ጊዜ እንዲሁም በታሪኩ ውስጥ ስለሁነቶች ቅደም ተከተል ያሰላስላሉ፡፡ በማዳመጥ ሂደት ጊዜ ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን የማዳመጥ ትምህርት በጥሞና በማዳመጥ መረጃዎችን የሚይዙበት ጊዜ ሲሆን በድህረ ማዳመጥ ጊዜ ደግሞ ካዳመጡት ታሪክ ውስጥ የሚጠየቁትን ጥያቄ የሚመልሱበት ደረጃ ነው፡፡

የተማሪዎች የማዳመጥ ችሎታ ለማዳበር በትምህርት ቤት የሚሰጥ የማዳመጥ ትምህርት የተለያዩ አላማዎች አሉት፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ማዳመጥን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የማዳመጥ ትምህርት አላማዎችን መሰረት አድርገው መሆን አለበት፡፡ እነዚህም፡- የሚሰሙትን ድምጾች በመለየት መልእክትን ለመረዳት፣ እውቀትን ለማግኘት እና መረጃን ለመቀበል እንዲሁም በሚያገኙት መረጃ ችግሮችን ለመፍታት፣ መልእክቶችን እየገመገሙ ራስን በማዝናት ንግግርን ለማድነቅ የሚሉ ናቸው፡፡ (በድሉ 2007፣ 68-70)፡፡

በዚህ ተግባር መምህሩ ተማሪዎቹ ለማወቅ የፈለጉትን በትክክል ማግኘታቸውን ወይም አለማግኘታቸውን ማየት፣ ካልተገነዘቡ ለምን ሊገነዘቡ እንዳልቻሉ ምክንያቱን ለይቶ ለመወቅ፣ የንግግሩን ርእስ ወይም ቋንቋ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በጥልቀት ለመመርመር፣ የተማሪዎችን ዝንባሌ እና አመለካከት ወይም ፍላጎት ለመገንዘብ እድሉን ያገኛሉ (Underwood, 1989:183)::

### 2.3.2.2 በሞዴሉ የማንበብ ትምህርት አተገባበር

አንብቦ መረዳትና ዳራዊ ወይም ቀዳሚ እውቀት ብርቱ ቁርኝት እንዳላቸው ጥናቶች ያመለክታሉ፣ በመሆኑም ተማሪዎች በንባብ ትግበራ ውስጥ ሲያልፉ ሙሉ ለሙሉ ከባዶ ተነስተው እንዳልሆነ ልንገነዘብ ይገባል፡፡ ይህ እውነት ደግሞ ለልጆች የምናቀርባቸው ምንባቦች በምን አይነት መሰረት ላይ እንደሚመረኮዙ ተነበው በፍሬ ነገሮቻቸው እንዲደረስም በአንባቢዎቹ አእምሮ ውስጥ ከተከማቹ ቀዳሚ እውቀቶችና ልምዶች ጋር እየተገናዘቡ ክንውኑ እንደሚቀጥል መምህራን ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ በመሆኑም መምህራንም ይህንን ውጫዊ እና ውስጣዊ ጥምረት ተገንዝበው ተማሪዎችን መርዳት አለባቸው (ደረጀ ፣ 2007፣ 97-98)::

በንባብ ትምህርት ውስጥ አንብቦ መረዳት ችሎታን ማዳበር የንባብ ትምህርት ዋንኛ አላማ ከመሆኑም በላይ ተማሪዎቹ ያነበቡትን መተንተን፣ መገንዘብ፣ መተርጎም ወዘተ ችሎታቸውን የሚያሳዩበት ነው፡፡ የተጻፉ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የቀደመ እውቀትን መጠቀም፣ ስለሚያነቡት ትምህርት ትንበያ ማካሄድ፣ የትምህርተ ድምጽ ግንዛቤን፣ የንግግር ድምጽ ግንዛቤን፣ አቀላጥፎ ማንበብን በተግባር ላይ ማዋል አለባቸው፡፡ መምህራንም ተማሪዎች የተሻለ አንባቢ እንዲሆኑ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይጠበቅባቸዋል (ትምህርት ሚኒስቴር 2007)

### 2.3.2.3 በሞዴሉ የንግግር ትምህርት አተገባበር

የንግግር ትምህርት የተማሪዎችን የማንበብ አድማስ ያሰፋል፣ የመግባባት ችሎታቸውን ከቀደመ ችሎታቸው በላይ እንዲልቅ ያደርጋል፡፡ የቋንቋው ተናገሪ ማህበረሰብ ቋንቋውን በምን አይነት ሁኔታ እንደሚጠቀምበት እውቀትና ክህሎት ማግኘት የሚቻለው በንግግር ትምህርት ስለሆነ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በግልና በቡድን ማለማመድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ንግግርን ስናስተምር ህበረተሰቡ በሚጠቀምበት ትክክለኛ መልኩ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ መጠቀም በሚያስችል መልኩ እየተገበርን እያሳየን ተማሪውም በዚሁ አይነት እንዲተገብር በማለማመድ፣ ልምምዱን በመቆጣጠር፣ ስህተቶችን በማረም ትምህርቱን ልንመራ ይገባል (ትምህርት ሚኒስቴር 2007)፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር (2009) በበኩሉ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የንግግር ክሂልን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚማሩት የንግግር ችሎታቸውን ለማዳበር ነው፡፡ ስለዚህ

የንግግር ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ጊዜ ድግግሞሽን፣ ተግባራዊ ልምምድን፣ ተፈጥሯዊ የቋንቋ አጠቃቀምን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ትምህርቱ ሊተገበር ይገባል ይላል፡፡

### 2.3.2.4 በሞዴሉ የመጻፍ ትምህርት አተገባበር

የጽህፈት ትምህርት የንግግር ቋንቋን ወደምልክት ለውጠን ሃሳባችንን የምንገልጽበት የመግባብያ ስልት በመሆኑ ተማሪዎች ሃሳባቸውን በተሸለ መንገድ ለመግለጽ በሚችሉበት መንገድ ትምህርቱ ተቀርጾ መምህሩ ከተማሪዎች ጋር በክፍል ውስጥ ይተገብራል፡፡ የህንን ተግባር መምህሩ ሲያለማምዳቸው ደጋግመው እንዲያስቡ እና እንዲመራመሩ በሚያደርግ ሁኔታ መሆን አለበት፡፡ ተማሪዎቹ ጽህፈትን በሚለማመዱበት ጊዜ ተያያዥ በሆነ መልኩ ስለቃላት ማጣመርና መነጠል ፣ ስለ አገባብ፣ ስለስርአተ ነጥቦች አጠቃቀም ወዘተ ግንዛቤ ይፈጥራሉ፡፡ መምህሩ ተማሪዎች በጽሁፍ ሃሳባቸውን በተሸለ መንገድ ለመግለጽ በሚያስችል መልኩ ቃላትን እና የአረፍተ ነገር መዋቅር ለመምረጥ ጥረት እንዲያደርጉ በማለማመድ ክሂላቸው እንዲዳብር ማድረግ አለበት (ትምህርት ሚኒስቴር 2007)

በአጠቃላይ የጽህፈት ትምህርት ተግባር የቅድመ ጽህፈት ተግባራትን፣ ረቂቅ መጻፍን፣ መከለስን፣ ማስተካከልን እና አርትኦትን መሰረት አድርጎ ይተገበራል፡፡

### 2.3.3 እናንተ ስሩ -በጋራ እና በግል ተግብሩ

ይህ የሞዴሉ ሶስተኛው የመዋቅር ደረጃ በውስጡ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ እነሱም አብራችሁ ተግብሩ እና በግል ተግብሩ የሚሉ ናቸው፡፡

### 2.3.3.1 በጋራ ተግብሩ

ይህ የማስተማር ሞዴል በሶስተኛው የሞዴሉ የመዋቀር ደረጃ የመጀመርያው ክፍል ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ መምህሩ ለተማሪዎች ያሳያቸውንና ያለማመዳቸውን ተግባር ተማሪዎች በጋራ የሚለማመዱበት የመዋቅሩ ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተማሪዎቹ ቀድሞ በመምህሩ የተተገበሩትን፣ በጋራ የሰሩትን እና የተለማመዱትን የበለጠ እንዲያጠናክሩ እና የተማሩትን እንዲያስታውሱ እድል የሚሰጥበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በትክክል መረዳት አለመረዳታቸውን የሚገነዘቡበት ደረጃ ነው፡፡ ተማሪዎች በጋራ የሰሩትን ትምህርት በሚገመግሙበት

ጊዜ ተማሪዎቹ ስለትምህርቱ ያላቸው መረዳት ምን ያህል እንደሆነ መምህሩ በቂ ግንዛቤ ሊያገኝበት ይችላል (Fisher and Frey 2008:3)፡፡

Levy, (2007) በበኩላቸው ቀስ በቀስ ሚናን ማስተላለፍ ሞዴል በጋራ መማር ትግበራ ሂደት መምህሩ ተማሪዎቹ የበለጠ ሃላፊነት ወስደው እንዲሰሩ እሱ ተግብሮ ያሳያቸውን እውቀትና ክህሎት ተማሪዎች እንዲተገብሩት ወይም እንዲያደርጉት እድሉን የሚሰጥበት ነው፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች ከእኩዮቻቸው ጋር አብረው በሚማማሩበት ጊዜ በጋራ ለመስራትና የጋራ ግንዛቤ ለመያዝ የበለጠ ሃላፊነት እንዲሰማቸው ያደርጋቸዋል ይላሉ፡፡

Maynes, Julien-Schultz, (2010: 65) በዚህ መዋቅር አተገባበር ላይ አስተማሪው ዋና ባለድርሻ አይደለም፡፡ ነገር ግን የተሰጠውን ተግባር በቡድን ለተደራጁ ተማሪዎች እንደየቡድኑ ሁኔታ የተለያየ ተግባር ሊያቀርብ ይችላል፡፡ በቡድን የተደራጁት ተማሪዎች በዚህ ሁኔታ የሚተገበረውን ተግባር ለማጠናቀቅ እውቀታቸውን እርስ በራሳቸው በመከፋፈል አንዳቸው ለሌላኛቸው እያሳዩ በአንድነት ይተገብራሉ፤ ይማራሉ::

በትብብር የመማር ክፍለ ጊዜ የማስተማር ዘዴዎች ብዙውን ጊዜ ቸል ይባላሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ከተለመደው የትምህርት አሰጣጥ ለየት ባለ መልኩ ተማሪዎች የእርስ በእርስ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡበት ሂደት ነው፡፡ በዚህ መንገድ ተማሪዎች አስተሳሰባቸውንና ሀገመረዳታቸውን እንዲያጠናክሩ የሚያስችል ሁኔታን ይፈጥራሉ፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች እንዲተገብሩ የተሰጣቸውን ተግባር በተማሩት መመሪያ መሰረት እንዲጠቀሙ እድል ይሰጣቸዋል (Maynes, Julien-Schultz, 2010: 65)፡፡

በትብብር መማር ጊዜ ለተማሪዎች አዲስ መረጃ የሚተዋወቅበት ጊዜ አይደለም፡፡ ይልቁኑ ይህ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች ቀድመው በሚያውቁት እውቀት ውስጥ ሆነው አዲስ የተዋወቁትን ትምህርት እንዲተገብሩ ወይም ቀድመው በሚያውቁት እውቀት መሰረት ላይ አዲሱን ትምህርት እንዲያሰላስሉ የሚደረግበት ነው፡፡ በትብብር መማር ስልት ቀድመው የሚያውቁትን ወይም የነበራቸውን አስተሳሰብ የሚያዳብሩበት ነው፡፡ በዚህ ሂደት ቀድሞ የነበራቸው ግንዛቤ የተሳሳተ ወይም

ትክክል ስለመሆኑ የሚገመገምበት እና ስለሚያውቁት እውቀት እርገጠኛ የሚሆኑበት ደረጃ ነው (Kong and Pearson 2003 :90)፡፡

Fisher and Frey (2007:39) በትብብር መማርን ተማሪዎች ሲተገብሩት ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ እርስ በእርሳቸው የሚከራከሩበትን እድል የሚያገኙበት ነው፡፡ በዚህ ትግበራ ጊዜ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ትምህርት ለማበልጸግ በየተራ በሚወከሉ ተማሪዎች ንግግር ሲያደርጉ የንግግር ተግባርን ይለማመዳሉ፡፡ አንዱ ሌላኛውን ለማስረዳት ሃሳቡን ሲገልጽ እርስ በእርሳቸው የማዳመጥ ትምህርትንም ይማራሉ፡፡ በዚህ ተግባር ውስጥ በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ ተገቢ የሆነውን መረጃ በመጠቀም ስለአንድ ርእሰ ጉዳይ ምንነት ማሰብንና ማሰላሰልንም ይለማመዳሉ፡፡

**ቁልፍ የቡድን ተግባር ክንውኖች**

1. ተማሪዎች በትብብር ወይም ቡድን መስርተው ሲማሩ እና ተግባራትን ሲተገብሩ በተወከሉ ተማሪዎች አማካኝነት በንግግር ስለርእሰ ጉዳዩ ያላቸውን ግንዛቤ ለመረዳት ስለተናገሩት ነገር ማብራሪያ እንዲሰጡ መጠየቅ ለምሳሌ፡- ምን ማለት እንደፈለጉ ሊገልጹልኝ ይችላሉ? በማለት
2. በቡድን እና በግል ተግባር ጊዜ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ስራ ወይም ተግባር ከጨረሱ በኋላ ያገኙትን ግኝት እና ውጤት በየግላቸው ያቀርባሉ፡፡ ስላቀረቡት ግኝት ማረጋገጫ ለማግኘት መፈተን ለምሳሌ፡-ያንን መረጃ ያገኙት ከየት ነው? በመጠየቅ
3. ከተግባራት በኋላ የተገኘው ውጤት ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተገቢ ዝምድና የሌለው ከሆነ እና ግኝቱን ያገኘው ከተሳሳተ ግንዛቤ ተነስቶ ከሆነ የተሳሳተ ግንዛቤን ለመቋቋም የሚያስችል ጥያቄ በማቅረብ የውጤቱን ክፍተት ማሳየት፡፡ ለምሳሌ፡- እኔ አልስማማም ምክንያቱም --------------- ብሎ ምክንያቶችን ደርድሮ በማስቀመጥ
4. የተሰጣቸው ተግባር በውይይት እንዲዳብር ከተደረገ በኋላ አከራካሪ ነጥብ ካለ የበለጠ ጉዳዩ እንዲብላላ እና ለክርክሩ መልስ እንዲሠጡ በማስገደድ እንዲናገሩ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ፡- በዚህ ጉዳይ ላይ ምሳሌ ሊሰጡኝ ይችላሉ ብሎ እንዲናገሩ ማድረግ

5. በውይይት በሚዳብሩ ሃሳቦች ውስጥ የቡድን አባላት የጋራ መግባባት ላይ ደርሰው በንግግር ሃሳብን ለመግለጽ አዳጋች ሁኔታ ካለ ወይም ተግባሩን በትክክል ተግብሮ ነገር ግን በቃል ለማቅረብ አዳጋች በሚሆንበት ጊዜ አንዱ ለሌላው ስለርእሰ ጉዳዩ መተርጎም ለምሳሌ፡- የእሱ አባባል ምናልባት --------------------ለማለት ፈልጎ ነው፡፡ በማለት

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች Fisher and Frey (2008:3) ሲገልጹ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ሊተገብሩት የሚገባና ያላቸውን ክሂል ለማዳበር እጅግ የሚጠቅም ተግባር ነው፡፡ እነዚህ ተግባራት የመናገር እና የማዳመጥ ዋና ዋና መርሆዎችን ለመተግበር አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፡፡ በተጨማሪም በዚህ ሂደት ተማሪዎች ግልጸኝነትን፣ በራስ መተማመንን፣ እራስን መግለጽን እርስ በእርስ መረዳዳትን፣ መተማመንን……ሊማሩበት ይችላሉ በማለት ይገልጻሉ፡፡

በትብብር መማር ተማሪዎች ቁልፍ ቁልፍ ስለሆኑ ጽንሰ ሃሳቦች እንዲያስቡ እድል ይሰጣል፡፡ በዚህ ሂደት ተፈጥሯዊ የሆነውን የመጠየቅ እድል ያገኛሉ፡፡ ከይዘቱ ወይም ከተግባሩ ጋርም በሚገባ ይተዋወቃሉ፡፡

ተማሪዎች ስለሚማሩት ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ እንዲዳብር ወይም እንዲጠነክር ችግሮችን የመፍታት፣ የመወያየት፣ የመግባባት፣ ከጓደኞቻቸው ጋር ስለተማሩት ትምህርት የማሰብ እድል ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በመተባበር መማር ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በተግባር የሚተገብሩበትን ከጓደኞቻቸው ጋር አብረው የሚሰሩበትን እድል ስለሚሰጣቸው ወይም ስለሚፈጥርላቸው ለተማሪዎች ላቅ ያለ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ከራሳቸው ጋር የሚያዋህዱበት ደረጃ ስለሆነ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል፡፡ እያንዳንዱ በመተባበር መማር ተግባር በቡድን መሆንን እና በጋራ መስራትን ይፈልጋል፡፡ በጋራ በሚሰሩበት ጊዜ ደግሞ እያንዳንዱ ተማሪ የግል ሃላፊነቱን መወጣት አለበት መምህሩም እያንዳንዱን ተማሪ ምን እየተገበረ እንዳለ መከታተልና ማወቅ አለበት፡፡

#### 2.3.3.2. በግል ተግብሩ

ይህ ደረጃ በእናንተ ስሩ መዋቅር ሁለተኛው ደረጃ ነው፡፡ ይህንን የመዋቅር ደረጃ አስመልክተው Maynes, Julien-Schultz, (2010: 165) በዚህ ደረጃ ላይ ተማሪዎች መምህሩ ያሳያቸውን እና ያለማመዳቸውን ተግባር በግላቸው የሚለማመዱበት ደረጃ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ተማሪዎቹ ቀድሞ በመምህሩ የተተገበሩትን በጋራ የሰሩትንና የተለማመዱትን የበለጠ እንዲያጠናክሩት እና የተማሩትን እንዲያስታውሱ እድል የሚሰጥበት ደረጃ ነው፡፡ የተማሩትንም ትምህርት በትክክል ለመረዳታቸው ወይም ለመገንዘባቸው እርግጠኛ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ተማሪዎቹ በግል የሰሩትን በሚገመግሙበት ጊዜ የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱት እና ምን ያህል እንዳወቁት መምህሩ ስለተማሪዎቹ በቂ እውቀት የሚያገኝበት ደረጃ ነው፡፡

የሞዴሉ የመጨረሻ ግብ ተማሪዎች በተለያየ ሁኔታ ላይ መረጃዎችን፣ ሃሳቦችን፣ ይዘትን፣ ክሂሎችን እና ስለቶችን በግል ስራ ላይ እንዲተገብሩ ማደረግ ነው፡፡ በዚህ ሂደት በሌሎች ሃሳብና መረጃ ላይ ጥገኛ ያልሆኑ ተማሪዎችን ለማብቃት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው ወይም በሌሎች ላይ ጥገኛ ሳይሆኑ ተግባራትን መፈጸም እና መማር አለባቸው፡፡ ባጠቃላይ በትምህርት ቤቶች በየጊዜው የሚሰናዱ ተግባር እና ትምህርታዊ ዝግጅቶች የተማሪዎችን ችሎታ የሚገነባ፣ የተጠናከረ፣ ቀጣይነት ያለው እና የተማሪዉን ሙሉ ለሙሉ የራስ የመማርያ ሃላፊነቶችን ለመቀበል የሚያበረታታ እና የሚደግፍ መሆን አለበት (Fisher and Frey 2007:66)፡፡

በግል መማር ወይም ነጻ የትምህርት አሰጣጥ የሚወሰነው ተማሪው በተግባሩ ላይ ለመሳተፍ ባለው ተነሳሽነት ነው፡፡ ብዙ ተማሪዎች በሚሰጣቸው የግል የመማር ተግባር ትኩረት የተደረገባቸው መመርያዎችን ሳይቀበሉ የተሰጣቸውን ተግባር ለማከናወን የሞክራሉ፡፡ ከዚህ ይልቅ ግን ተማሪዎቹ በሚሰሩት ስራ ውጤታማ ለመሆን ወደ ትግበራው ከመሄዳቸው በፊት መመርዎችን መቀበል አለባቸው፡፡

Levy, (2007) ተማሪዎች አዲስ ውጤት ለማስመዝገብ እውቀታቸውን እና ክህሎታቸውን ለማሳደግ ዝግጁዎች ከሆኑ ሊጠቀሙባቸው የሚገቡ ልዩ ልዩ ተግባራት አሉ፡፡ በሙከራ የተገኘ ውጤት የሚያረጋግጠው በተማሪዎች የሚወደድ

ተግባር ሁል ጊዜ በውጤታማነት ሰርተው ያጠናቅቁታል፡፡ ይህ ደረጃ እያንዳንዱ ተማሪ የተቀበለውን ተግባር በራሱ የመማር ስልት ከተሰጠው ተግባር ጋር መቆራኘት አለበት፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪው በትግበራው ያገኘውን ውጤት በአዲስ መንገድ እንዲገነዘበው ሰፊ እድል ይፈጥርለታል ይላሉ፡፡

## 2.4 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ርእስ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው የአገር ውስጥ ጥናታዊ ጽሁፎች አልተገኙም፡፡ ይሁን እንጂ ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የተሰሩ ሞዴል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ እና የማስተማርያ ዘዴ የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ትኩረት ያደረጉ እና የተጠኑ ጥናቶች አሉ፡፡ እነዚህም እንደሚከተለው ቀርበዋል

ውቤ ጣሰው (2002) “በበጌምድር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ትምህርት ክፍል የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ” በሚል ርእስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የዚህ ጥናት አብይ አላማ በ2002 ዓ.ም. በበጌምድር መማህራን ትምህርት ኮለጅ አማራኛ ትምህርት ክፍል 10+3 የስልጠና መርሐ ግብር የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ እና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡

ኤልያስ አድማሱ (1997) “በኦሮሚያ መምህራን ኮለጅ ውስጥ መሰረታዊ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ” በሚል ርዕስ ያጠኑት ጥናት ሲሆን፤ አጥኚው ጥናቱን በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ አምስት መምህራን ትምህርት ኮለጅ መርጠው ያጠኑበት አላማ መሰረታዊ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡

ደረጀ ነጋሽ (1999) “የተማሪ ተኮር አቀራረብ አተገባበር ፍተሻ በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል በ10+3 የስልጠና መርሃ ግብር” በሚል ርእስ ጥናታቸውን አቅርበዋል፡፡ የጥናታቸው ዋና አላማ ያደረጉት በ1999 ዓ.ም. በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮለጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል የ10+3 የስልጠና መርሃ ግብር የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ አተገባበርን መፈተሽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ፀሐይ ሃይለመስቀል (2003) "በስነ ልሳን ኮርሶች አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴ የክፍል ውስጥ አተገባበር በደሴና በደብረብርሃን መምህራን ትምህርት ኮለጅ" በሚል ርእስ ጥናታቸውን አቅርበዋል፡፡ የጥናቱ አላማ በስነልሳን ኮርሶች አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴ በደሴ እና በደብረ ብርሃን መምህራን ኮሌጅ እንዴት እንደሚተገበር ማጥናት ነበር፡፡

እንግዳ ዘውዴ (1992) "የ "ቶፕ ዳውን" (Top-down) የንባብ ማስተማርያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት፡- በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት" በሚል ርእስ ጥናታቸውን አቅርበዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ "የቶፕ ዳውን" የንባብ ማስተማርያ ሞዴል አማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማደበር ያለው ተግባረዊነትና ውጤታማነት ለመፈተሽ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ተተኳሪ አድርጎ ማጥናት ነበር፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የውቤ ጣሰው (2002)፣ የኤልያስ አድማሱ 91997) እና ደረጀ ነጋሽ (1999) ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር የማስተማር ዜዴዎችን በክፍል ውስጥ ከመተግበር አንጻር ከመመሳሰል በስተቀር እንዲሁም ፀሃይ ሃይለመስቀል (2003) እና እንግዳ ዘውዴ (1992) ከማስተማርያ ሞዴልና ዘዴነት ጋር ከመመሳሰል በስተቀር እኔ ከማጠናው የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ወይም (ልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር) ሞዴል ጋር በቀጥታ ግንኙነት የላቸውም፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ  ዘዴ

## 3.1 የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት የተካሄደው በሻሸመኔ ከተማ መስተዳደር ባሉና በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች ላይ ነው፡፡ የአጠናን ዘዴውም አይነታዊና መጠናዊ ምርምርን መሰረት ያደረገ ሲሆን ከጥናቱ የተገኘው ውጤትም በገለጻና በመቶኛ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ይህ የአጠናን ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ከምልከታ እና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በቁጥር ስለተቀመጡ በመቶኛ፣ በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ደግሞ በገለጻ ለመተንተን አመቺ በመሆናቸው ነው፡፡ አጥኚው ጥናቱን ሲያካሂድ የተጠቀምባቸው የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ እና የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

በዚህ ጥናት ውስጥ የመረጃ ምንጮች ሆነው ያገለገሉት በክፍል ምልከታ ወቅት ከምልከታ የተገኘ መረጀ፣ ከተማሪ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ የተገኘ መረጃ እና ከመምህራን ቃለመጠይቅ በመቅጸ ድምጽ ተቀድቶ የተገኘ መረጃ፤ ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ

### 3.3.1 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በሻሸመኔ ከተማ ከሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ በእጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ የተመረጡ ሶስት  ትምህርት ቤቶች በጥናቱ እንዲታቀፉ ተደርገዋል፡፡ የአመራረጥ ሂደቱም አስራ አራት በሻሸመኔ ከተማ የሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በቶች በሙሉ ስማቸው እጣው ወረቀት ላይ ተጽፎ ሶስት ትምህርት ቤቶች ብቻ በእጣው ተመርጠዋል፡፡ እጣው የወጣላቸው ትምህርት ቤቶችም አሌሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ መልካ ኤሳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ኤዱ መዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡

### 3.3.2 የመምህራን አመራረጥ

ጥናቱ በሚካሄድበት ሶስቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ 8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን አንድ አንድ ብቻ በመሆናቸው በጠቅላይ ናሙና ዘዴ ሁሉም ለዚህ ጥናት መረጃ እንዲሰጡ ወይም የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተመርጠዋል፡፡

### 3.3.3 የተማሪዎች አመራረጥ

በጥናቱ መረጃ የሚሰበሰብባቸው ትምህርት ቤቶች ተለይተው ከታወቁ በኋላ ቀጣዩ ተግባር የነበረው ተተኳሪ ተማሪዎችን መምረጥ ነበር፡፡ በተመረጡት ሶስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ2010 ዓ.ም. 8ኛ ክፍል ተመዝግበው ከሚማሩ አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ የሚማሩ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ውስጥ ሆን ተብሎ በአላማ ከየክፍሉ ተመርጠዋል፡፡ የተማሪ ናሙና አመራረጡ የጾታ ስብጥርን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ሆኖ በቁጥር ተመጣጣኝ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ለጥናቱ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች የተመረጡት ሆን ተብሎ በአላማ ተኮር ናሙና (Purposive sampling) ነው፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በዚህ የክፍል ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመግባት የሚዘጋጁበት ወቅት በመሆኑ ይህ የማስተማር ሞዴል ተግባራዊ ከተደረገባቸው ክፍል ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ መረጃ ይሰጣሉ ብሎ አጥኚው በመገመቱ ነው፡፡

### 3.3.4 የመማሪያ ክፍል አመራረጥ

ለዚህ ጥናት ከተመረጡት እና ተተኳሪ ከሆኑት በሻሸመኔ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ ሶስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሁለቱ ትምህርት ቤት ሶስት ሶስት ምድቦች፣ በአንዱ ትምህርት ቤት ሁለት ምድቦች ተመርጠዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በየትምህርት ቤቱ የሚገኙ አፍ ፈት የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ብዛታቸው ከሶስት እና ከሁለት ክፍል ስለማይበለጡ የክፍል ናሙና አመራረጡ ከጥናቱ አላማ አንጻር በጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል (ያለው 2006፡132)፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ጥቅም ላይ የዋሉት ሶስት ዘዴዎች ናቸው፡፡ እነዚህም የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅ እና ቃለመጠይቅ

ናቸው፡፡ የክፍል ውስጥ ምልከታው በዋና የመረጃ ምንጭነት ያገለገለ ሲሆን የጽሁፍ መጠይቁ እና ቃለ መጠይቁ ደግሞ በደጋፊ የመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡ የእያንዳንዱ መረጃ መሰብሰብያ ዘዴ አተገባበር ከዚህ በታች እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 3.4.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

በዚህ ጥናት ከተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ የሆነው ምልከታ በዋና የመራጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ምልከታ በዋና የመረጃ ምንጭ ሆኖ በአጥኚው የተመረጠበት ምክንያት መምህሩና ተማሪው የልስራ፣ እንስራ ስሩ ሞዴልን እንዴት በክፍል ውስጥ እንደሚተገብሩት አጥኚው በክፍል ውስጥ ተገኝቶ መረጃ ስለሚሰብሰብ የሚሰበሰበው መረጃ ተአማኒነት ይኖረዋል ብሎ ስላመነ ነው፡፡ ምልከታው ግቡን እንዲመታ በቅድሚያ ለመምህራኑ የምልከታውን አላማ በማስረዳት በምልከታው የተካተቱ ነጥቦች የሚተገበሩበት ጊዜ ተለይቷል፡፡ በዚህም መሰረት ስድስት ክፍለ ጊዜዎችን ለማየት ተሞክሯል፡፡

በምልከታው ሂደት በክፍል ውስጥ የመምህራኑን የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል አተገባበርን ለመገንዘብ የሚያስችል የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅጽ ተዘጋጅቶ የጥናቱ አማከሪ እንዲያዩት ተደርጓል፡፡ እያንዳንዱ ተግባር ፊት ለፊት “ተተግብሯል” እና “አልተተገበረም” የሚሉ ሳጥኖች እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ በቅጹ ውስጥ በቃለ መጠይቁና በጽሁፍ መጠይቁ ትኩረት የተሰጣቸው ተግባራት ተካተዋል፡፡ በእያንዳንዱ የትግበራ የትኩረት ነጥቦች ፊት ለፊት ትግበራው በምልከታው ወቅት ተተግብሯል ወይም አልተተገበረም በሚለው ስር ምልክት ተደርጓል፡፡

### 3.4.2 ቃለ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት የዋናው መረጃ መሰብሰቢያ ደጋፊ ተደርጎ ከተመረጠው የመረጃ መሰብሰብያ ውስጥ አንዱ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው በጥናቱ ረዕስ ተተኳሪነት ቃለ መጠይቆችን አዘጋጅቶ ለታላሚዎቹ ወይም አማርኛ ቋንቋን 8ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን ከመቅረባቸው በፊት በሙያ አጋሮቹ፣ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሁለተኛ ዲገሪ ባላቸውና ሁለተኛ ዲግሪ በመማር ላይ በሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና በመጨረሻም በአማካሪው እንዲገመገሙ እና አስተያየት እንዲሰጥባቸው አድርጓል፡፡ በአስተያየታቸውም መሰረት መሻሻያ ተደርጎባቸዋል፡፡ በመጨረሻም በተመረጡት

ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሰጡት ቀጠሮ መሰረት ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል። ቃለ መጠይቁ ሲደረግ በመቅለፀ ድምጽ የተቀዳው የመምህራን ምላሽም ተሰብስቦ ወደ ጽሁፍ ተገልብጦ ተተንትኗል።

### 3.4.3 የጽሁፍ መጠይቆች

ሌላው ለዋናው የመረጃ ምንጭ ደጋፊ ተደርጎ የተወሰደው የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ የጽሁፍመጠይቁ የሚደረገው የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴል የክፍል ውስጥ አተገባበር በምን መልኩ እየተካሄደ እንዳለ በመፈተሽ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ የቀረበው በሻሸመኔ ከተማ በሚገኙ በተመረጡ ሶስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ለሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ነው፡፡ ለተማሪዎቹ የቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ በመጀመርያው ክፍል አጠቃላይ ማንነትን በተመለከተ ስለራሳቸው መረጃ የሚሰጡበት ክፍል ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴልን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡባቸው ናቸው፡፡ በክፍል ሁለት የቀረቡት ጥያቄዎች የምርጫ ጥያቄዎች ሲሆኑ፣ እያንዳንዳቸው አምስት አማራጮች ይዘዋል፡፡ እነሱም ሁልጊዜ ይተገበራል፣ አልፎ አልፎ ይተገበራል፣ ለመወሰን እቸገራለሁ፣ አልፎ አልፎ አይተገበርም እና በጭራሽ አይተገበርም የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህ አማራጮች የተመረጡበት ምክንያት አንድ ተደጋግሞ የሚታይ ነገር ድግግሞሽን ለመለካት ጥሩ አማራጮች በመሆናቸው ነው (ያለው 2006)፡፡ አማራጮቹ ተማሪዎቹን እንዳያሻሟቸው ለማድረግ አማራጮቹ በቁጥር ከ5-1 ሆነው በምርጫው ውስጥ ተቀምጠዋል፡፡

በጽሁፍ መጠይቅ ክፍሎቹ ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች እንደ ምልከታ ቅጹ እና እንደ ቃለ መጠይቁ ሁሉ መሰረት ያደረጉት ጥናቱ ይዟቸው የተነሳውን ጥያቄዎችና በክለሳ ድርሳናት ምዕራፍ የተነሱትን ሃሳቦች ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ በተቻለ መጠን በቃለ መጠይቁና በምልከታ ቅጹ ከተዘረዘሩት ሃሳቦች ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው ጥረት ተደርጓል፡፡ በመጀመርያ መጠይቁ ለተማሪዎች እንዲሞሉት ከመሰጠቱ በፊት በአማካሪ መምህር እና በስራ አጋሮች አስተያየት እንዲሰጥባቸው

ተደርጓል፡፡ ዋናው መጠይቅ ለተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት የሙከራ ጥናት ተደርጎ በሙከራው ጥናት በተገኙ መረጃዎች መሰረት ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡

ጥናቱ በተካሄደበት በሶስቱም ትምህርት ቤት የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉ ወይም በጽሁፍ መጠይቁ የተሳተፉት ተማሪዎች 120 ናቸው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉት 120 ተማሪዎች በሙሉ የጽሁፍ መጠይቁን መልሰዋል፡፡ ተሞልተው ከተመለሱት 120 የጽሁፍ መጠይቆች ውስጥ 3ቱ ተማሪዎች የሞሉት መጠይቅ ከአንድ በላይ አማራጮች የተመረጡበት፣ አማራጮች የተዘለሉበት እና ግልጽነት የሌላቸው ሆነው በመገኘታቸው ከ117 ተማሪዎች የተሰበሰቡ የጽሁፍ መጠይቆች ብቻ በዚህ ጥናት ውስጥ ተተንትነዋል፡፡

### 3.4.4 የሙከራ ጥናት

የመጠይቁን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይቶ ለማወቅ ወይም ለመገምገም ዋናው መጠይቅ ከመደረጉ በፊት የሙከራ መጠይቅ ተዘጋጅቶ በእጣ ንሞና ዘዴ የተመረጡ ተማሪዎች የሙከራውን መጠይቅ እንዲሞሉ እና ግልጽነት የሌላቸው ጥያቄዎች ካሉ እንዲያመለክቱና ችግራቸውንም እንዲጠቁሙ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም አማርኛ ቋንቋ በማስተማር የረጅም አመት ልምድ ያላቸው መምህራን መጠይቁን እንዲያዩት እና አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት የሙከራውን መጠይቅ ከሞሉ ተማሪዎች እና መጠይቁ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ከተጠየቁ መምህራን የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ በመጠይቁ ላይ አንዳንድ ማስተካከያዎች ተደርገዋል፡፡ በዚህም መጠይቁን አስተማማኝ እና ተአማኒነት እንዲኖረው ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

## 3.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች እና በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች  አይነታዊ ገላጭ  የመረጃ መተንተኛ ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ እንዲሁም በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ደግሞ በመጠናዊ የመተንተኛ ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም ምርምሩ መረጃዎችን እያመሳከረ የሚገልጽ የሚተነትንና የሚያብራራ ገላጭ ምርምር እና በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን በቁጥር እና በመቶኛ የሚገልጽ የምርምር አይነት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ

መረጃዎችን መተንተን ያስፈለገው ለሚካሄደው ጥናት አመቺ ወይም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

በጥናቱ መረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በቅደም ተከተል በመጀመርያ በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙ መረጃዎች እና በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ በመቀጠልም ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በቅደም ተከተል ተደራጅተው ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃዎች ትንተናና የጥናቱ ውጤት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አጥኚው በተለያየ መንገድ የሰበሰባቸውን መረጃዎች ማለትም ከክፍል ውስጥ ምልከታ፣ ለመምህራን ከቀረቡ ቃለ መጠይቆችና ለተማሪዎች ከቀረቡ የጽሁፍ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች በመተንተኛው ዘዴ መንገድ በመተንተን እና በመቀመር የጥናቱ ግኝት ምን እንደሚያሳይ ወይም ምን ውጤት ላይ እንደደረሰ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሰረት ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች፣ ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የየተገኙ መረጃዎች ከአይነታዊ የምርምር አይነቶች አንዱ በሆነው ገላጭ ምርምር በሚከተለው መንገድ ተተንትኗል፡፡

## 4.1 የተጠኘ መምህራንና ተማሪዎች ዳራ

ትንተናውን ግልጽ ለማድረግ ሲባል በጥናቱ የተሳተፉ መምህራንና ተማሪዎችን ዳራ ከዚህ በታች በተለያዩ ሰንጠረዦች ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 1. የመምህራን ዳራ**

| ተ.ቁ | የሚገኙበት ተ/ቤት ስም | የመምህራን ብዛት | የት/ት ደረጃ | አብይ የሰለጠኑበት የት/ት አይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መልካ ኤሳ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት | 1 | ዲፕሎማ | አማርኛ |
| 2 | አሌሉ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት | 1 | 1ኛ ዲግሪ | ማኔጅመንት |
| 3 | ኤዱ መዳ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት | 1 | ዲፕሎማ | አማርኛ |

ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ የተጠቀሱ ሶስቱም ትምህርት በቶች የመንግስት ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በተጠቀሱት ትምህርት

ቤቶች አማርኛ ቋንቋን ከሚያስተምሩ ሶስቱ መምህራን ውስጥ ሁለቱ በአማርኛ ቋንቋ አብይ የትምህርት አይነት የሰለጠኑና በዲፕሎማ ደረጃ ያሉ መምህራን ሲሆኑ አንዷ መምህርት ግን የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት ማኔጅመንት/አስተዳደር/ ሲሆን በዲግሪ ደረጃ የሰለጠኑ ናቸው፡፡

በሰንጠረዡ ላይ በቀረበው መረጃ መሰረት ሁለቱ መምህራን በሰለጠኑበት የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት አይነት መስክ በዲፕሎማ ደረጃ ሆነው የሚያስተምሩ ሲሆን አንዷ መምህርት ግን በማኔጅመንት/በአስተዳደር/ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን አማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ባልሰለጠኑበት መስክ እያስተማሩ መሆኑን በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡

**ሰንጠረዥ 2. የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች ዳራ**

| ተ.ቁ | የሚገኙበት ት/ቤት ስም | አፍ መፍቻ ቋንቋ | ጾታ | | ድምር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወንድ | ሴት | | |
| 1 | መልካ ኤሳ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት | አማርኛ | 20 | 25 | 45 | 37.5% |
| 2 | አሌሉ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት | አማርኛ | 17 | 28 | 45 | 37.5% |
| 3 | ኤዱ መዳ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት | አማርኛ | 11 | 19 | 30 | 25% |
| | ድምር | | 48 | 72 | 120 | 100% |

ከላይ በሰንጠረዡ የቀረበው የተማሪዎች ዳራ እንደሚያስረዳው ከሶስቱም ትምህርት ቤት በጽሁፍ መጠይቁ የተሳተፉ ወንድ ተማሪዎች 48 እንዲሁም ሴት ተማሪዎች 72 በጠቅላላው 120 ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ 45ቱ ተማሪዎች በመልካ ኤሳ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ሌሎች 45 ተማሪዎች አሌሉ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ቀሪዎቹ 30 ተማሪዎች ደግሞ ከኤዱ መዳ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከመጠይቁ መረዳት እደሚቻለው መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች በሙሉ አማርኛ ቋንቋን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች አልተካተቱም፡፡ ምክንያቱም ሞዴሉን በመጠቀም የማስተማርያ መጽሃፉ የተዘጋጀው አማርኛ ቋንቋን እንደ አፍ መፍቻ ለሚማሩ ተማሪዎች ብቻ ስለሆነ ነው፡፡

## 4.2 ከክፍል ውስጥ ምልከታ እና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.2.1 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የግልና የቡድን ተግባራት

**ሰንጠረዥ 3. በእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ከቡድንና ከግል ተግባራት አተገባበር፡፡**

| ተ.ቁ | የትኩረት ነጥቦች | ተተግብሯል | አልተተገበረም |
|---|---|---|---|
| 1.1 | በቡድን በመደራጀት የቡድን ተግባራትን ተግብረዋል | 3 | --- |
| 1.2 | በግል ተግባራት ጊዜ ለሁሉም ተማሪ እኩል እድል ተሰጥቷል? | --- | 3 |
| 1.3 | ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ሰርተው አጠናቀዋል? | --- | 3 |
| 1.4 | ተማሪዎቹ የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን የመሰረቱት ቡድን የጾታ ስብጥርን ከግምት ውስጥ አስገብቷል? | 3 | |
| 1.5 | ተማሪዎች ከተግባራት በኋላ በቡድን ያገኙትን ውጤት እንዲያቀርቡ እድል ተሰጥቷል? | --- | 3 |
| 1.6 | እያንዳንዱን ተግባር መምህሩ ሞዴል ሆነው ሰርተው አሳይተዋል? | --- | 3 |
| 1.7 | መምህሩ ተግባራትን ከተማሪዎች ጋር አብረው ይሰራሉ? | 1 | 2 |

ከላይ ከሰንጠረዡ ለመረዳት እንደሚቻለው በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል በቡድን በመደራጀት የቡድን ተግባራትን ሲተገብሩ እና ለተለያየ ተግባር የመሰረቱት ቡድን የጾታ ስብጥርን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን በምልከታው ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከተግባራቱ ውስጥ በግል ትግበራ ወቅት መምህሩ ለሁሉም ተማሪ እኩል እድል ለመስጠት ሲቸገሩ፣ የግልና የቡድን ተግባር በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ሰርቶ/ተግብሮ/ ለማጠናቀቅ በግል ለእያንዳንዱ ተማሪ እደሉን ለመስጠት የጊዜ እጥረት ሲያጋጥም፣ ተማሪዎቹ የተለያየ ተግባራትን እንዲያከናውኑ በተመሰረተው ቡድን ተግባራትን ሰርተው አከናውነው ያገኙትን ውጤት ለማቅረብ እያንዳቸው እድል አለማግኘታቸውን፣ መምህራን ሁሉንም ተግባር ሞዴል ሆነው ለማሰራት ፍላጎት ሲያጡ፣ አልፎ አልፎ ተግባራትን ከተማሪዎች ጋር አብሮ ለመተግር ሲቸገሩ በምልከታው ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 4. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የግልና የቡድን ተግባራት የተማሪዎች ምላሽ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ዘወትር ይተገበራል | | አልፎአልፎ ይተገበራል | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | አልፎአልፎ አይተገበርም | | ፈጽሞ አይተገበርም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% |
| 1.1 | በቡድን በመደራጀት የቡድን ስራ ትሰራላችሁ | 35 | 29.9% | 66 | 56.9% | 4 | 3.4% | 4 | 3.4% | 8 | 6.8% |
| 1.2 | የግል ተግባራትን ስትሰሩ ሁሉም እኩል እድል ይሰጠዋል | 66 | 56.4% | 18 | 15.4% | 13 | 11.1% | 8 | 6.8% | 12 | 10.3% |
| 1.3 | በክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን በቂ ጊዜ ይሰጣችኋል | 25 | 21.4% | 22 | 18.8% | 19 | 16.2% | 31 | 26.5% | 20 | 17.7% |
| 1.4 | የተለያዩ ተግባራትን በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ሰርታችሁ ታጠናቅቃላችሁ | 21 | 17.9% | 15 | 12.8% | 8 | 6.8% | 40 | 34.2% | 33 | 28.2% |
| 1.5 | የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ቡድን ስትመሰርቱ የጾታ ስብጥርን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው | 66 | 56.4% | 15 | 12.8% | 9 | 7.7% | 4 | 3.4% | 23 | 19.7% |
| 1.6 | የግል ወይም የቡድን ተግባራትን ካጠናቀቃችሁ በኋላ የገኛችሁትን ግኝት እንድታቀርቡ እድል ይሰጣችኋል | 20 | 17.7% | 14 | 12% | 26 | 22.2% | 33 | 28.2% | 24 | 20.5% |
| 1.7 | እያንዳንዱን ተግባር መምህሩ ሞዴል ሆነው ሰርተው ያሳያሉ | 51 | 43.6% | 30 | 25.6% | 15 | 12.8% | 7 | 6.0% | 14 | 12.0% |
| 1.8 | መምህሩ ተግባራትን ሰርተው ካሳዩ በኋላ ከተማሪዎች ጋር በጋራ ይሰራሉ | 73 | 62.4% | 24 | 20.5% | 2 | 1.7% | 7 | 6.0% | 11 | 9.4% |

ከላይ ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎቹ በሰጡት መረጃ መሰረት ለ1ኛው ጥያቄ (29.9%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (56.4%)ቱ ደግሞ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (86.3%)ቱ የሰጡት ምላሽ ሁልጊዜና አልፎ አልፎ በቡድን በመደራጀት የቡድን ስራዎችን እንደሚሰሩ የተገኘው ውጤት ያሳያል። በመሆኑም በምልከታ እና በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ውጤት በተመሳሳይ በቡድን በመደራጀት የቡድን ስራዎችን እንደሚሰሩ ያሳያል። ሰንጠረዥ 4 ጥያቄ ሁለት ላይ  የግል ተግባራትን ሲሰሩ ለሁሉም ተማሪ እኩል እድል መሰጠት አለመሰጠቱን አስመልክቶ (56.4%)ቱ ዘወትር ይተገብራሉ እና (15.4%)ቱ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (71.8%)ቱ ዘወትር ይተገበራልና እና አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት የግል ተግባርን ለመተግበር እኩል እድል እነደሚሰጣቸው የሰጡት ምላሽ ያስረዳል። በክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን ለተገባር ወይም ለማከናወን በቂ ጊዜ ይሰጣችኋል ለሚለው ሶስተኛው ጥያቄ (26.5%)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም (17.7%)ቱ ፈጽሞ አይተገበርም እንዲሁም (16.2%) ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት መልሰዋል።በዚሁ መሰረት (44.2%)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም እና ፈጽሞ አይተገበርም በማለት ተግባራትን ለማከናወን በቂ ጊዜ እንደማይሰጣቸው ከምላሻቸው ለመረዳት ተችሏል።

በጥያቄ 5 ላይ ተግባራትን ለማከናወን የሚመሰርቱት ቡድን የጾታ ስብጥርን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው ለሚለው ጥያቄ (56.4%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (12.8%)ቱ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (69.2%)ቱ በክፍል ውስጥ የሚመሰርቱት ቡድን የጾታ ስብጥርን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል። በተራ ቁጥር ሰባት ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ (43.6%)ቱ ዘወተውር ይተገበራል እና (25.6%)ቱ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (69.2%)ቱ በክፍል ውስጥ የሚተገብሩትን ተግባር መምህሩ ሞዴል ሆነው ሰርተው እንደሚያሳዩአቸው የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል።በተራ ቁጥር ስምንት ላይ ለቀረበው ጥያቄ (62.4%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (20.5%) አልፎ ልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (82.9%)ቱ መምህሩ የተለያዩ ተግባራትን ከሰሩ በኋላ ቀጥለው ከተማሪዎች ጋር በጋራ እንደሚሰሩ የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል።

በተራ ቁትር አራት ላይ ለቀረበው ጥያቄ (28.2 %)ቱ ፈጽሞ አይተገበርም እና (34.2 %)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም በማለት በድምሩ (62.4%)ቱ የግልና የቡድን

ተግባራትን በተሠጠው ጊዜ ውስጥ ሰርተው እንደማያጠናቅቁ በሰጡት ምላሽ አረጋግጠዋል፡፡ በተራ ቁጥር ስድስት ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ (20.5% )ቱ ፈጽሞ አይተገበርም እና (28.2 %)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም በማለት በድምሩ (48.7% )ቱ የግል ወይም የቡድን ተግባራትን ካጠናቀቁ በኂላ ያገኙትን ግኝት እንዲያቀርቡ እድል እንደማይሰጣቸው የሰጡት ምላሽ አረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከምልከታ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው በቡድን በመደራጀት የቡድን ተግባራትን እንደሚተገበሩና የመሰረቱት ቡድን የጾታ ስብጥርን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆኑን ነው፡፡ በአንጻሩ የተለያዩ ተግባራትን ለመተግበር ለሁሉም ተማሪ እኩል እድል እንደማይሰጣቸው እና የተለያዩ ተግባራትን በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ተግብረው እንደማያጠናቅቁ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡ ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እነዚህኑ እውነቶች የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 4.2.2 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የጾታ ተኮር አካቶትምህርት እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አተገባበር

**ሰንጠረዥ 5. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ጾታ ተኮር፣ አካቶ ትምህርትና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አተገባበር በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ | የትኩረት ነጥብ | ተተግብሯል | አልተተገበረም |
|---|---|---|---|
| 2.1 | ሴትና ወንድ ተማሪዎች ከአድሎ በጸዳ መልኩ በእኩል ተስተናግደዋል | 3 | ---- |
| 2.2 | አካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ይደረገላቸዋል | የለም | የለም |
| 2.3 | ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸዋል | 3 | ---- |

ከላይ በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው በክፍል ምልከታ ወቅት ሴትና ወንድ ተማሪዎች ከአድሎ በጸዳ መልኩ በእኩል ሲስተናገዱ ለማየት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ተገቢ የሆነ ድጋፍ ሲደረግላቸው በምልከታው ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ግን ጥናቱ በተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚማሩ ተማሪዎች መካከል ምንም አይነት የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች እንደሌሉ በምልከታው ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 6. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞደል የጾታ ተኮር፣ አካቶ ትምህርትና ልዩ ፍላጎት ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች ምላሽ፡፡**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ዘወትር ይተገበራል | | አልፎ አልፎ ይተገበራል | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | አልፎ አልፎ አይተገበርም | | ፈጽሞ አይተገበርም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% |
| 2.1 | መምህሩ በክፍል ውስጥ በልዩ ልዩ ተግባራት ላይ ሴትና ወንድ ተማሪዎችን ከአድሎ በጸዳ መልኩ በእኩል የሳትፋሉ | 94 | 80.3 | 7 | 6.0 | 7 | 6.0 | 4 | 3.4 | 5 | 4.3 |
| 2.2 | የመማር ተግባርን ስታከናውኑ ያለ ጾታ አድሎ መምህሩ በእኩል አይን ያዩኒችኋል | 87 | 74.4 | 10 | 8.5 | 6 | 5.1 | 5 | 4.3 | 9 | 7.7 |
| 2.3 | አካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ይደረግላችኋል | 21 | 17.9 | 10 | 8.5 | 60 | 51.3 | 15 | 12.8 | 11 | 8.5 |
| 2.4 | ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍ ይደረገላቸዋል | 41 | 25.0 | 26 | 22.2 | 23 | 29.7 | 8 | 6.8 | 19 | 16.2 |

በሰንጠረዥ 6 በተራ ቁጥር 2.1 ላይ ለተነሳው ጥያቄ (80.3%) የሚሆኑት ዘወትር ይተገበራል እና (6.0%) የሚሆኑት ደግሞ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (86.3%) የሚሆኑት በክፍል ውስጥ በልዩ ለዩ ተግባራት ላይ ሴትና ወንድ ተማሪዎች ከአድሎ በጸዳ መልኩ በእኩል እንደሚሳተፉ ወይም በሌላ አነጋገር የጾታ እኩልነት በክፍል ውስጥ መረጋገጡን ከሰጡት ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በጥያቄ ቁጥር 2.2 ላይ (74.4%) የሚሆኑት ዘወትር ይተገበራል እና (8.5%) የሚሆኑት ደግሞ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (82.9%) የሚሆኑት መምህሩ ሴትና ወንድ ተመሪዎችን በእኩል አይን እንደሚያዩና በእኩልነት እንደሚያሳትፏቸው ከሰጡት ምልሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡በተራ ቁጥር 2.4 ላይ (25.0%) የሚሆኑት ዘወትር ይተገበራል ሲሉ (22.2%) የሚሆኑት ደግሞ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (47.2%) የሚሆኑት ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢ የሆነ ድጋፍ እንደሚሰጣቸው የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል፡፡በዚሁ ጥያቄ ውስጥ (29.7%) የሚሆኑት ደግሞ በዚህ ጥያቄ ላይ የሚሰጡትን መልስ ለመወሰን እንደሚቸገሩ ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በተራ ቁጥር 2.3 ላይ (51.3%) የሚሆኑት ተማሪዎች የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል ወይም ይሰጣቸዋል ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ሲመልሱ (12.8%) የሚሆኑት አልፎ አልፎ አይተገበርም (8.5%) የሚሆኑት ፈጽሞ አይተገበርም በማለት በድምሩ (21.3%) አልፎ አልፎና ፈጽሞ እንደመይተገበር ገልጸዋል፡፡ በአጠቃለይ በምልከታውና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሰረት ጥናቱ በተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ባለመኖራቸው (51.3%) የሚሆኑ ተማሪዎች ይህንን ጥያቄ አስመልክቶ መልስ ለመስጠት እንደሚቸገሩ ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከክፍል ምልከታው  እና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ የሚያመለክተው ሴት ተማሪዎች ከአድሎ በጸዳ መልኩ በተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራት ከወንዶች ጋር እኩል እንደሚሳተፉ እና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ሲሆን የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች በክፍል ምልከታ ወቅት በክፍል ውስጥ አጥኚውን አላጋጠሙም ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃም አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ለመወሰን እንደሚቸገሩ በሰጡት መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 4.2.3 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የማንበብ ተግባር

**ሰንጠረዥ 7. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናነተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የማንበብ ተግባር የክፍል ምልከታ መረጃ።**

| ተ.ቁ | የትኩረት ነጥቦች | ተተግብሯል | አልተተገበረም |
|---|---|---|---|
| 3.1 | የማንበብ ተግባራትን ስትተገብሩ የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ መተንበይ … በአግባቡ ይተገበራል | 3 | ---- |
| 3.2 | የማንበብ ተግባርን መምህሩ ሞዴል ሆነው ያሳያሉ | 3 | ---- |
| 3.3 | መምህሩ እያንዳንዱ ተማሪ አንብቦ መረዳቱን በአግባቡ ይከታተላሉ | 3 | ---- |
| 3.4 | እያንዳንዱ ተማሪ አቀላጥፎ የማንበብ እድል ይሰጠዋል | ---- | 3 |
| 3.5 | መምህሩ ተማሪዎች የማንበብ እክል ሲገጥማቸው በግል ይረዷቸዋል | 3 | ---- |
| 3.6 | ለፈጣን አንባቢዎች የማንበብ ተግባርን ካጠናቀቁ በኋላ ተጨማሪ የንባብ መጻሃፍ በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ እድል ይሰጣቸዋል | ---- | 3 |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደሚታየው የንባብ ተግባርን አስመልክቶ የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ፣ መተንበይ፣ በንባብ ተግባር ጊዜ መምህሩ ሞዴል ሆኖ ማሳየት እና ተማሪዎች በንባብ ጊዜ እክል ሲገጥማቸው በግል መርዳት የሚሉት በአግባቡ በክፍል ውስጥ ሲተገበሩ በምልከታው ወቀት ለማረጋገጥ ተችሏል።

በሌላ መልኩ ደግሞ እንዳንዱ ተማሪ አንብቦ መረዳቱን ለመከታተል እንዲሁም ለእያንዳንዱ ተማሪ አቀላጥፎ የማንበብ እድል ለመስጠት የጊዜ እጥረት ሲገጥማቸው በምልከታው ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ ለፈጣን አንባቢዎች

የማንበብ ተግባርን ካጠናቀቁ በኋላ ተጨማሪ የንባብ መጸሃፍ እንዲያነቡ እንደማይሰጣቸው በምልከታው ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 8. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የማንበብ ተግባር የተማሪዎች ምላሽ፡፡**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ዘወትር ይተገበራል | | አልፎ አልፎ ይተገበራል | | ለመስን እቸገራለሁ | | አልፎ አልፎ አይተገበርም | | ፈጽሞ አይተገበረም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% |
| 3.1 | የማንበብ ተግባርን ስትተገብሩ የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ፣ መተንበይ … በአግባቡ ትተገብራላችሁ | 60 | 51.3 | 31 | 26.5 | 11 | 9.4 | 10 | 8.5 | 55 | 4.3 |
| 3.2 | አቀላጥፎ ማንበብን መምህሩ ሞዴል በመሆን በተግባር አንብበው ያሳያሉ | 82 | 70.1 | 15 | 12.8 | 4 | 3.4 | 5 | 4.3 | 11 | 9.4 |
| 3.3 | በማንበብ ጊዜ የማንበብ አላባውያንን በሚገባ ትተገብራላችሁ | 51 | 43.6 | 34 | 29.0 | 17 | 14.5 | 4 | 3.4 | 11 | 9.4 |
| 3.4 | መምህሩ በማንበብ ጊዜ እያንዳንዱ ተማሪ አንብቦ መረዳቱን ይከታተላሉ | 10 | 8.5 | 22 | 18.8 | 7 | 6.0 | 50 | 42.7 | 28 | 23.9 |
| 3.5 | እያንዳንዱ ተማሪ አቀላጥፎ የማንበብ እድል ይሰጠዋል | 16 | 13.7 | 14 | 12.0 | 12 | 10.3 | 65 | 55.6 | 10 | 8.5 |
| 3.6 | በማንበብ ጊዜ እክል (ችግር) ሲገጥማችሁ መምህሩ እያንዳንዳችሁን በግል ይረዷችኋል | 46 | 39.3 | 21 | 17.9 | 11 | 9.4 | 8 | 6.8 | 31 | 26.5 |
| 3.7 | የተማሪዎችን የማንበብ ፍጥነት ለመገምገም መምህሩ ሰአት ይዘው ያስነብባሉ | 17 | 14.5 | 23 | 19.7 | 10 | 8.5 | 6 | 5.1 | 61 | 52.1 |
| 3.8 | ለፈጣን አንባቢዎች የማንበብ ተግባርን ካጠናቀቁ በኋላ ተጨማሪ የንባብ መጽሃፍ ተዘጋጅቶ እንዲያነቡ ይሰጣቸዋል | 14 | 12.0 | 18 | 15.4 | 10 | 8.5 | 2 | 1.7 | 73 | 62.4 |
| 3.9 | ከክፍል ውጪ በግል የንባብ ችሎታችሁን እንድታዳብሩ ምክርና ድጋፍ ይሰጣችኋል | 41 | 35.0 | 24 | 20.5 | 6 | 5.1 | 9 | 7.7 | 37 | 31.6 |

በተሰጠው መረጃ መሰረት ለትያቄ 3.1 (51.3%)ቱ ዘወትር ይተገበራልና እና (26.5%)ቱ ደግሞ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (77.8%)ቱ የማንበብ ተግባራትን ሲተገብሩ የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ፣ መተንበይ … በአግባቡ እንደሚተገብሩ የሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡በጥያቄ 3.2 (70.1%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (12.8%)ቱ አልፎ አለፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (82.9%)ቱ አቀላጥፎ ማንበብን መምህሩ ሞዴል በመሆን በተግባር አንብበው ለተማሪዎች እንደሚያሳዩ ወይም እንደሚተገብሩ የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል፡፡ለጥያቄ 3.3 (43.6%)ቱ ዘወትር ይተገበራል (29.0%)ቱ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (72.6%)ቱ በማንበብ ጊዜ የማንበብ አላባውያንን በሚገባ እንደሚተገብሩ የተገኘው ውጤት ያሳያል፡፡ ጥያቄ 3.6ን አስመልክቶ (39.3%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (17.9%)ቱ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (57.2%)ቱ የሚሆኑቱ በማንበብ ጊዜ እክል (ችግር) ሢገጥማቸው መምህሩ በግል እንደሚረዷቸው የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል፡፡ጥያቄ ቁጥር 3.9 ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ (35.0%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (20.5%)ቱ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (55.5%)ቱ ከክፍል ውጪ የማንበብ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ምክርና ድጋፍ እንደሚሰጣቸው ከሰቱት ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በጥያቄ 3.4 ላይ ለቀረበው ጥያቄ (42.7%)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም እና (23.9%)ቱ ደግሞ ፈጽሞ አይተገበርም በማለት በድምሩ (66.6%)ቱ በንባብ ጊዜ መምህሩ እያንዳንዱ ተማሪ አንብቦ መረዳቱን ለመከታተል (ሙሉ በሙሉ ሁሉንም ተማሪ ለማዳረስ) እንዳልቻሉ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡ ጥያቄ 3.5 ለይ (55.6%)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም እና (8.5%)ቱ ፈጽሞ አይተገበርም በማለት በድምሩ(64.1%)ቱ ሁሉም ተማሪ አቀላጥፎ የማንበብ እድል እንደማይሰጣቸው(እድሉ ለሁሉም ተማሪ አለመዳረሱን) የሰጡት መረጃ ይገልጻል፡፡ በጥያቄ 3.7 ላይ (52.1%)ቱ ፈጽሞ አይተገበርም እና (5.1%)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም በማለት በድምሩ (57.2%)ቱ የንባብ ፍጥነታቸውን ለመገምገም መምህራቸው ሰአት ይዘው እንደማያስነብቧቸው ከሰጡት ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለጥያቄ 3.8 (1.7%)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም እና (62.4%)ቱ ፈጽሞ አይተገበርም በማለት በድምሩ (64.1%)ቱ ለፈጣን አንባቢዎች በክፍል ውስጥ የተሰጣቸውን የማንበብ ተግባር ካጠናቀቁ በኋላ ተጨማሪ የንባባ

መጻሃፍ መምህሩ አዘጋጅተው እንደማይሰጧቸው ከተሰጠው ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 4.2.4 በእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የመጻፍ ተግባር

**ሰንጠረዥ 9. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የመጻፍ ተግባር የክፍል ምልከታ መረጃ**

| ተ.ቁ | የትኩረት ነጥቦች | ተተግብሯል | አልተተገበረም |
|---|---|---|---|
| 4.1 | የቅድመ መጻፍ ተግባራትን በየደረጃው አከናውነዋል | 3 | ---- |
| 4.2 | በጽህፈት ተግባር ጊዜ ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው በግል እንዲጽፉ እድል ተሰጥቷቸዋል | 3 | ---- |
| 4.3 | ተማሪዎች በጽህፈት ጊዜ ችግር ሲገጥማቸው መምህሩ ረድተዋቸዋል | 3 | ---- |

ሰንጠረዡ ላይ ከተቀመጠው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው በሞዴሉ የመጻፍ ተግባርን አስመልክቶ ቅድመ መጻፍ ተግባራትን በየደረጃው እንደሚያከናውኑ፣ ራሳቸውን ችለው በግል እንዲጽፉ አድል እነደሚሰጣቸው፣ በጥህፈት ተግባር ጊዜ እክል ወይም ችግር ሲገጥማቸው መምህሩ እንደሚረዷቸውና ከትግበራም በኋላ ግብረመልስ እንደሚሰጧቸው በክፍል ምልከታ ወቅት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 10. በእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የመጻፍ ተግባርን አስመልክቶ ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ፡፡**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ዘወትር ይተገበራል | | አልፎ አልፎ ይተገበራል | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | አልፎ አልፎ አይተገበርም | | ፈጽሞ አይተገበርም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% |
| 4.1 | የቅድመ መጻፍ ተገባራትን በየደረጃው ታከናውናላችሁ | 45 | 38.5 | 34 | 29.1 | 13 | 11.1 | 10 | 8.5 | 15 | 12.8 |
| 4.2 | በጽህፈት ተግባር ጊዜ ራሳችሁን ችላችሁ በግል እንድትጽፉ እድል ይሰጣችኋል | 56 | 47.9 | 26 | 22.2 | 13 | 11.1 | 6 | 5.1 | 16 | 13.7 |
| 4.3 | በጽህፈት ተግባር ጊዜ እክል ወይም ችግር ሲገጥማችሁ መምህሩ ይረዷችኋል | 62 | 53.0 | 19 | 16.2 | 13 | 11.1 | 3 | 2.6 | 20 | 17.1 |
| 4.4 | የጽህፈት ተግባር ካከናወናችሁ በኋላ ግብረ መልስ ይሰጣችኋል | 57 | 48.7 | 17 | 14.5 | 10 | 8.5 | 11 | 9.4 | 22 | 18.8 |

በሰንጠረዥ 10. እንደሚታየው በተራ ቁጥር 4.1 ላይ ለተነሳው ጥያቄ በጽሁፍ መጠይቁ ከተካተቱ 117 ተማሪዎች ውስጥ (38.5%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (29.1%)ቱ ደግሞ አልፎ አልፎ የተገበራል በማለት በድምሩ (67.6%) የሚሆኑት ቅድመ መጻፍ ተግባራትን በየደረጃው እንደሚያከናውኑ ከሰጡት መረጃ ማወቅ ተችሏል፡፡ በተራቁጥር 4.2 ላይ ለተነሳው ጥያቄ (47.9%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (22.2%)ቱ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (70.1%)ቱ በጽህፈት ተግባር ጊዜ እራሳቸው ችለው በግል እንዲጽፉ እድል እንደሚሰጣቸው ገልጸዋል፡፡ በተራ ቁጥር 4.3 ላይ ለተነሳው ጥያቄ (53.0%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (16.2%)ቱ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (69.2%)ቱ በጽህፈት ተግባር ጊዜ እክል ወይም ችግር ሲገጥማቸው መምህሩ እንደሚረዷቸው የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል፡፡ ለጥያቄ 4.4 ደግሞ (48.7%)ቱ ዘወትር ይተገበራል ሲሉ (14.5%)ቱ ደግሞ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (63.2%)ቱ የጽህፈት ተግባርን በክፍል ውስጥ ካከናወኑ በኋላ ግብራ መልስ እነደሚሰጣቸው በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### 4.2.5 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የማዳመጥ ተግባር

**ሰንጠረዥ 11. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የማዳመጥ ተግባር የክፍል ምልከታ መረጃ፡፡**

| ተ.ቁ | የትኩረት ነጥቦች | ተተግብሯል | አልተተገበረም |
|---|---|---|---|
| 5.1 | በማዳመጥ ተግባር ጊዜ ለተማሪዎች ምዘና ወይም ፈተና ይሰጣቸዋል | ---- | 3 |
| 5.2 | ተማሪዎች የማዳመጥን ተግባር ካከናወኑ በኋላ ድጋፍና ማበልጸግ ይደረግላቸዋል | ---- | 3 |
| 5.3 | አዳምጦ የመረዳት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል | ---- | 3 |

በሰንጠረዥ 11. ላይ በሞድሉ የማዳመጥ ተግባርን አስመልክቶ በተደረገ የክፍል ውስጥ ምልከታ በማዳመጥ ተግባር ጊዜ ማዳመጥን ለመመዘን ፈተና እንደማይሰጣቸው፣ የማዳመጥ ተግባርን ከተገበሩ በኂላ ድጋፍና ማበልጸግ እንደማይደረግላቸው፣ አዳምጠው ለመረዳት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍና ማበልጸግ እንደማይደረግላቸው በምልከታው ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 12. በእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የማዳመጥ ተግባር የተማሪዎች ምላሽ፡፡**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ዘወትር ይተገበራል | | አልፎ አልፎ ይተገበራል | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | አልፎ አልፎ አይተገበር ም | | ፈጽሞ አይተገበርም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛ ት | በ% | ብ ዛ ት | በ% | ብ ዛ ት | በ% | ብዛ ት | በ% | ብዛ ት | በ% |
| 5.1 | በማዳመጥ ተግባር ጊዜ ምዘና ወይም ፈተና ይሰጣችኂል | 19 | 16.2 | 21 | 17.9 | 11 | 9.4 | 27 | 23.1 | 39 | 33.3 |
| 5.2 | የማዳመጥን ተግባር ካከናወናችሁ በኂላ ድጋፍና ማበልጸግ ይደረግላችኂል | 24 | 20.5 | 18 | 15.4 | 18 | 15.4 | 28 | 23.9 | 29 | 24.8 |
| 5.3 | አዳምጠው የመረዳት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ ይደረግላቸዋል | 18 | 15.4 | 18 | 15.4 | 23 | 19.7 | 22 | 18.8 | 36 | 30.8 |

በሰንጠረዥ 12. የማዳመጥ ተግባርን አስመልክቶ በተራ ቁጥር 5.1 ላይ (33.3%)ቱ ፈጽሞ አይተገበረም እና (23.1%)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም በማለት በድምሩ (56.4%)ቱ በማዳመጥ ተግባር ጊዜ ምዘና ወይም ፈተና እንደማይሰጣቸው የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል፡፡ በተራ ቁትር 5.2 (24.8%)ቱ ፈጽሞ አይተገበርም እና (23.9%)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም በማለት በድምሩ (48.7%)ቱ የማዳመጥን ተግባር ካከናወኑ

በኋላ ድጋፍና ማበልጸግ እንደማደረግላቸው እና (15.4%)ቱ ደግሞ ለመወሰን እነደሚቸገሩ የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል፡፡ በተራ ቁጥር 5.3 ላይ (30.8%)ቱ ፈጽሞ አይተገበርም እና (18.8%)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም በማለት በድምሩ (49.6%)ቱ አዳምጦ የመረዳት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ እንደማይደረገላቸው የሰጡት መረጃ ያረጋግጣል፡፡

**4.2.6 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የንግግር ተግባር**

**ሰንጠረዥ 13. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የንግግር ተግባር የክፍል ምልከታ መረጃ፡፡**

| ተ.ቁ | የትኩረት ነጥቦች | ተተግብሯል | አልተተገበረም |
|---|---|---|---|
| 6.1 | ተማሪዎች በግልና በንኡስ ቡድን ንግግር እንድታደርጉ እድል ይሰጣቸዋል | ---- | 3 |
| 6.2 | ተማሪዎች በንግግር ጊዜ ለሚገጥማቸው ችግር ወይም እክል ማስተካከያ ተሰጥቷቸዋል | 3 | ---- |

ከላይ ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በክፍል ምልከታ ወቅት እያንዳንዱ ተማሪ በግል ንግግር እንዲያደርግ እድል ይሰጠዋል የሚለውን በተመለከተ ንግግር እነዲያደረጉ እድሉ ለሁሉም ተማሪዎች እንደማይሰጥ ከምልከታው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በንግግር ወቅት ተማሪዎች ችግር ወይም እክል ሲገጥማቸው ድጋፍ እንደሚደረገላቸው በምለከታው ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 14. በእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣ አናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል የንግግር ተግባር የተማሪዎች ምላሽ፡፡**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ዘወትር ይተገበራል | | አልፎ አልፎ ይተገበራል | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | አልፎ አልፎ አይተገበርም | | ፈጽሞ አይተገበርም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% |
| 6.1 | በግልና በንኡስ ቡድን ንግግር አንድታደርጉ እድል ይሰጣችኋል | 17 | 14.5 | 24 | 20.5 | 10 | 8.5 | 42 | 35.9 | 24 | 20.5 |
| 6.2 | በየምእራፉ ባሉ የንግግር ተግባራት ላይ እንድትናገሩ ለእያንዳንዳችሁ እድል ይሰጣችኋል | 20 | 17.1 | 18 | 15.4 | 7 | 6.0 | 36 | 30.8 | 36 | 30.8 |
| 6.3 | በንግግር ጊዜ ለሚገጥማችሁ ችግር ማስተካከያ ይሰጣችኋል | 60 | 51.3 | 31 | 26.5 | 6 | 5.1 | 4 | 3.4 | 16 | 13.7 |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው ለጥያቄ 6.1 (35.9%)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም እና (20.5%)ቱ ፈጽሞ አይተገበርም በማለት በድምሩ (56.4%)ቱ እያንዳንዱ ተማሪ በግል ንግግር እነዲያደርግ እድሉ ለሁሉም ተማሪ እንደማይሰጣቸው የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል፡፡ በጥያቄ ቁጥር 6.2 ላይ (30.8%)ቱ አልፎ አልፎ አይተገበርም እና (30.8%)ቱ ፈጽሞ አይተገበርም በማለት በድምሩ (61.6%) ቱበየምራፉ ባሉ የንግግር ተግባራት ላይ እንዲናገሩ ለእያንዳንዱ ተማሪ እድል እንደማይሰጠው(እድሉ ሁሉንም ተማሪ እንደማዳርስ የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል፡፡

በጥያቄ ቁጥር 6.3 ላይ (51.3%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (26.5%)ቱ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (77.8%) በንግግር ጊዜ ለሚገጥማቸው ችግር ማስተካከያ(እርምት) እንደሚሰጣቸው በሰጡት ምላሽ አረጋግጠዋል፡፡

### 4.2.7 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ግብረ መልስ፣ ድጋፍና ማበልጸግ

**ሰንጠረዥ 15. በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ግብረመልስ፣ ድጋፍ እና ማበልጸግን በተመለከተ በተመለከተ የክፍል ምልከታ መረጃ**

| ተ.ቁ | የትኩረት ነጥቦች | ተተግብሯል | አልተተገበረም |
|---|---|---|---|
| 7.1 | ለተማሪዎች የመማር ፍላጎታቸውን የሚያነሳሳ እና እንዲጨምር የሚያደርግ ግብረ መልስና ድጋፍ ይሰጣቸዋል | 3 | |
| 7.2 | ለተማሪዎች ግብረ መልስ ሲሰጣቸው ትክክል ወይም ሥህተት መሆኑ ይነገራቸዋል | 2 | 1 |
| 7.3 | ለተማሪዎች ወቅቱን የጠበቀ ግብረ መልስ ተሰጥቷቸዋል | 3 | |
| 7.4 | ለተማሪዎች ምዘና በአግባቡ እና በተገቢው ጊዜ ተሰጥቷቸዋል | 2 | 1 |

ከላይ ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በክፍል ውስጥ ምልከታ በተደረገ ጊዜ መምህራኖቹ ለተማሪዎች የመማር ፍላጎታቸውን የሚያነሳሳና እንዲጨምር የሚያደረግ ግብረ መልስና ድጋፍ ሲሰጧቸው እና ወቅቱን ጠብቀው(ተግባሩ በሚከናወን ጊዜ) ግብረ መልስ ሲሰጧቸው እደዚሁም ሲሰጡ ታይቷል፡፡ ነገር ግን ለተማሪዎች ግብረ መልስ ሲሰጧቸው ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን በመንገር ላይ ሁለቱ ትምህርት ቤቶች ላይ በአግባቡ ሲተገበር በአንድ ትምህርት ቤት ላይ ግን ግብረ መልስ ሲሰጣቸው ትክክል ወይም ስህተት መሆኑ ተነግሯቸው ሳይሆን ከተግባራቱ በኋላ ጠቅለል ተደርጎ እንደሚነገራቸው፣ ምዘናን በተመለከተ እንዲሁ በሁለት ትምህርት ቤቶች በአግባቡ ወቅቱን የጠበቀ ምዘና ሲሰጥ በምልከታው ወቅት ለማረጋጥ ተችሏል፡፡

ሰንጠረዥ 16. በእኔ ልስራ፣አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ግብረ መልስ፣ ድጋፍና እና ማበልጸግን በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ፡፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ዘወትር ይተገበራል | | አልፎ አልፎ ይተገበራል | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | አልፎ አልፎ አይተገበርም | | ፈጽሞ አይተገበርም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% |
| 7.1 | የመማር ፍላጎታችሁን የሚያነሳሳ እና እንዲጨምር የሚያደርግ በቂና ተገቢ የሆነ ግብረ መልስ እና ድጋፍ ሰጣችኋል | 45 | 38.5 | 29 | 24.8 | 14 | 12.0 | 8 | 6.8 | 21 | 17.9 |
| 7.2 | ላከናወናችሁት ተግባር ግብረ መልስ የሚሰጣችሁ ትክክል ወይም ስህተት መሆኑ ተነግሯችሁ ነው | 54 | 46.2 | 22 | 18.8 | 11 | 9.4 | 7 | 6.0 | 23 | 19.7 |
| 7.3 | የሚሰጣችሁ ግብረ መልስ ወቅቱን የጠበቀና ወዲያውኑ ነው | 57 | 48.7 | 20 | 17.1 | 16 | 13.7 | 6 | 5.1 | 18 | 15.4 |
| | ምዘና ወይም ፈተና በአግባቡና በተገቢው ጊዜ ይሰጣችኋል | 75 | 64.1 | 16 | 15.7 | 8 | 6.8 | 7 | 6.0 | 11 | 9.4 |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው ለጥያቄ 7.1 (38.5%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (24.8%)ቱ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (63.3%)ቱ የመማር ፍላጎታቸውን የሚያነሳሳና እንዲጨምር የሚያደርግ በቂና ተገቢ የሆነ ግብረ መልስና ድጋፍ እንደሚደረግላቸው(እንደሚሰጣቸው) የሰጡት መረጃ ያረጋግጣል፡፡ ለቅያቄ 7.2 (46.2%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (18.8%)ቱ አልፎ አልፎ የተገበራል በማለት

በድምሩ (65.0%)ቱ ላከናወኑት ተግባር ግብረ መልስ የሚሰጣቸው ትክክል ወይም ስህተት መሆኑ ተነግሯቸው እንደሆነ የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል፡፡ ለጥያቄ 7.3 (48.7%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (17.1%)ቱ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (65.8%)ቱ የሚሰጣቸው መልስ ወቅቱን የጠበቀና ወዲያውኑ እንደሆነ የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል፡፡ ለጥያቄ 7.4 (64.1%)ቱ ዘወትር ይተገበራል እና (13.7%)ቱ አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት በድምሩ (77.8%)ቱ ምዘና ወይም ፈተና በአግባቡና በተገቢው ጊዜ እንደሚሰጣቸው በሰጡት ምላሽ አረጋግጠዋል፡፡

## 4.3 ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ምራፍ መጀመርያ ላይ እነደተገለጸው ለዚህ ጥናት ሌላው አጋዥ መረጃ መሰብሰብያ ዘዴ ቃለመጠይቅ ነው፡፡ ቃለመጠይቁ ለጥናቱ በተመረጡ በሶስቱ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋን ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ ሲሆን በእኔልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ(ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የግልና የቡድን ተግባራትን፣ የጾታ ተኮር፣ አካቶ ትምህርትና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አተገባበር፣ የማንበብ ተግባር፣ የመጻፍ ተግባር፣ የማዳመጥ ተግባር፣ የንግግር ተግባር እና ግብረ መልስ፣ ድጋፍና ማበልጸግ በምን መልኩ በክፍል ውስጥ እነደሚተገበሩ ለማወቅ የተካሄደ ቃለመጠይቅ ነው፡፡

ቃለ መጠይቁ የተደረገው መምህራኖቹ በሰጡት ቀጠሮ እና አመቺ በሆኑ ቀኖች ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ቃለ መጠይቁ የተደረገው በአሌሉ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህርትን በ24/08/2010 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4፡00 - 4፡20 ሠዓት ባለው ጊዜ ውስጥ፣ በኤዱ መዳ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙት መምህርት በ3/9/2010 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4፡00 - 4፡20 ሠዓት ባለው ጊዜ ውስጥ እና በመልካ ኤሳ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህርት ደግሞ በ26/08/2010 ዓ.ም. ከሰዓት በኂላ ከ8፡30 — 8፤50 ሠዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ቃለመጠይቁ ባጠቃላይ አስራ አንድ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን ሶስቱም መምህራን ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ተጠቃሎ ከዚህ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### 4.3.1 የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴልን በተመለከተ

የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ(ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) የማስተማር ሞዴልን በየክፍለ ጊዜው በወሰዱት ስልጠና መሰረት በአግባቡ በክፍል ውስጥ ይተገብራሉ? ተብለው ለተነሳላቸው ጥያቄ (መ.1) "በሚገባ! ከዚህ ቀደም ሞዴሉን በተመለከተ የአስር ቀን ስልጠና ተሰጥቶን ነበር እኔም በዚህ ስለጠና ላይ ተሳትፌ ነበር፡፡ ከስልጠናው ባገኘሁት እውቀት መሰረት እየተገበርኩ ነው" በማለት ለተነሳላቸው ጥያቄ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከላይ የተነሳው ጥያቄ ለ(መ.2) ቀርቦላቸው እንዲህ በማለት መልሰዋል

> *የሞዴሉን አተገባበር በተመለከተ ስልጠና ወስጃለሁ፡፡ ነገር ግን የሰለጠንኩበት የትምህርት አይነት አስተዳደር ቢሆንም በትምህርት ቤታችን የአማርኛ ቋንቋ መምህር እጥረት ስላለ አማርኛ ቋንቋ እንዳስተምር ተመድቤ እያስተማርኩ እገኛለሁ፡፡ የማስተማርያ መጸሃፉ ሞዴሉን መሰረት አድርጎ ስለተዘጋጀ መጽሃፉ የግድ እንድንተገብር ያደርገናል፡፡ መጽሃፉን እስከተጠቀምን ድረስ የማስተማር ሞዴሉን መተግበር ግድ ነው፡፡*

በተመሳሳይ ከላይ ለቀረበው ጥያቄ (መ.3) "አዎን 2008 ዓ.ም. የሞዴሉን አተገባበር በተመለከተ ስልጠና ወስጃለሁ፡፡ በወሰድኩት ስልጠና መሰረትም በሚገባ በመተግበር ላይ እገኛለሁ፡፡" በማለት መልሰዋል፡፡

ሞዴሉን በአግባቡ የመተግበር ሁኔታን በተመለከተ ሁለም መምህራን በተመሳሳይ መልኩ አዲስ ተዘጋጅቶ ለማስተማርያ የቀረበውን መጸሃፍ እስከተጠቀምንበት ድረስ አዲሱ የማስተማር ሞዴል በሚያዘን መሰረት ከተማሪዎች ጋር በጋራ አብረን እንሰራለን በማለት በተመሳሳይ ሁኔታ መዴሉን ተጠቅመው እንደሚያስተምሩ ከመጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

### 4.3.2 በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴል የመምህሩ ሚና በተመለከተ

በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል እርሶ ሞዴል ሆነው ለተማሪዎች እንዲያሳዩ በሚጠይቅ ተግባር ላይ ሞዴል ሆነው ተግባራትን ለተማሪዎች ሰርተው ያሳያሉ? ተብሎ ለተጠየቁ ጥያቄ (መ.1) "አዎ! መጽሃፉ በሚያዘው መሰረት ማንኛውንም ተግባር ተማሪው ከመተግበሩ በፊት ሞዴል ሆኜ እተገብራለሁ ወይም አሳያለሁ" በማለት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ  መልስ ሰጥተዋል፡፡ (መ.2) ይህንኑ ጥያቄ አስመልክቶ እንዲህ በማለት መልሰዋል "የመምህሩ መምርያ በሚያዘው መሰረት ተግብሬ አሳያለሁ፡፡ ተማሪዎች በቡድንና በግል የተሰጣቸውን ተግባር ከመስራታቸው በፊት የትምህርቱን አጠቃላይ መልክ ላሳያቸው እሞክራለሁ" በማለት መልሰዋል፡፡ (መ.3) በበኩላቸው "የመምህሩ መምርያ በሚያዘው መሰረት በማንበብ ተግባር፣ በመጻፍ ተግባር፣ በማዳመጥ እና በመናገር ተግባራት በደንብ ተግብሬ አሳያቸዋለሁ" በማለት መልሰዋል፡፡

ሶስቱም መምህራን በተመሳሳይ መልኩ ሞዴል ሆነን ለተማሪዎች ሰርተን በምናሳየው ተግባር ላይ ሞዴል ሆነን እናሳያለን በማለት በተመሳሳይ መልኩ መልሰዋል፡፡ በአጠቃላይ ከመምህራን የተገኘው የቃል መጠይቅ መምህራኑ ሞዴል ሆነው ተግባራትን ተግብረው ለተማሪዎቻቸው እንደሚያሳዩ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

### 4.3.3 በሞዴሉ አብረን እንስራ ክንውንን በተመለከተ

በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል በእንስራ ጊዜ ከተማሪዎች ጋር በመሆን ተግባራትን አብረው ይተገብራሉ ወይም ይሰራሉ ተብለው ሲጠየቁ (መ.1)  "በእርግጥ ተግባራትን ከተማሪዎች ጋር አብሬ እተገብራለሁ ነገር ግን በክፍል ውስጥ ያለው የተማሪ ቁጥር፣ የተማሪ መጽሃፍ እጥረት እና የተማሪው ስነምግባር ጉዳይ ተግባራቱን ሙሉ በሙሉ በሞዴሉ መሰረት ለመተግበር አላስቻለኝም፡፡" በማለት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ መልስ ሰጥተዋል፡፡ (መ.2) ይህንኑ ጥያቄ አስመልክተው

> *እተገብራለሁ፡፡ ነገር ግን ትግበራው ከሙሉ ተማሪ ጋር ነው የሚካሄደው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እንደዚህ በገለጻ መልክ ለሁሉም ተማሪ መረጃ ከማቀበል ውጪ በግል ከእያንዳንዱ ተማሪ ጋር አብሮ ለመተግበር አስቸጋሪ ነው የሚሆነው፡፡ የተማሪ ቁጥር መብዛት፣ የመማርያ ክፍል*

*ሁኔታ እና የመጽሃፍ አለመኖር በአንድነት ተዳምረው ከእያንዳንዱ ተማሪ ጋር አብሮ ለመተግበር አስቸጋሪ ነው የሚሆነው፡፡*

በማለት መልስ የሰጡ ሲሆን (መ.3) በበኩላቸው ይህንኑ ጥያቄ አስመልክተው እንዲህ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

*መተግበሩን እተገብራለሁ፡፡ ነገር ግን ወንድሜ ሞዴሉን በተዋጣለት መልኩ ለመተግበር ግን እያንዳንዱ ተማሪ በነፍስ ወከፍ የመማርያ መጽሃፍ ሊያገኝ ይገባል፡፡ እኔ በማስተምርበት ትምህርት ቤት ግን የተማሪ መጽሃፍ የለም፡፡ ታድያ የመማርያ መጽሃፍ ተማሪው በእጁ ሳይኖረው ይህንን ተግባር በተሟላ መልኩ ለመተግበር አስቸጋሪ ነው፡፡*

ከቃለ ምልልሱ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው በእንስራ ጊዜ መምህራኑ የተለያዩ ተግባራትን ሞዴል ሆነው እንዳሳይዋቸው ሁሉ ከተማሪዎቻችውም ጋር አብረው እንደሚተገብሩ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው ምላሽ ያረጋግጣል፡፡ በሌላ በኩል ምንም እንኳን ተግባራቱን ከተማሪዎቻቸው ጋር አብረው ቢተገብሩም በክፍል ውስጥ ያለው የተማሪ ቁጥር፣ የመጽሃፍ እጥረት፣ የተማሪው የስነ ምግባር ጉዳይ ተግባራቱን በአግባቡ ለመተግበር ተግዳሮት እንደሆነባቸው ተናግረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተግባራቱን ለመተግበር እና እያንዳንዱን ተማሪ ለመድረስ የጊዜ እጥረት እነደሚገጥማቸው የተገኘው መረጃ ያሳያአል፡፡ በዚህም ምክኒያት እያንዳንዱን ተማሪ ለመድረስ ከመጣር ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎችን በአነስተኛ ቡድን(በክፍል ውስጥ ባለ የ1 ለ 5 አደረጃጀት) መሰረት ለመድረስ እንደሚሞክሩ በክፍል ምልከታ ወቅትም በአጥኚው ተስተውሏል፡፡

በአጠቃላይ መምህራኑ በሞዴሉ መሰረት ለመተግበር ጥረት ቢያደርጉም አብረን እንስራ የሚለው የሞዴሉ ሁለተኛ ክፍል ሙሉ በሙሉ እየተተገበረ እንዳይደለ ከጥናቱ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

### 4.3.4 በሞጁሉ የግልና የቡድን ተግባራትን በተመለከተ

በሞጁሉ አተገባበር በስሩ ጊዜ ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው የተለዩ ተግባራትን በግልና በቡድን እንዲሰሩ እድል ይሰጣቸዋል ለሚለው ጥያቄ (መ.2) ሲመልሱ"ተግባራትን በቡድን ለማሰራት አዳጋች አይደለም እድል ይሰጣቸዋል ነገር ግን ለእያንዳንዱ ተማሪ እድል ለመስጠት የተማሪው መጽሃፍ ስለሌለ በጣም አዳጋች ነው፡፡" ብለዋል (መ.1) ከላይ የቀረበውን ጥያቄ አስመልክተው እንዲህ ብለዋልል

> *በእኔ ልስራ ጊዜ ተግብሬ ያሰየሁትን በአብረን እንስራ ጊዜ አብረን የተገበርነውን በግልና በቡድን እንዲሰሩ አደርጋቸዋለሁ፡፡ ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ተማሪ በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ በግል ምን እንደተገበረ ለማየት የጊዜ እጥረት ያጋጥመኛል፡፡ ስለዚህ ባለኝ ጊዜ ከተወሰኑ ተማሪዎች ጋር ብቻ ነው አብሬ የምተገብረው፡፡*

በዚሁ ጥያቄ ላይ (መ.3) "እድል መስጠት እሰጣቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን እኔ እድሉን ብሰጣቸውም እጃቸው ላይ የተማሪው መጽሃፍ ከሌለ ምን ዋጋ አለው አንዳንድ ተግባራትን ክፍል ውስጥ በተገኘው መጽሃፍ መጠን ቡድን ሰርተው እንዲተገብሩ አደርጋለሁ፡፡" በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ከላይ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው እድሉን ለመስጠት ቢችሉም ተማሪው በተሰጠው እድል ተጠቅሞ እንዳይሰራ ግን ተግዳሮቶች አሉ እነዚህም የተማሪ ቁጥር መብዛት፣ የመማርያ መጽሃፍ አለመኖር እና የጊዜ እጥረት መሆናቸውን የመጠይቁ ውጤት ያረጋግጣል፡፡

### 4.3.5 በሞጁሉ የማንበብ ተግባርን በተመለከተ

በልስራ፣እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል በንባብ ተግባር ጊዜ ሞዴል ሆነው በማንበብ ተማሪዎች ልዩ ልዩ የንባብ ተግባር ሲያከናውኑ በመከታተል ተማሪዎችን ይረዳሉ ለሚለው ጥያቄ (መ.1) እንዲህ ብለው መልሰዋል

> *ሞዴል ሆኖ ለማንበብ ችግር የለብኝም ያለምንም ስህተት በጥሩ የድምጽ ቅላጼ ሞዴል ሆኜ ለተማሪዎች አነብላቸዋለሁ፡፡ እዚህ ላይ ግን አንድ ችግር አለ እያንዳንዱን ተማሪ በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ማስነበብ እጅግ አዳጋች ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ በራሴ በኩል የማደርገው*

*ለየቡድኑ አንዳንድ ተማሪ እነዲያነብ እድል እሰጥና ለማንበብ እክል ሲገጥማቸው በተቻለ መጠን የገጠማቸውን ችግር ለመፍታት እሞክራለሁ፡፡*

ይህንኑ ጥያቄ አስመልክቶ (መ.2) እንዲህ በማለት መልሰዋል

*መጽሃፉ አድርጉ ስለሚል ሞዴል አንባቢ ሆኜ ድምጼን ከፍ አድርጌ ካነበብኩ በኋላ ተማሪዎቹም ልክ እኔ ባነበብኩት የድምጽ ቅላጼ እንዲያነቡ እድል እሰጣቸዋለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ለዚያ ሁሉ የክፍል ተማሪ በግል ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ እጂግ ፈታኝ ነው የሚሆነው፡፡*

ይህንኑ ጥያቄ አስመልክቶ (መ.3) በበኩላቸው ከዚህ እንደሚከተለው መልስ ሰጥተዋል

*ሞዴል ሆኜ አነባለሁ፡፡ በማነበበት ጊዜ በተቻለኝ አቅም ያለምንም ስህተት ለማንበብ እሞክራለሁ፡፡ በንባብ ተግባር ጊዜ እያንዳንዱ ተማሪ ንባብን እንዲተገብር እና ትግበራውንም ለመከታተል አስቸጋሪ ነው የሚሆነው፡፡ ይሁን እንጂ በየክፍለ ጊዜው የማንበብ እድል የሚገጥማቸውን ተማሪዎች እንዴት እንደሚያነቡ ተከታትዬ አስፈላጊውን ድጋፍ አደርግላቸዋለሁ፡፡ ሌላው ችግር ለፈጣን ተማሪዎች ተጨማሪ የንባብ መጽሃፍ አለማግኘት ነው፡፡*

ከላይ ለቀረበው ጥያቄ ሶስቱም መምህራን በተመሳሳይ መልኩ ሞዴል ሆነው እንደሚያነቡ እና ለእያንዳንዱ ተማሪ ግን የማንበብ አድል ለመስጠት እንደሚቸገሩ እና በሞዴሉ መመርያ መሰረት ለፈጣን አንባቢዎች ተጨማሪ የንባብ መጽሃፍ እንደማይሰጡ ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

### 4.3.6 በሞዴሉ የንግግር እና የጽህፈት ተግባርን በተመለከተ

በእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ተማሪዎች የንግግር እና የጽህፈት ተግባርን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ (መ.1)

*በእርግጥ በተቻለኝ መጠን ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ አደርግላቸዋለሁ ይሁን እንጂ አሁንም ይህንን ተግባር ለመተግበር ችግር አለ፡፡ ሁሉንም*

*ተማሪ በንግግር ተግባር ለማሳተፍ እና ለመገምገም አዳጋች ነው፡፡ በጽህፈትም ጊዜ እያንዳንዱ ተማሪ እንዴት እንደሚጽፍ በነፍስ ወከፍ ለመከታተልና ድጋፍ ለማድረግ ከተማሪው ቁጥር አንጻር አስቸጋሪ ነው፡፡*

በዚሁ ጥያቄ ላይ (መ.2) እንዲህ በማለት መልሰዋል፡፡ "በመጠኑም ቢሆን ክትትል እና ድጋፍ አደርግላቸዋለሁ ነገር ግን ሁሉንም ተማሪ በትክክል በአንድ ክፍለ ጊዜ ለመርዳት አስቸጋሪ ነው፡፡ በዚህ ተግባር እያንዳንዱን ተማሪ ለመርዳት እንዲሁም እንዲናገር እና እንዲጽፍ እድል ለመስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ በማለት መልሰዋል፡፡" (መ.3) በበኩላቸው

*ክትትልና ድጋፍ አደርጋለሁ፡፡ ነገር ግን ከላይ ልገልጽልህ እንደመከረኩት የተማሪ መጽሃፍ እጥረት እና የተማሪ ቁጥር መብዛት ሁሉንም ተማሪ በአንድ ክፍለ ጊዜ ለመድረስ አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለዚህ እድል ለደረሳቸው ተማሪዎች ክትትል እና ድጋፍ አደርግላቸዋለሁ፡፡* በማለት መልስ ሰጥጠዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለቀረበው ጥያቄ ሶስቱም መምህራን ቅድመ መጻፍና ቅድመ ንግግር ተግባርን በየደረጃው እንደሚያከናውኑ እንዲሁም ተማሪዎች የንግግርንና የመጻፍን ተግባር በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ተገቢ የሆነ ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርጉላቸው ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህም ክፍል እያንዳንዱን ተማሪ በየክፍለ ጊዜው እድል ሰጥቶ ለማሳተፍ እንዳልተቻለ የተገኘው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

### 4.3.7 ተግባራትን በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ተግብሮ መጨረስን በተመለከተ

በሞዴሉ የእለቱን፣ የሳምንቱን እና የምራፉን ትምህርት በተሰጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ሰርተው ወይም ተግብረው ያጠናቅቃሉ ለሚለው ጥያቄ (መ.1) "ያልኩህ ችግሮች እንዳሉ ሆነው የሳምንቱንና የወሩን ትምህርት በእቅዱ መሰረት ተግባራዊ አደርጋለሁ፡፡ የአመቱን ትምህርት ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ ግን አልችልም፤ የጊዜ እጥረት ያጋጥመኛል፡፡ የትምህርት ጊዜዎች በስብሰባ ይባክናሉ፡፡" (መ.2) ይህንኑ ጥያቄ አስመልክተው እንዲህ በማለት መልሰዋል

*የእለቱን፣ የሳምንቱንና የምእራፉን ትምህርት በተመደበለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ተግብሬ ለማጠናቀቅ እችላለሁ፡፡ እያደረግኩትም ነው፡፡ ነገር ግን ምን መሰለህ የእለቱን፣ የሳምንቱን እና የምእራፉን ትምህርት ማጠናቀቅ*

*ብቻ በቂ አይደለም። የአመቱ ትምህርት ሲጀምር አንድ ወር ዘግይቶ ነው። በተለያየ ጊዜ የተለያየ ስብሰባ ይኖራል። እነዚህ እና የመሳሰሉ ጉዳዮች የአመቱን የትምህርት ጊዜ በእጅጉ ይጎዱታል። በዚህም ምክንያት በመጽሃፉ ውስጥ በአንድ አመት እንዲጠናቀቁ ተለክተው የጠሰጡ ተግባራት በአንድና በሁለት ምራፍ ወደኋላ ይቀራሉ። ይህ እንዳይሆን እና መጽሃፉን ለማጠናቀቅ በጥድፊያ ለማጠናቀቅ እንገደዳለን።*

ይህንኑ ጥያቄ አስመልክቶ (መ.3)

*የእለቱን፣ የሳምንቱን እና የምእራፉን ትምህርት በተሰጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ለመተግበር የጊዜ እጥረት ያጋጥመኛል፡፡ ለዚህም ምክንያት ናቸው የምላቸው*

1. *ብዙ ተማሪ በአንድ ክፍል ውስጥ መኖር*
2. *በአመቱ መጀመርያ ዘግይቶ ትምህርት መጀመር*
3. *በልዩ ልዩ ስብሰባ የትምህርት ጊዜ መባከን*
4. *የሁለተኛ ወሰነ ትምህርት ዘግይቶ መጀመር*
5. *የተማሪ መጽሃፍ እጥረት መኖር ናቸው።*

ከላይ የቃለ መጠይቁ መልስ ሶስቱም መምህራን የእለቱን፣ የሳምንቱን እና የምእራፉን ትምህርት በተሰጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ እንደሚተገብሩ ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ይቻላል። የአመቱን ትምህርት ለማጠናቀቅ ግን የጊዜ እጥረት እንዳለባቸው በምላሻቸው ገልጸዋል።

በአጠቃላይ የእለቱን፣ የሳምንቱን እና የምእራፉን ትምህርት ለማጠናቀቅ እንደሚሞክሩ ነገር ግን የጊዜ እጥረት እንደሚያጋጥማቸው የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል። በተጨማሪም የጥናቱ ውጤት በሞዴሉ እየተገበሩ ለአመቱ ትምህርት የተዘጋጀውን መጽሃፍ ለማጠናቀቅ እንደማይችሉ የጥናቱ ውጤት ያረጋግጣል።

### 4.3.8 ማበረታቻና ግብረ መልስን በተመለከተ

በትምህርት ሂደት የተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ የሚያጠናክር ተገቢ የሆኑ አዎንታዊ ማበረታቻ ይሰጣሉ ግብረ መልስ ሲሰጡስ ስህተት ወይም ትክክል መሆኑን በመንገር ነው ይህንን ጥያቄ አስመልክተው (መ.1) “በደንብ እንጂ! ለተማሪዎች የምሰጣቸው ሌላ ማበረታቻ ባይኖረኝም በጣም ጥሩ! ጎበዝ! በማለትና ለተሳትፏቸው

መጠነኛ ማርክ በመስጠት አበረታታቸዋለሁ፡፡" በማለት መልሰዋል፡፡ (መ.2) በበኩላቸው "እሰጣለሁ፡፡ ማበረታቻ ተማሪን ያነቃቃል፡፡ በተጨማሪም ከአዎንታዊ ማበረታቻ ጎን ለጎን ስህተት ከፈጸሙ ስህተቱ እንዴት ሊፈጸም እንደቻለ እና እንዴት እንደሚታረም እነግራቸዋለሁ፡፡" (መ.3) ይህንኑ ጥያቄ አስመልክተው

> *እሰጣለሁ፡፡ የትምህርት ተሳትፏቸውን ለማጠናከር የጠሰጣቸውን ተግባር ሰርተው ካጠናቀቁ በኋላ የሰሩት ተግባር ትክክል ሆነ አልሆነ ስለሙከራቸው ብቻ አበረታታቸዋለሁ፡፡ ይህንን ሳደርግ ግን ከማበረታቻው በኋላ የሰሩት ተግባር ትክክል ነው ወይም አይደለም ለሚለው ማብራርያ እሰጣቸዋለሁ፡፡* በማለት መልሰዋል፡፡

በአጠቃላይ ሶስቱም መምህራን የተማሪዎቻቸውን የትምህርት ተሳትፎ የሚያጠናክር ተገቢ የሆኑ አዎንታዊ ማበረታቻዎችን እንደሚሰጡ በምላሾቻቸው ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ለተጠየቁት ጥያቄ በሚሰጡት ምላሽ ላይ አስተያየት ስንሰጥ ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን በመንገር ስህተቱ እንዴት እንደተከሰተ በማሳየት ከስህተቱ የሚታረሙበትን ብልሃት በማሳየት ጭምር ነው በማለት መልስ ሠጥተዋል፡:

### 4.3.9 ተከታታይ ምዘናን በተመለከተ

በማያቋርጥ ሂደት ተማሪዎች እንዴት እየተማሩ እንደ ሆነ መረጃ ለመሰብሰብ ተከታታይ ምዘና ለተማሪዎች ይሰጧቸዋል ተብለው የቀረበላቸውን ጥያቄ አስመልክተው (መ.1) "በሚገባ እሰጣለሁ ተማሪዎቼ የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል ተረድተውታል የሚለውን ለማወቅ ተከታታይ ምዘና ባወጣሁት ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ አመታዊ እቅድ መሰረት ምዘና ለተማሪዎቼ እሰጥና እገመግማቸዋለሁ፡፡" በማለት ገልጸዋል

ይህንን ጥያቄ አስመልክተው (መ.2) እንዲህ በማለት መልሰዋል፡፡

> *ባወጣሁት አመታዊ እቅድ መሰረት ተማሪዎቼ በተማሩት ትምህርት ምን ያህል ውጠየታማ ናቸው የሚለውን ለመገምገም ተከታታይ ምዘና እሰጣለሁ፡፡ ከምዘናው ተነስቼ ተማሪው በተማረው ትምህርት ምን ያህል ውጠየታማ እንደሆነ መረጃ እሰበስባለሁ፡፡ የሰበሰብኩት መረጃ ያለውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን እገመግምማለሁ፡፡ ባገኘሁትም ውጤት ላይ ተመርኩዤ የተማሪዎቼን ክፍተት በመለየት እረዳቸዋለሁ፡፡*

ይህንኑ ጥያቄ አስመልክቶ (መ.3)

> *ተከታታይ ምዘና እሰጣለሁ፡፡ ነገር ግን ተከታታይ ምዘናው የሚሰጠው አጫጭር ጥያቄዎች፣ አንድ የጥያቄ አይነት፣ ውስን መመርያ ያላቸውን ጥያቄዎች ብቻ ነው ለተማሪዎች ምዘና የምንሰጠው፡፡ ሌላው ቀርቶ የሴሚስተር አጋማሽ እና የሴሚስተር ፈተናዎችን እንኳን በጥቁር ሰሌዳ ነው ጽፈን የምንሰጠው፡፡ በቂ የትምህርት ቁሳቁስ በሌለበት ደግሞ ምዘናው ሙሉ በሙሉ ውጤታማ ይሆናል ለማለት አይቻልም፡፡*

በአጠቃላይ ሶስቱም መምህራን ባወጡት አመታዊ እቅድ መሰረት ተከታታይ ምዘናዎችን እንደሚሰጧቸው እና እንደሚገመግሟቸው እንደዚሁም አጠቃላይ ምዘና በየወሰነ ትምህርቱ እንደሚሰጧቸው እና የተማሪዎችን አጠቃላይ የትምህርት አቀባበል በሚያስመዘግቡት ውጤት መሰረት እነደሚገመግሙ ገልጸዋል፡፡ የተገኘው መረጃ በአጠቃላይ የሚያመለክተው ተከታታይ ምዘና እንደሚሰጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ምዘናው የታለመለትን ግብ እንዲመታ አስፈላጊው የትምህርት ቁሳቁስ ስላልተሟላ በቂውጤት ይገንበታል ተብሎ አይታመንም፡፡

### 4.3.10 በሞዴሉ የጾታ እኩልነትን በተመለከተ

በክፍል ውስጥ የጾታ እኩልነትን የሚያረጋግጡ ወይም የሚያዳብሩ የማስተማርያ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ ለሚለው ጥያቄ (መ.1) “ስለሞዴሉ አተገባበር ስልጠና በወሰድኩት መሰረት ከቡድን ምስረታ ጀምሮ በትምህርቱ ሂደት ላይ ምሳሌ ስሰጥ፣ ጥያቄ ስጠይቅ፣ ጥያቄ እንዲመልሱ ሳደርግ ፍትሃዊ የጾታ እኩልነት እንዲረጋገጥ አደርጋለሁ፡፡ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡” (መ.2) ይህንን ጥያቄ አስመልክተው “ባገኘሁት ስልጠና መሰረት የጾታ እኩልነት የሚያረጋግጡ ዘዴዎችን እጠቀማለሁ፡፡ ምሳሌ የምሰጠውም ሁለቱንም ጾታ ባማከለ መልኩ ነው፡፡ ጥያቄ ስጠይቅና ለጥያቄ መልስ እንዲሰጡ ሳደርግ ሁለቱንም ጾታ በእኩል ነው የማሳትፈው፡፡” በማለት መልሰዋል፡፡

ይህንኑ ጥያቄ አስመልክተው (መ.3) መልስ ሲሰጡ “በሚገባ አጠቀማለሁ ምሳሌ ስሰጥ ጥያቄ ስጠይቅ ሁለቱንም ጾታ በእኩል ነው የማሳትፈው፡፡” በማለት መልሰዋል፡፡

በቃለ መጠይቁ የጠሳተፉ መምህራን በክፍል ውስጥ ከሚመሰርቱት ቡድን ጀምረው የጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ጥረት እንደሚያደርጉ፣ የተለያዩ ምሳሌዎችን ሲሰጡ

ሁለቱንም ጾታ መሰረት በማድረግ እንደሚሰጡ እነዲሁም ጥያቄ ሲጠይቁ ለጥያቄ መልስ ሲቀበሉ ለሁለቱም ጾታ እኩል እድል በመስጠት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በአጠቃላይ ሞዴሉን ተጠቅመው ሲያስተምሩ ሁለቱንም ጾታ ከአድሎ በጸዳ መልኩ በክፍል ውስጥ በእኩል እነደሚያሳትፉ የጥናቱ ውጠየት አረጋግጧል፡፡

### 4.3.11 በሞዴሉ አካቶ ትምህርት ልዩ ፍላጎት ትምህርትን በተመለከተ

የሁሉንም ተማሪዎች ብዝሃ ፍላጎት ለማርካት እና መገለልን ለመቀነስ አካቶ ትምህርትንና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸዋል ለሚለው ጥያቄ (መ.1) "ለጊዜ እኔ በማስተምርበት ክፍል ውስጥ አካል ጉዳተኛ ተማሪ የለም፡፡ ነገር ግን በተለያየ ጉዳይ የስነ ልቦና ችግር የገጠማቸውን ተማሪዎች ለመርዳት እሞክራለሁ፡፡" (መ.2) የህንኑ ጥያቄ አስመልክተው "እኔ በማስተምርበት ትምህርት ቤት የለም፡፡ እነዚህ እ-እ-እ- ወጣ ያለ አስተሳሰብና ወጣ ያለ ባህሪ ያላቸው ተማሪዎች ከባህሪያቸውና ከፍላጎታቸው አንጻር ልረዳቸው እሞክራለሁ፡፡" (መ.3) ይህንን ጥያቄ አስመልክተው "እኔ በማስተምርበት ክፍል ውስጥ አካል ጉዳተኛ ተማሪ የለም፡፡ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ግን በሞዴሉ መመርያ መሰረት እረዳቸዋለሁ፡፡"

በአጠቃላይ በሰጡት ምላሽ አካልጉዳተኛ ተማሪ ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት እንደሌለ ነው፡፡ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በወሰዱት ስልጠና መሰረት እንደሚተገበሩ በሰጡት ምላሽ አረጋግጠዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳብ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሻሸመኔ ከተማ በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል የአተገባበር ሁኔታ ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ በጥናቱ ሂደት ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት ያሉ መምህራንና ተማሪዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ አጥኚው ይህንን ጥናት ሲያጠና ለጥናቱ መረጃ ለማሰባሰብ የክፍል ውስጥ ምልከታን እና የተማሪ መጠይቅን በዋናነት የተጠቀመ ሲሆን ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅን በደጋፊ የመረጃ ማሰባሰብያ መሳሪያነት ተጠቅሞበታል፡፡ በነዚህ የመረጃ ማሰባሰብያ መሳሪያዎች ተገኘው መረጃ መሰረት በማድረግ በምእራፍ አራት ውስጥ የምልከታውንና የጽሁፍ መጠይቁን በዋናነት፣ እንዲሁም ቃለመጠይቁን በደጋፊነት በማስቀጥ ትንተና ተካሂዷል፡፡

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ትንተናውን መሰረት በማድረግ ልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል በክፍል ውስጥ በመተግበር ረገድ የታዩትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት ጠንካራው ጎን ተሻሽሎ እና ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ ደካማ ጎኖች ደግሞ የሚሻሻሉበትን ሁኔታ የሚጠቁም የማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

## 5.1 ማጠቃለያ

የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል የክፍል ውስጥ አተገባበር በሻሸመኔ ከተማ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በስምንተኛ ክፍል ተተኳሪነት ያለውን ሁኔታ በሚመለከት ከትንተናው የተገኘውን ውጤት መነሻ በማድረግ የሚከተሉት የማጠቃለያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል በክፍል ውስጥ ሲተገበር ጉድለት ሆነው የታዩ ነገሮች አሉ እነዚህም

- ተማሪዎች የግልና የቡድን ስራዎችን በተሰጠው ክፍለ ጊዜ ውስጥ ሰርተው ለማጠናቀቅ ወይም ተግብረው ለመጨረስ የጊዜ እጥረት እንደገጠማቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

- መምህራን በወሰዱት ስልጠና መሰረት ሞዴሉን ተጠቅመው በክፍል ውስጥ እያስተማሩ ቢሆንም ሞዴሉን ሙሉ ለሙሉ በክፍል ውስጥ ለመተግበር እንደተሳናቸው የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡
- ሞዴሉ ለተማሪዎች ምቹ ሁኔታ ቢፈጥርላቸውም ተግባራትን ሙሉ ለሙሉ ለመተግበር የመጽሃፍ እጥረት እንደገጠማቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡
- እያንዳንዱ ተማሪ አቀላጥፎ የማንበብ እድል እንደማይሰጠው የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡
- የንባብ ተግባርን ቀድመው ለሚያጠናቅቁ ፈጣን ተማሪዎች ተጨማሪ የንባብ መጸሃፍ እንደማይሰጣቸው በጥናቱ ታይቷል፡፡
- በማዳመጥ ተግባር ጊዜ ለተማሪዎች ምዘና በአግባቡ እንደማይሰጣቸው፣ ድጋፍና ማበልጸግም በአግባቡ እንደማይሰጥ ወይም እንደማይደረግላቸው ጥናቱ አመልክቷል ፡፡
- አዳምጠው ለመረዳት ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ምንም አይነት ልዩ ድጋፍ እንዳልተደረገላቸው ጥናቱ አሳይቷል፡፡
- በክፍል ውስጥ ሁሉም ተማሪ የመናገር እድል እንደማይሰጠው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡
- እያንዳንዱ ተማሪ ተግባራትን ለመፈጸም ምቹ የሆነ የተማሪ መቀመጫ እንደሌለው በጥናቱ ወቅት ታይቷል፡፡
- የመማርያ መጸሃፍ እጥረት በክፍል ውስጥ ታይቷል፡

በአጠቃላይ ከጥናቱ የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው በአሁኑ ጊዜ የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴል በትቤቶቹ እየተተገበረ ቢሆንም አተገባበሩ ግን በስልጠናው መሰረት ሙሉ በሙሉ ሞዴሉን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ያልተቻለ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሃሳብ

በጥናቱ ውጤት መሰረት አጥኚው የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል በክፍል ውስጥ ሲተገበር ሊሻሻሉ ይገባቸዋል ያለውን የመፍተሄ ሃሳብ እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

- ተማሪዎች የግልና የቡድን ተግባርን በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ማከናወን ያልቻሉት በክፍል ውስጥ ካለው ተማሪ ቁጥር የተነሳ ስለሆነ በተቻለ መጠን በትምህርት ቤቱ አስተዳደር በኩል በክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች አነስተኛ ቁጥር እንዲኖራቸው ቢደረግ፣
- ለመምህራን በጥናቱ የታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት ተጨማሪ የማነቃቂያ ስልጠና ቢሰጣቸው፣
- ተማሪዎች ጥሩ አንባቢ እንዲሆኑ በተለያየ ምክንያት የሚባክነው የትምህርት ጊዜ በአግባቡ በጥቅም ላይ ውሎ ለተማሪዎቹ በቂ የንባብ ጊዜ ተሰጥቷቸው ውጤታማ እንዲሆኑ በት/ቤቱ አስተዳደርና በየደረጃው ባሉ የትምህርት ባለሞያዎች ተገቢ ትኩረት በመስጠት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት ቢያደርጉ፣
- ፈጣን አንባቢ ተማሪዎች በምንባብ ጊዜ ፈጥነው አንብበው ስለሚጨርሱ ሌሎች ተማሪዎች አንብበው እስኪጨርሱ ሌሎች ለደረጃው የሚመጥኑ እና ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን መጽሃፎች እያነበቡ እንዲቆዩ እና እንዳይረብሹ ተጨማሪ የንባብ መጽሃፍ ትምህርት ቤቱ ወይም ወላጆች ቢያዘጋጁላቸው፣
- በማዳመጥ ትምህርት ጊዜ ተማሪዎቹ ስላዳመጡት ነገር ምንያህል ግንዛቤ እንዳገኙ ቢገመገሙና በዘላቂነት ክትትልና ድጋፍ ቢደረግላቸው፣
- አዳምጦ የመረዳት ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት ችግራቸውን ለመቅረፍ በቂ ክትትልና ድጋፍ ቢደረግላቸው እና ከላይ የተዘረዘሩት ጉድለቶች ተለይተው ቢቀረፉ ሞዴሉን ተጠቅሞ በማስተማር ይመጣል የተባለው ውጤት በእርግጥም ሊመጣ ይችላል፡፡

## ዋቢ ፅሁፎች


በድሉ ዋቅጂራ። (2007)። *በስነ ፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር።* አዲስ አበባ፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማ።

ትምህርት ሚኒስቴር። (2009)። *መምህርነት ቅድመ ሁኔታ የማይገድበው ወላጅነትና ባላደራነት ማሰልጠኛ ማንዋል።* (ያልታተመ)

ትምህርት ሚኒስቴር። (2007)። *አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመምህራን ማሰልጠኛ ማንዋል።*

አለማየሁ ተ/ማሪያም። (2009)።*በመተባበር መማር*።አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲነግ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር።

ኤልያስ አድማሱ፡፡ (1997)፡፡ *"በኦሮሚያ መምህራን ኮለጅ ውስጥ መሰረታዊ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ"* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)

እንግዳ ዘውዴ፡፡ (1992)፡፡ *"የ "ቶፕ ዳውን"* (Top-down) *የንባብ ማስተማርያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት ፡-በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት"* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)

ውቤ ጣሰው፡፡ (2002)፡፡ *"በበጌምድር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ትምህርት ክፍል የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ"* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)

ያለው እንዳወቀ። (2006)። *የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር።* አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ደረጀ ነጋሽ፡፡ (1999)፡፡ *"የተማሪ ተኮር አቀራረብ አተገባበር ፍተሻ በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል በ10+3 የስልጠና መርሃ ግብር"* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)

ደረጀ ገብሬ። (2007)። *በተማሪዎች የቤት ስራ የመምህራንና የወላጆች ሚና ።* አዲስ አበባ፣ አፍሪካ ማተምያ ኃላ/የተ/የግ/ማ ።

ፀሐይ ሃይለመስቀል፡፡ (2003)፡፡ “በስነ ልሳን ኮርሶች አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴ የክፍል ውስጥ አተገባበር በደሴና በደብረብርሃን መምህራን ትምህርት ኮለጅ” አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)

Brown,H. (1994). Teaching by principles: an Introduction Approach to language Pedagogy. London: prentice hall.

Buehl, D, (2005).Scaffolding, Reading Room, Retrieved April 26, WWW.weac.Org/News/2005- 06/sept 05/ reading Room oct 05.htm›(November 11,2006).

Douglas Fisher and nancy Frey. (2008) “Gradual Release of Responsibility Frame work for Active learning.” https: / / WWW. Thinkport. Org /grr/ index. Htmal.

------------ (2008) “Better Learning Through Structured Teaching” A framework for the Gradual Release of Responsibility, 2nd Edition WWW. Ascd. Org /Publictions/ Book / overiew/ Better-Learning-Through, Structured-Teaching.

Duke, N. K. and P. D Pearson (2002). “ Efective Practices for Developing Reading Comprehention, ” International Reading Association, Nework, Delaware.

Ellis, R, (1989),*Understanding second language Acquisition* (5th ed) Oxford: Oxford University Press.

Fisher, D. and N.Frey (2007). ‹‹Implimenting a scool Wide literacy Fremwork: Improving achievement in an urban elementary scool ››The Reading Teacher.

--------------(2008). *Better Learning Through structured Teaching*: *A framework for the Gradual Release of responsibility*. Alexandria, VA: ASCD.

--------------(2008). “Home work and the gradual release of responsibility: making ‹‹responsibility›› *Possible English Journal*. 98(2), 22-30.

Frey, N. and D.Fisher, (2oo6). *Language Arts Workshoop. Purposeful Reading and Writing instruction,* Merrill Education, upper saddle River, New Jersey.

Kral. T. (1996). *Teache Development. Making the right Moves*, Washing English Language Programs Division.

Kong, A. and P. D. Pearson (2003). ‹‹The Road to Participation: The constraction of a Literacy practice in a Learnig Community of Lingustically Divere Learning, ›› Research in The Teaching of Engilish. Journal 87(3) 30.

Larsen. Freeman, D, and Richards, J. (1986). *Teacher learning in language Teaching*. Journal. 66(2), 140-149,

Levy, E. (2007). *Gradual Release of Responsibility: I Do, We do, You Do*, Retrieved October 12, 2015, Retrieved from http/ /WWW. Sjboces. Org /doc/Gifted/ Gradual Release Responsibility jan 08.

Maynes, N. , Julien-Schultz, L. (2010). Modeling and the Gradual Release of Responsibility: What does it look like in the classroom? Brock Education Journall, 19(2), 65-77. Retrieved from http: / / WWW. Ed brocku.ca /ois/ index. Php/brocked/ article /view/ 136/ 131.

Norrish H, J. (1983). *Language Learners and their Errors*. London and Basing stoke, Mcmilan publishers Ltd.

Pearson, PD, Gallagher, M. (1983).‹‹The instruction of Reading Comprehension.›› Contemporary Educationl Psychology. Washington, DC: University of Illiois, National institute of Education. Journal v.1.

Raimes, A (1983). *Techniques in Teaching Writing.* Oxford University Press.

Richards, J. C, and Rodgers, T.S. (1986). Errors Analysis Perspectives on Second Language Acquisition London and New York. Longman Group Ltd.

Richards, C.J and Rodgers, S.T. (2001). Approaches and Methods in Language Teaching. 2nd ed. Cambridge: Cambridge University Press.

Tharp, R. , and Gallimore, R. (1991). ‹‹Atheory of teaching as assisted performance.›› Inp. Light, S. Sheldon, and M. Woodhead (Eds.) Learning to think. London, New York: The open University.P:

Tudor.I.(1996).*lerner centredness as language Education.* Cambridge: Cambridge university Press.

Underwood, M. (1989). Teaching Listening. London: Longman Group Ltd.

Wendon,Anta and Joan Rubin,(1987).*Learning Strategies in Language Learning*. New York: Prentice Hall International (UK)Lted.

# አባሪዎች

# አባሪ አንድ

# የምልከታ ቅፅ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ቋንቋዎች ጥናት፣ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር

## ክፍለ ትምህርት የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የዚህ የክፍል ውስጥ ምልከታ ዋና አላማ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል የክፍል ውስጥ አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት መሳካት አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት እችል ዘንድ እና የክፍል ውስጥ ምልከታ አደርግ ዘንድ ለሚደረግልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

1.የትምህርት ቤቱ ስም------------------------------------------------------------------------

2.ምልከታው የተደረገበት ቀን-------------------------

3. ምልከታ የተደረገበት ክፍል ---------------ምድብ ----------------------

4. የክፍለ ጊዜ ርዝመት--------------------------

5.በክፍሉ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት ወንድ---------ሴት---------ድምር-----------

6. ትምህርቱ የተጀመረበት ሰዓት------------የተጠናቀቀበት ሰዓት------------------

7. የትምህርቱ ርዕስ----------------------------------------------------

**መግለጫ** - የምልከታው ቅፅ ሁለት አማራጮች አሉት፡፡ 1. አዎ (ተተግብሯል)

2.የለም (አልተተገበረም) የሚል ነው፡፡

| ተ.ቁ | የምልከታ መከታተያ ጥያቄዎች(ተግባራት) | ተተግብሯል | አልተተገበረም |
|---|---|---|---|
| 1 | በልስራ፣እንስራ፣ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የግልና የቡድን ተግባራት | | |
| 1.1 | በቡድን በመደራጀት የቡድን ተግባራትን ይተገብራሉ? | | |
| 1.2 | በግል ተግባራት ጊዜ ለሁሉም ተማሪ እኩል እድል ይሰጣል? | | |
| 1.3 | ተማሪዎች የተለያዩ ተግባርን በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ሰርተው ወይም ተግብረው ያጠናቅቃሉ? | | |
| 1.4 | ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን የመሰረቱት ቡድን የጾታ ስብጥርን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው? | | |
| 1.5 | ተማሪዎች ከተግባራት በኋላ በቡድን ያገኙትን ውጤት እንዲያቀርቡ እድል ይሰጣቸዋል? | | |
| 1.6 | እያንዳንዱን ተግባር መምህሩ ሞዴል ሆነው ሰርተው ያሳያሉ? | | |
| 1.7 | መምህሩ ተግባራትን ከተማሪዎች ጋር አብረው ይሰራሉ? | | |
| 2 | በልስራ፣እንስራ፣ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የጾታ ተኮር፣ አካቶ ትምህርትና ልዩ ፍላጎት ትምህርት አተገባበር | | |
| 2.1 | ሴትና ወንድ ተማሪዎች ከአድሎ በጸዳ መልኩ በእኩል ይስተናገዳሉ? | | |
| 2.2 | የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ይደረግላቸዋል? | | |
| 2.3 | ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ተገቢ የሆነ ድጋፍ ይደረግላቸዋል? | | |
| 3 | የልስራ፣እንስራ፣ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የንባብ ተግባር | | |
| 3.1 | የማንበብ ተግባራትን ሲተገብሩ የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ ፣ መተንበይ . . . በአግባቡ ይተገብራሉ? | | |
| 3.2 | የማንበብ ተግባርን መምህሩ ሞዴል ሆነው ያያሳያሉ? | | |
| 3.3 | መምህሩ እያንዳንዱ ተማሪ አንብቦ መረዳቱን በአግባቡ ይከታተላሉ? | | |
| 3.4 | እያንዳንዱ ተማሪ አቀላጥፎ የማንበብ እድል ይሰጠዋል? | | |
| 3.5 | መምህሩ ተማሪዎች የማንበብ እክል ሲገጥማቸው በግል ይረዷቸዋል? | | |
| 3.6 | ለፈጣን አንባቢዎች የማንበብ ተግባርን ካጠናቀቁ በኋላ ተጨማሪ የንባብ መጽሃፍ በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ይሰጣቸዋል? | | |
| 4 | በልስራ፣እንስራ፣ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የመጻፍ ተግባር | | |
| 4.1 | የቅድመ መጻፍ ተግባራትን በየደረጃው ያከናውናሉ? | | |
| 4.2 | በጽህፈት ተግባር ጊዜ ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው በግል እንዲጽፉ እድል ይሰጣቸዋል? | | |
| 4 .3 | ተማሪዎች በጽህፈት ጊዜ ችግር ሲገጥማቸው መምህሩይረዷቸዋል? | | |
| 5 | በልስራ ፣እንስ ፣ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የማዳመጥ ተግባር | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5.1 | በማዳመጥ ተግባር ጊዜ ለተማሪዎች ምዘና ወይም ፈተና ይሰጣቸዋል? | | |
| 5.2 | ተማሪዎች የማዳመጥን ተግባር ካከናወኑ በኋላ ድጋፍና ማበልጸግ ይደረግላቸዋል? | | |
| 5.3 | አዳምጦ የመረዳት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ይደረገላቸዋል? | | |
| 6 | በልስራ፣እንስራ፣ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የንግግር ተግባር | | |
| 6.1 | እያንዳንዱ ተማሪ በግል ንግግር እንዲያደርግ እድል ይሰጠዋል? | | |
| 6.2 | ተማሪዎች በንግግር ጊዜ ለሚገጥማቸው ችግር ማስተካከያ ይሰጣቸዋል? | | |
| 7 | በልስራ፣እንስራ፣ስሩ(ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል ግብረ መልስ ፣ድጋፍና ማበልጸግ | | |
| 7.1 | መምህሩ የመማር ፍላጎታቸውን የሚያነሳሳና እንዲጨምር የሚያደርግ ግብረ መልስና ድጋፍ ይሰጣቸዋል? | | |
| 7.2 | ለተማሪዎች ግብረ መልስ ሲሰጣቸው ትክክል ወይም ስህተት መሆኑ ይነገራቸዋል? | | |
| 7.3 | ለተማሪዎች ወቅቱን የጠበቀ ግብረ መልስ ይሰጣቸዋል? | | |
| 7.4 | ለተማሪዎች ምዘና በአግባቡና በተገቢው ጊዜ ይሰጣቸዋል? | | |

# አባሪ ሁለት

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮለጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረምረቃ መርሃ ግብር

### ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

ይህ መጠይቅ በሻሸመኔ ከተማ በሚገኙ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ ሞዴል የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ያተኩራል፡፡ መጠይቁ በክፍል ውስጥ ፍተሻ አድርጎ ለሚካሄደው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ታቅዶና ይህንን መሰረት አድርጎ ለ8ኛ ክፍል የአማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡

ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ለጥናቱ መሳካት የበኩላችሁን ትብብር እንድታደርጉልኝ በማለት በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

በቅድሚያ ውድ ጊዜያችሁን ሰጥታችሁ ላደረጋችሁለኝ ትብብር ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ**

-በመጠይቁ ላይ ስም፣ ክፍል፣ ቁጥር የመሳሰሉትን መጻፍ አያስፈልግም፡፡

-በመጠይቁ ላይ ግልጽ ያልሆነ ጥያቄ ካለ መጠይቁን የሚያስሞላውን ሰው መጠየቅ ይቻላል፡፡

-እናንተ የምትሰጡት መረጃ ለዚህ ጥናት ከመዋሉ ውጪ ለምንም ተግባር አይውልም፡፡

-መጠይቁ የሚሞላው በግል ነው፡፡

**አጠቃላይ መመርያ**

ይህ የጽሁፍ መጠይቅ ሁለት ክፍሎች አሉት

1.አጠቃላይ መረጃን የሚመለከት መጠይቅና

2. አምስት አማራጮችን የያዙ የምርጫ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

**ክፍል አንድ**

**አጠቃላይ መረጃ**

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች የምትስማሙበትን በሳጥኑ ውስጥ የ (×) ምልክት አድርጉ፡፡

1.የምትማርበት (የምትማሪበት) ትምህርት ቤት ስም-----------------------------------------------

2. ፆታ --------        ወንድ--------    ሴት---------

**ክፍል ሁለት**

የሚከተሉትን ሃሳቦች ካነበብህ/ ካነበብሽ በኃላ ከቀረቡት አማራጮች መካከል በአንዱ ስር (×) ምልክት በማድረግ መልስ ስጥ/ ጭ፡፡

**አማራጭ መልሶች**

5. ዘወትር ይተገበራል

4. አልፎ አልፎ ይተገበራል

3. ለመወሰን እቸገራለሁ

2. አልፎ አልፎ አይተገበርም

1. ፈጽሞ አይተገበርም

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | በልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የግልና የቡድን ተግባራት | | | | | |
| 1.1 | በቡድን በመደራጀት የቡድን ስራዎችን ትሰራላችሁ? | | | | | |
| 1.2 | የግልና የቡድን ተግባራትን ስትሰሩ ሁሉም እኩል እድል ይሰጠዋል? | | | | | |
| 1.3 | በክፍል ውስጥ የግልና የቡድን ተግባራትን ለማከናወን በቂ ጊዜ ይሰጣችኋል? | | | | | |
| 1.4 | የግልና የቡድን ተግባራትን በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ሰርታችሁ ታጠናቅቃላችሁ? | | | | | |
| 1.5 | የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ቡድን ስትመሰርቱ የጾታ ስብጥርን ከግንዛቤ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ውስጥ በማስገባት ነው? | | | | | |
| 1.6 | የግል ወይም የቡድን ተግባራትን ካጠናቀቃችሁ በኃላ ያገኛችሁትን ግኝት እንድታቀርቡ እድል ይሰጣችኃል? | | | | | |
| 1.7 | እያንዳንዱን ተግባር መምህሩ ሞዴል ሆነው ሰርተው ያሳያሉ? | | | | | |
| 1.8 | መምህሩ ተግባራትን ሰርተው ካሳዩ በኃላ ከተማሪዎች ጋር በጋራ ይሰራሉ? | | | | | |
| 2 | በልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የፆታ ተኮር፣ አካቶ ትምህርትና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አተገባበር | | | | | |
| 2.1 | መምህሩ በክፍል ውስጥ በልዩ ልዩ ተግባራት ላይ ሴትና ወንድ ተማሪዎችን ከአድሎ በጸዳ መልኩ በእኩል ያሳትፋሉ (የጾታ እኩልነት ተረጋግጧል) | | | | | |
| 2.2 | የመማር ተግባርን ስታከናውኑ ያለ ስርአተ ጾታ አድልኦ መምህሩ በእኩል አይን ያይዋችኋል? | | | | | |
| 2.3 | የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል? | | | | | |
| 2.4 | ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢ የሆነ ድጋፍ ይሰጣቸዋል? | | | | | |
| 3 | በልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የማንበብ ተግባር? | | | | | |
| 3.1 | የማንበብ ተግባራትን ስትተገብሩ የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ፣ መተንበይ… በአግባቡ ትተገብራላችሁ? | | | | | |
| 3.2 | አቀላጥፎ ማንበብን መምህሩ ሞዴል በመሆን በተግባር አንብበው ያሳያሉ? | | | | | |
| 3.3 | በማንበብ ጊዜ የማንበብ አላባውያንን በሚገባ ትተገብራላችሁ? | | | | | |
| 3.4 | መምህሩ በማንበብ ጊዜ እያንዳንዱ ተማሪ አንብቦ መረዳቱን ይከታተላሉ? | | | | | |
| 3.5 | እያንዳንዱ ተማሪ አቀላጥፎ የማንበብ እድል ይሰጠዋል? | | | | | |
| 3.6 | በማንበብ ጊዜ እክል (ችግር) ሲገጥማችሁ መምህሩ እያንዳንዳችሁን በግል ይረዷችኋል? | | | | | |
| 3.7 | የተማሪዎችን የማንበብ ፍጥነት ለመገምገም መምህሩ ሰዓት ይዘው ያስነብባሉ? | | | | | |
| 3.8 | ለፈጣን አንባቢዎች የማንበብ ተግባርን ካጠናቀቁ በኋል ተጨማሪ የንባብ መጸሃፍ ተዘጋጅቶ እንዲያነቡ ይሰጣቸዋል? | | | | | |
| 3.9 | ከክፍል ውጪ በግል የንባብ ችሎታችሁን እንድታዳብሩ ምክርና ድጋፍ ይሰጣችኋል? | | | | | |
| 4 | በልስራ፣እንስራ፣ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የመጻፍ ተግባር | | | | | |
| 4.1 | የቅድመ መጻፍ ተግባራትን በየደረጃው ታከናውናላችሁ? | | | | | |
| 4.2 | በጽህፈት ተግባር ጊዜ ራሳችሁን ችላችሁ በግል እንድትጽፉ እድል | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ይሰጣችኋል? | | | | | |
| 4.3 | በጽህፈት ተግባር ጊዜ እክል ወይም ችግር ሲገጥማችሁ መምህሩ ይረዷችኋል? | | | | | |
| 4.4 | የጽህፈት ተግባር ካከናወናችሁ በኋላ ግብረ መልስ ይሰጣችኋል? | | | | | |
| 5 | በልስራ፣እንስራ፣ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የማዳመጥ ተግባር | | | | | |
| 5.1 | በማዳመጥ ተግባር ጊዜ ምዘና ወይም ፈተና ይሰጣችኋል? | | | | | |
| 5.2 | የማዳመጥን ተግባር ካከናወናችሁ በኋላ ድጋፍና ማበልጸግይደረግላችኋል? | | | | | |
| 5.3 | አዳምጦ የመረዳት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ ይደረግላቸዋል? | | | | | |
| 6 | በልስራ፣እንስራ፣ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል የንግግር ተግባር | | | | | |
| 6.1 | በግልና በንኡስ ቡድን ንግግር እንድታደርጉ እድልይሰጣችኋል? | | | | | |
| 6.2 | በየምእራፉ ባሉ የንግግር ተግባራት ላይ እንድትናገሩ ለእያንዳንዳችሁ እድል ይሰጣችኋል? | | | | | |
| 6.3 | በንግግር ጊዜ ለሚገጥማችሁ ችግር ማስተካከያ ይሰጣል? | | | | | |
| 7 | በልስራ፣እንስራ፣ስሩ (ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴል ግብረ መልስ፣ ድጋፍና ማበልጸግ | | | | | |
| 7.1 | የመማር ፍላጎታችሁን የሚያነሳሳ እና እንዲጨምር የሚያደርግ በቂና ተገቢ የሆነ ግብረ መልስ እና ድጋፍ ይሰጣችኋል? | | | | | |
| 7.2 | ላከናወናችሁት ተግባር ግብረ መልስ የሚሰጣችሁ ትክክል ወይም ስህተት መሆኑ ተነግሯችሁ ነው? | | | | | |
| 7.3 | የሚሰጣችሁ ግብረ መልስ ወቅቱን የጠበቀና ወድያውኑ ነው? | | | | | |
| 7.4 | ምዘና ወይም ፈተና በአግባቡና በተገቢው ጊዜ ይሰጣችኋል? | | | | | |

## አባሪ ሶስት

## ለመምህራን የቀረበ ቃለመጠይቅ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮለጅ አማርኛ ቋነቋ፣ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ አፋቸውን በአማርኛ የፈቱ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ለሚያስተምሩ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ

ፆታ----------

የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም -------------------------------------------------------

የትምህርት ደረጃ ---------------------------------

የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ አብይ -------------------- ንኡስ ----------------

የአገልግሎት ዘመን----------------------------

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን ----------------------- ሰዓት ----------------------

**ውድ መምህራን**

ይህ ቃለ መጠይቅ የተዘጋጀው በሻሸመኔ ከተማ መስተዳድር ለ8ኛ ክፍል አፍ ፈት ለሆኑት የተዘጋጀ የአማርኛ ቋነቋ ትምህርት የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ በሚል ርእስ ጥናት ለማካሄድና ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃ ለመሰብሰብ ታስቦ ነው፡፡ ስለዚህ ለጥናቱ መሳካት ከዚህ በታች ለቀረቡ ቃለ መጠይቆች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት የበኩላችሁን ትብብር እንድታደርጉልኝ እጠይቃለሁ፡፡

በቅድሚያ ውድ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ ስላደረጋችሁልኝ ትብብር ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

**መነሻ ጥያቄዎች**

1.የልስራ፣እንስራ፣ ስሩ(ቀስ በቀስ እያበቁ መሄድ) ሞዴልን በየክፍለጊዜው በአግባቡ በክፍል ውስጥ ይተገብራሉ?

2.እርሶ ሞዴል ሆነው ለተማሪዎች እንዲያሳዩ በሚጠይቅ ተግባር (በልስራ) ላይ ሞዴል ሆነው ተግባራትን ለተማሪዎች ሰርተው ያሳያሉ?

3.በእንስራ ጊዜ ከተማሪዎች ጋር በመሆን ተግባራትን አብረው ይሰራሉ?

4.ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን ራሳቸውን ችለው በግልና በቡድን እንዲሰሩ እድል ይሰጣቸዋል?

5.በንባብ ተግባር ጊዜ ሞዴል ሆነው በማንበብ ተማሪዎች ልዩ ል የማንበብ ተግባር ሲያከናውኑ በመከታተል ተማሪዎችን ይረዳሉ

6.ተማሪዎች የንግግር እና የጥህፈት ተግባርን ተግባርን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል

7.የእለቱን፣የሳምንቱን እና የምእራፉን ትምህርት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሰርተው ያጠናቅቃሉ?

8.በትምህርት ሂደት የተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ የሚያጠናክር ተገቢ የሁነ አዎንታዊ ማበረታቻ ይሰጣሉ?

9.በማያቋርጥ ሂደት ተማሪዎች እንዴት እየተማሩ እንደሆነ መረጃ ለመሰብሰብ ተከታታይ ምዘና ይሰጧቸዋል?

10.በክፍል ውስጥ የጾታ እኩልነትን የሚያረጋግጡ (የሚያዳብሩ) የማስተማርያ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ?

11.የሁሉንም ተማሪዎች ብዝሃ ፍላጎት ለማርካትና መገለልን ለመቀነስ አካቶ ትምህርትንና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸዋል?

# አባሪ አራት

በኦሮምያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ መስተዳድር በናሙና በተመረጡ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍል አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ በማስተማር ላይ ያሉ መምህር አንድ ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች

1. አ፡ በቅድሚያ ለቃለመጠይቁ ስለተባበሩኝ አመሠግናለሁ!

   መ1፡ እኔም አመሰግናለሁ

2. አ፡ የት/ት ደረጃዎን ቢገልጹልኝ

   መ1፡ የዲፕሎማ ምሩቅ ነኝ የሰለጠንኩበት አብይ የትምህርት አይነትም አማርኛ ነው፡፡

3. አ፡ እኔ ልሰራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ስልጠና ወስደዋል?

   መ1፡ በሚገባ! አስር ቀን ስልጠና ተሰጥቶናል፡፡ እኔም በዚህ ስልጠና ላይ ደስ ብሎኝ ተሳትፌአለሁ!

4. አ፡ የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ ሞዴልን በየክፍለ ጊዜው በአግባቡ ይተገብራሉ?

   መ1፡ የግድ ነዋ! ምክንያቱም አዲሱን የተማረውን መፅሀፍና የመምህሩን መምሪያ ስለምጠቀም ምን አማራጭ አለኝ? መጽሀፉን ከተጠቀምክ ግዴታ ነው፡፡

5. አ፡ እርስዎ ሞዴል ሆነው ለተማሪዎ እንዲያሳዩ በሚጠይቅ ተግባር (በእኔ ልስራ) ላይ ሞዴል ሆነው ተግባራትን ለተማሪዎች ሰርተው ያውቃሉ?

   መ1፡ አዎ! መፅሐፉ በሚያዘው መሠረት ማንኛውንም ተግባር ተማሪው ከመተግበሩ በፊት ሞዴል ሆኜ አሳያለሁ፡፡

6. አ፡ በአብረን እንስራ ጊዜ ተግባራትን ከተማሪዎች ጋር አብረው ይተገብራሉ?

   መ1፡ በእርግጥ ተግባራትን ከተማሪዎች ጋር አብሬ እተገብራለሁ ነገር ግን በክፍል ውስጥ ያለው የተማሪ ቁጥር፣ የተማሪ መፅሀፍ እጥረት፣ የተማሪው ሥነምግባር ጉዳይ ተግባራቱን ሙሉ በሙሉ በሞዴሉ መሰረት ለመተግበር ተግዳሮት ሆኖብኛል፡፡

7. አ፡ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን ራሳቸውን ችለው በግልና በቡድን እንዲሰሩ

እድል ይሰጧቸዋል?

መ፡ በእኔ ልስራ ጊዜ ተግብሬ ያሳየሁትን፣ በአብረን እንስራ ጊዜ አብረን የተገበርነውን በግልና በቡድን እንዲሰሩ አደርጋቸዋለሁ፡፡ ይሁን እንጂ እያንዳንዱን ተማሪ በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ምን እንደተገበረ ለማየት የጊዜ እጥረት ያጋጥመኛል፤ ስለዚህ ባለኝ ጊዜ የተወሰኑ ተማሪዎችን ብቻ ለማየት እገደዳለሁ፡፡

8. አ፡ በንባብ ተግባር ጊዜ ሞዴል ሆነው በማንበብ ተማሪዎች ልዩ ልዩ የማንበብ ተግባር ሲያከናውኑ በመከታተል ተማሪዎችን ይረዳሉ?

መ1፡ ሞዴል ሆኖ ለማንበብ ችግር የለብኝም ያለምንም ስህተት በጥሩ የድምፅ ቅላፄ ሞዴል ሆኜ ለተማሪዎች አነብላቸዋለሁ፡፡ እዚህ ላይ ግን አንድ ችግር አለ እያንዳንዱ ተማሪ በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ማስነበብ አዳጋች ነው፡፡ በራሴ በኩል የማደርገው ከቡድን ውስጥ አንድ አንድ ተማሪ እንዲያነብ እድል እሠጥና የማንበብ ግድፈት ሲፈጥሩ በተቻለ መጠን ስህተታቸውን እንዲያርሙ እረዳቸዋለሁ፡፡

9. አ፡ ተማሪዎች የንግግርና የፅህፈት ተግባርን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል?

መ1፡ በእርግጥ በተቻለኝ መጠን ተገቢ ክትትልና ድጋፍ አደርግላቸዋለሁ፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም ይህን ተግባር ለመተግበር ችግር አለ፡፡ ሁሉንም ተማሪ በንግግር ትምህርት ጊዜ ለማሣተፍና ለመገምገም አዳጋች ነው፡፡ በፅህፈትም ጊዜ እያንዳንዱ ተማሪ እንዴት እንደሚጽፍ በነፍስ ወከፍ ለመከታተልና ድጋፍ ለማድረግ ከተማሪው ቁጥር አንፃር አስቸጋሪ ነው፡፡

10. አ፡ የእለቱን፣ የሳምንቱን እና የምዕራፉን ትምህርት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሰረተው ያጠናቅቃሉ?

መ1፡ ያልኩህ ችግሮች እንዳሉ ሆነው የሳምንቱንና የወሩን ትምህርት በእቅዱ መሠረት ተግባራዊ አደርጋለሁ፡፡ የአመቱን ትምህርት አጠቃሎ ለማጠናቀቅ ግን አልችልም፡፡ የጊዜ እጥረት ያጋጥመናል፡፡ ጊዜዎች በስብሰባ ይባክናሉ፡፡

11. አ፡ በትምህርት ሂደት የተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ የሚያጠናክር ተገቢ

የሆነ አዎንታዊ ማበረታቻ ይሰጣሉ?

መ1፡ በደንብ እንጂ! ተማሪዎቹን ሌላ የምሰጣቸው ነገር ባይኖረኝም፣ በጣም ጥሩ! ጎበዝ! በማለትና ለተሳትፏቸው መጠነኛ ማርክ በመስጠት አበረታታቸዋለሁ፡፡

12. አ፡ በማያቋርጥ ሂደት ተማሪዎች እንዴት እየተማሩ እንደሆነ መረጃ ለመሰብሰብ ተከታታይ ምዘና ለተማሪዎች ይሰጣሉ?

መ1፡ በሚገባ እሰጣለሁ! ተማሪዎቹ የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል ተረድተውታል የመሚለውን ለማወቅ ተከታታይ ምዘና ባወጣሁት ሳምንታዊ፣ ወርሃዊና አመታዊ እቅድ መሠረት ምዘና ለተማሪዎቹ እሰጥና እገመግማቸዋለሁ፡፡

13. አ፡ በክፍል ውስጥ የፆታ እኩልነትን የሚያረጋግጡ ወይም የሚያዳብሩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ?

መ1፡ በሚገባ እጠቀማለሁ ስለሞዴሉ አተገባበር ሥልጠና ሲሠጥ ባገኘሁት እውቀትመሠረት ከቡድን ምስረታ ጀምሮ በትምህርቱ ይዘት ላይ ምሳሌ ስሰጥ፣ ጥያቄ ስጠይቅ፣ ጥያቄ እንዲመልሱ ሳደርግ ፍትሃዊ የፆታ እኩልነት እንዲረጋገጥ አደርጋለሁ፡፡

14. አ፡ የሁሉንም ተማሪዎች ብዝሃ ፍላጎት ለማርካት እና መገለልን ለመቀነስ አካቶ ትምህርትን እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

መ1፡ ለጊዜው እኔ በማስተምርበት ክፍል ውስጥ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሉም፡፡ ነገር ግን በተለያየ ምክንያት የሥነልቦና ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለመርዳት እሞክራለሁ፡፡ በክፍል ውስጥም እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ እጥራለሁ፡፡

15.አ፡ ለቃለ መጠይቁ ስለተባበሩኝ አመሠግናለሁ!

መ1፡ እኔም አመሠግናለሁ!

# አባሪ አምስት

በኦሮምያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ መስተዳድር በናሙናነት በተመረጡ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍል አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ በማስተማር ላይ ያሉ መምህር ሁለት ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች

1. አ፡ በቅድሚያ ለቃለመጠይቁ ስለተባበሩኝ አመሠግናለሁ!

   መ2፡ እሺ እኔም አመሰግናለሁ

2. የትምህርት ደረጃዎን ቢገልፁልኝ?

   መ.2 በማኔጅመንት ወይም በአስተዳደር የመጀመሪያ ዲግሪ አለኝ

3. አ፡ እኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴል ስልጠና ወስደዋል?

   መ2፡ ሥልጠናውን ወስጃለሁ፡፡ የሰለጠንኩበት የትምህርት አይነት አስተዳደር ቢሆንም የአማርኛ ቋንቋ መምህር እጥረት በትምህርት ቤታችን ስላለ የአማርኛ ቋንቋ እንዳስተምር ተመድቤ እየሰራሁ ነው፡፡

4. አ፡ የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴልን በክፍለ ጊዜው በአግባቡ በክፍል ውስጥ ይተገብራሉ?

   መ2፡ ምን ምርጫ አለኝ ግድ ነዋ፡፡ መፅሐፉ ሞዴሉን መሠረት አድርጎ ስለተዘጋጀ መፅሀፉ የግድ እንድትተገብረው ያደርገኛል፡፡ መፅሀፉን እስከተጠቀምኩ ድረስ ሞዴሉን መተግበር ግድ ነው፡፡

5. አ፡ እርሶ ሞዴል ሆነው ለተማሪዎች እንዲያሳዩ በሚጠይቅ ተግባር (በእኔ ልስራ) ላይ ሞዴል ሆነው ተግባራትን ለተማሪዎች ሠርተው ያሳያሉ?

   መ2፡ የመምህሩ መምሪያ በሚያዘው መሠረት ተግብሬ አሳያለሁ፡፡ ተማሪዎች በቡድንና በግል የተሰጣቸውን ተግባር ከመስራታቸው በፊት የት/ቱን አጠቃላይ መልክ ላሳያቸው እሞክራለሁ፡፡

6. አ፡ በአብረን እንስራ ጊዜ ተግባራትን ከተማሪዎች ጋር አብረው ይተገብራሉ?

   መ2፡ እተገብራለሁ፡፡ ነገር ግን ትግበራው ከሙሉ ተማሪ ጋር ነው የሚሆነው አብዛኛውን ጊዜ እንደዚህ በገለፃ መልክ ለሁሉም ተማሪ

መረጃ ከማቀበል ውጪ በግል ከእያንዳንዱ ተማሪ ጋር አብሮ ለመተግበር አስቸጋሪ ነው የሚሆነው፡፡ ችግሩን አንተም ታውቀዋለህ የመማሪያ ክፍል ሁኔውና የተማሪው ብዛት ይህንን ለማድረግ እድል አይሰጥም፡፡

7. አ፡ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የተለያየ ተግባራትን እንዲተገብሩና በግልና በቡድን እንዲሰሩ እድል ይሰጣቸዋል?

 መ2፡ ተግባራትን በቡድን ለማሰራት ብዙም አዳጋች አይደለም በግል ተግባራትን ሰጥቶ እያንዳንዱን ተማሪ እንደሚሰራ ወይም ተግባራትን እንዴት እንደሚተገብሩ ለመከታተል አዳጋች ነው፡፡

8. አ፡ በንባብ ተግባር ጊዜ ሞዴል ሆነው በማንበብ ተማሪዎች ልዩ ልዩ የማንበብ ተግባር ሲያከናው በመከታተል ተማሪዎችን ይረዳሉ?

 መ2፡ መፅሐፉ አድርጉ ስለሚል ሞዴል አንባቢ ሆኜ ደግሜ በማንበብ ተማሪዎቼ ልክ እኔ ባነበብኩበት የድምፅ ቅላፄ መሠረት እንዲያከናው ወይም እኔ ባነበብኩበት መሠረት እንዲያነቡ እድል ሰጥቸዋለሁ፡፡ መቼም ያ ሁሉ የክፍል ተማሪ በግል ክትትል ለማድረግ በኛ አገር ፈፅሞ አይሞከርም፡፡

9. አ፡ ተማሪዎች የንግግርና የፅህፈት ተግባርን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል?

 መ2፡ በመጠኑም ቢሆን ክትትልና ድጋፍ አደርግላቸዋለሁ ነገር ግን ሁሉንም ተማሪ በክትትል በአንድ ክፍለ ጊዜ ለመርዳት አስቸጋሪ ነው፡፡ እያንዳንዱን ተማሪ ለመከታተል እና እንዲናገር እድል ለመስጠት በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ የማይታሰብ ነው፡፡ ድጋፍም እንደዚሁ ለሁሉም ተማሪ በእኩል ለመድረስ ፈታኝ ነው፡፡ ያስቸግራል!

10. አ፡ የእለቱን፣ የሳምንቱን እና የምዕራፉን ትምህርት በተሰጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ሰርተው ወይም ተግብረው ያጠናቅቃሉ?

 መ2፡ የእለቱን የሣምንቱን እና የምዕራፉን ትምህርት በተመደበለት ጊዜ ገደብ ውስጥ ተግብሬ ለማጠናቀቅ እችላለሁ፡፡ እያደረኩትም ነው፡፡ ነገር ግን ምን መሰለህ የእለቱን፣ የሳምንቱን እና የምዕራፉን

ትምህርት በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የአመቱ ትምህርት በአንድ ወር ዘግይቶ ይጀመራል፤ በሴሚስተር ዝግ እንደዚሁ ሁለት ሣምንት ይዘጋል፣ የተለያዩ የትምህርት ቤት ስብሰባዎች በየጊዜው ይደረጋሉ፣ በትምህርት ቤት እና በትምህርት ቢሮ አማካኝነት በየጊዜው ስብሰባ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ደግሞ የአመቱን የትምህርት ጊዜ በእጅጉ ይጎዱታል፡፡ በዚህም ምክንያት በመፅሐፉ ውስጥ በአንድ አመት የትምህርት ወቅት እንዲጠናቀቁ ተለክተው የተሰጡ ተግባራት በአንድና በሁለት ምዕራፍ ወደኋላ ይቀራሉ፡፡ ታዲያ የአመቱ ትምህርት ማጠናቀቅ ግዴታ በመሆኑ ተግባራትን በጥድፊያ ሠርተን ለማጠናቀቅ እንገደዳለን፡፡ ይህ ደግሞ ሞዴሉን ሙሉ በሙሉ ለመተግበር አያስችለንም፡፡

11.አ፡ በትምህርት ሂደት የተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ የሚያጠናክር ተገቢ የሆኑ አዎንታዊ ማበረታቻ ይሰጣሉ?

መ2፡ እሰጣለሁ፡፡ ማበረታቻ እኮ ተማሪን ያነቃቃል፡፡ በተለይ ህፃናት ሲሆኑ እጅግ በጣም ደስ ይላቸዋል፡፡ በተጨማሪ ተማሪዎች በተግባራት ላይ ለሚጠየቁት ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ከአዎንታዊ ማበረታቻው ጎን ለጎን ስህተት ከፈፀሙ ስህተቱ እንዴት ሊከሰት እንደቻለና በምንስ መንገድ ስህተቱ እንደሚታረም ብልሃቱን ጭምር በመንገር ነው፡፡

12. አ፡ በማያቋርጥ ሂደት ተማሪዎች እንዴት እየተማ እንደሆነ መረጃ ለመሰብሰብ ተከታታይ ምዘና ይሰጧቸዋል?

መ2፡ ባወጣሁት አመታዊ እቅድ መሠረት ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት ምን ያህል ውጤታማ ናቸው የሚለውን ለመገምገም ተከታታይ ምዘና እሰጣለሁ፡፡ ከምዘናው ተነስቼ ተማሪው በተማሪው ትምህርት ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ መረጃ እሰበስባለሁ የሰበሰብኩትን መረጃ፣ ያለውን ጠንካራና ደካማ ጎን እገመግማለሁ ባገኘሁትም ውጤት ላይ ተመርኩዤ የተማሪዎችን ክፍተት በመለየት እረዳቸዋለሁ፡፡

13. አ፡ በክፍል ውስጥ የፆታ እኩልነትን የሚያረጋግጡ ወይም የሚያዳብሩ

የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ?

መ2፡ ስለማስተማርያ ሞዴሉ ለስልጠና በተሰጠን መሠረት የፆታ እኩልነትን የሚያረጋግጡ ወይም የሚያዳብሩ ዘዴዎችን እጠቀማለሁ፡፡ ይኸውም ምሳሌ ስሰጥ ሁለቱንም ፆታ ባማከለ መልኩ ነው የምሰጠው፡፡ ጥያቄ ስጠይቅና ለጥያቄ መልስ እንዲሰጡ ሳደርግ ሁለቱንም ፆታ በእኩል ነው የማሳተፈው፡፡

14. አ፡ የሁሉንም ተማሪዎች ብዝሃ ፍላጎት ለማርካት እና መገለልን ለመቀነስ አካቶ ትምህርት እና የልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸዋል?

መ2፡ የአካል ጉዳተኛ ተማሪ እኔ በማስተምርበት ክፍል ውስጥ የለም፡፡ ቢኖር ግን በወሰድኩበት ስልጠና መሠረት ልረዳቸው እሞክራለሁ፡፡ እነዚህ እ-እ-እ- ወጣ ያለ ባህሪ ያላቸውን ተማሪዎች እና ወጣ ያለ አስተሳሰብ ያላቸውን ተማሪዎች በተቻለኝ አቅም ከባህሪያቸው አንፃር ፍላጎታቸውን በመለየት ልረዳቸው እሞክራለሁ፡፡

15.አ፡ ለቃለ መጠይቁ ስለተባበሩኝ አመሠግናለሁ!

መ2፡ እኔም አመሰግናለሁ

# አባሪ ስድስት

በኦሮምያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ መስተዳድር በናሙናነት በተመረጡ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍል አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ በማስተማር ላይ ያሉ መምህር ሶስት ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች

1. አ፡ በቅድሚያ ለቃለመጠይቁ ስለተባበሩኝ አመሠግናለሁ!

   መ3፡ አይ ምንም አይደለም!

2. አ፡ የትምህርት ደረጃዎን ቢገልፁልኝ

   መ3፡ የዲፕሎማ ምሩቅ ነኝ፡፡ ሜጀሬ አማርኛን ማስተማር ነው፡፡

3. አ፡ እኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴልን በተመለከተ ስልጠና ወስደዋል?

   መ3፡ አዎን በ2008 ዓ.ም የ10 ቀን ስልጠና ወስደናል፡፡ ተመልሰው ሳይመጡ በዚያው ሄዱ እንጂ!

4. አ፡የእኔ ልስራ፣ አብረን እንስራ፣ እናንተ ስሩ የማስተማር ሞዴልን በየክፍለ ጊዜው በአግባቡ በክፍል ውስጥ ይጠቀማሉ?

   መ3፡ አዎን በሚገባ እተገብረዋለሁ በመጀመሪያ የሚተገብረውን ተግባር እኔ ሰርቼ አሳያቸዋለሁ በሁለተኛ ደረጃ ተግባራትን አብረን እንተገብራለን በመጨረሻም ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው የሚሰሩበትን እድል እሰጣቸዋለሁ፡፡ ዞሬም እከታተላቸዋለሁ፡፡ ጥያቄ እንዲጠይቁም እድል እሰትና ከጠየቁኝ ለጥያቄያቸው መልስ እሰጣቸዋለሁ፡፡

5. አ፡ እርሶ ሞዴል ሆነው ለተማሪዎች እንዲያሳዩ በሚጠይቅ ተግባር (በእኔ ልስራ) ላይ ሞዴል ሆነው ተግባራትን ለተማሪዎች ሰርተው ያሳያሉ?

   መ3፡ የመምህሩ መምሪያ በሚያዘኝ መሠረት በማንበብ ተግባር፣ በመፃፍ ተግባር፣ በማዳመጥና በመናገር ተግባራት ላይ በደንብ ነው ሠርቼ ወይም ተግብሬ የማሳያቸው፡፡

6. አ፡ በአብረን እንስራ ጊዜ ተግባራትን ከተማሪዎች ጋር አብረው ይተገብራሉ?

መ3፡ መተግበሩን እተገብራለሁ ይሄውልህ ወንድሜ ሞዴሉን በተዋጣለት መልክ ለመተግበር ግን እያንዳንዱ ተማሪ በነፍስ ወከፍ የመማሪያ መፅሐፍ ሊያገኝ ይገባል፡፡ እኔ በማስተምርበት ትምህርት ቤት ግን የተማሪ መፅሐፍ የለም፡፡ ታዲያ መፅሐፍ ተማሪው በእጁ ሳይኖረው እንዴት አድርገህ ነው አብረህ የምትተገብረው? አስቸጋሪ ነው!

7. አ፡ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን ራሳቸውን ችለው በግልና በቡድን እንዲተገብሩ እድል ይሰጣቸዋል?

መ3፡ እድል መስጠት እሰጣቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን እኔ እድሉን ብሰጣቸውም እጃቸው ላይ የተማሪው መፅሐፍ ከሌለ ምን ዋጋ አለው? አንዳንድ ተግባራትን ክፍል ውስጥ በተገኘው መፅሐፍ መጠን ቡድን ሠርተው በቡድን እርስ በርሳቸው እንዲማሩ እድል እሰጣቸዋለሁ፡፡

8. አ፡ በንባብ ተግባር ጊዜ ሞዴል ሆነው በማንበብ ተማሪዎች ልዩ ልዩ የማንበብ ተግባር ሲያከናው በመከታተል ተማሪዎችን ይረዳሉ?

መ3፡ ሞዴል ሆኜ አነብባለሁ፡፡ በማነብበት ጊዜ በተቻለኝ አቅም ያለምንም ስህተት ለማንበብ እሞክራለሁ፡፡ በየክፍለ ጊዜው እያንዳንዱን ተማሪ ንባብን እንዲተገብርና ሲተገብርም እያንዳንዱን ተማሪ በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ለመከታተል አይቻልም፡፡ ይሁን እንጂ በየክፍለ ጊዜው የማንበብ እድል የሚደርሳቸውን ተማሪዎች እንዴት እንደሚያነቡ ተከታትዬ አስፈላጊን ድጋፍ አደርግላቸዋለሁ፡፡ ሌላው ችግር ለፈጣን ተማሪዎች ተጨማሪ የንባብ መፅሐፍ ለማግኘት መቸገር ነው፡፡

9. አ፡ ተማሪዎች የንግግርና የፅህፈት ተግባርን በክፍለ ውስጥ ሲተገብሩ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል?

መ3፡ ክትትልና ድጋፍ አደርጋለሁ፡፡ ነገር ግን ከላይ ልገልፅልህ እንደሞከርኩት የመፅሐፍ እጥረትና የተማሪ ቁጥር ሁሉንም ተማሪ በአንድ ክፍለ ጊዜ ለመድረስ አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለዚህ እድል የደረሳቸው ተማሪዎች ክትትልና ድጋፍ አደርግላቸዋል፡፡

10. አ፡ የእለቱን፣ የሣምንቱን እና የምዕራፉን ትምህርት በተሰጠው የጊዜ

ገደብ ውስጥ ሠርተው ወይም ተግብረው ያጠናቅቃ?

መ3፡ የእለቱን፣ የሳምንቱን እና የምዕራፉን ትምህርት በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ለመተግበር   የጊዜ እጥረት ያጋጥማል፡፡ ለዚህም ምክንያት ናቸው የምላቸው፡፡

1. ብዙ ተማሪ በአንድ ክፍል ውስጥ መኖር
2. በአመቱ መጀመሪያ ዘግይቶ ትምህርት መጀመሩ
3. በልዩ ልዩ ስብሰባ የትምህርት ጊዜ መባከኑ
4. የሁለተኛ ወሰነ ትምህርት ዘግይቶ መጀመር
5. የተማሪ መፅሐፍ እጥረት መኖር ናቸው፡፡

11. አ፡ በትምህርት ሂደት የተማሪዎችን የትምህት ተሳትፎ የሚያጠናክር ተገቢ የሆነ አዎንታዊ ማበረታቻ ይሰጣሉ?

መ3፡ እሰጣለሁ፡፡ የትምህርት ተሳትፏቸውን ለማጠናከር የተሰጣቸውን ተግባር ሰርተው ካጠናቀቁ በኋላ የሰሩት ተግባር ትክክል ሆነ አልሆነ ስለሞከሩ ብቻ ማበረታቻ እሰጣቸዋለሁ፡፡ ይህንን ሣደርግ ግን ከማበረታቻው በኋላ የሰሩት ተግባር ተገቢ ነው ወይም አይደለም ለሚለው ማብራሪያ በመስጠት በትክክል የሰራው እንዲያጠናክር በስህተት የሰራው ደግሞ ስህተቱን እንዲያርም አደርጋለሁ፡፡

12. አ፡ በማያቋርጥ ሂደት ተማሪዎች እንዴት እየተማሩ እንደሆነ መረጃ ለመሰብሰብ ተከታታይ ምዘና ለተማሪዎች ይሰጧቸዋል?

መ3፡ ተከታታይ ምዘና እሰጣለሁ፡፡ ነገር ግን ተከታታይ ምዘናው የሚሰጠው አጫጭር ጥያቄዎች፣ አንድ የጥያቄ አይነትት ውስን ጥያቄዎን ብቻ ነው ለተማሪዎች ምዘና የምንሰጠው፡፡ ሌላው ቀርቶ የሴሚስተር አጋማሽ ፈተና እና የሴሚስተር ፈተናዎችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ነው የምንሰጠው፡፡ ይህ ደግሞ ውጤታማ አያደርግም፡፡ በቂ የሆነ ቁሳቁስ በትምህርት ቤቱ በኩል ቢቀርብልን ውጤታማ እንሆናለን፡፡

13. አ፡ በክፍል ውስጥ የፆታ እኩልነትን የሚያረጋግጡ ወይም የሚያዳብሩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ?

መ3፡ የፆታ እኩልነት በኔ ክፍለ ጊዜ የተረጋገጠ ነው፡፡ ለምን መሰለህ ይህንን የምለው ከቡድን ምስረታ ጀምሮ ልዩ ልዩ ተግባራትን ሲሰሩ የፆታ ስብጥሩ የተረጋገጠ ነው፡፡ በሁሉም ተግባር ላይ ወንድና ሴት ተማሪዎች በእኩል ይሳተፋሉ፡፡

14.አ፡ የሁሉንም ተማሪዎች ብዝሃ ፍላጎት ለማርካት እና መገለልን ለመቀነስ አካቶ

15. ትምህርት እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸዋል?

መ3፡ እኔ በማስተምርበት ክፍል ውስጥ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ማለትም አይነስውራን እና መስማት የማይችሉ ተማሪዎች የሉም፡፡ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ግን በሞጁሉ መመርያ መሠረት እረዳቸዋለሁ፡፡

16. አ፡ ለቃለ መጠይቁ ስለተባበሩኝ አመሠግናለሁ!

መ3፡ እኔም አመሠግናለሁ፡፡

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለጸውና የፈረምኩት ተማሪ፣ ይህ በሻሸመኔ ከተማ መስተዳድር በሻሸመኔ ከተማ በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ሞዴል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ በሻሸመኔ ከተማ በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤት በስምንተኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርእስ የቀረበው ጥናት የራሴ ስራ መሆኑንና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ዋቢ ጽሁፎች በሙሉ ምንጫቸውን በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ካሳሁን አጤሮ

ፊርማ---------------------